ሦስት

የግርጌ ማስታወሻዎች

1 በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በግልጥ ካልተጠቀሰ በቀር ቤተ ክርስቲያን የተባለችው የምዕራብዋ ማለትም የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ወይም ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያን ናቸው::

2 በእኛ አገርና በዓለምም ሁሉ የፕሮቴስታንቶች ትክክለኛ መጠሪያ ወንጌላውያን (Evangelicals) ነው:: ፕሮቴስታንት (ተቃዋሚዎች) የተባሉት መጀመሪያ ላይ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንን ትምህርት በመቃወም ጥለዋት የወጡት ናቸው:: ወንጌላውያን የሚባሉት እንደ ወንጌል ቃል ኃጢአተኛው ሰው የሚጸድቀው በእግዚአብሔር ጸጋ እና በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ብቻ ነው ብለው ስለሚያምኑ ነው::

3 "ካሪዝማ" የግሪክ ቃል ሲሆን አንዱ ትርጓሜው (የመንፈስ ቅዱስ) ሥጦታ ማለት ነው::

4 "ሞገድ" የተባለው በእንግሊዝኛው "Wave" የሚለው ቃል ነው:: "ሦስተኛ" የተባለው ጳንጠቆስጤአዊው ሪቫይቫል እንደ አንደኛ፣ ካሪዝማዊው ተሐድሶ ደግሞ እንደ ሁለተኛ ተቆጥረው ነው:: "ሦስተኛ ሞገዶች" በትምህርትና በልምምድ ልክ እንደ ካሪዝማውያኑ ሲሆኑ ለራሳቸው የመረጡት ስያሜ ግን ይሽኛው ነው::

5 እነዚህ ስታቲስቲካዊ አሐዞች የተወሰዱት David B. Barrett "The 20th Century Pentecostal/ Charismatic Renewal in the Holy Spirit, with its Goal of World Evangelization" በሚል ርዕስ ካዘጋጀው ጽሑፍ ላይ ነው:: David B. Barrett አሐዞቹን ያገኛቸው ከ"International Bulletin of Missionary Research" የ July 1988 እትም ላይ ነው::

6 ይኸ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አሐዝ አይደለም::

7 Johnstone, Patrick. "Operation World" (5th Edition), Om Publishing, 1993.

8 "ግትሮ ተሐድሶ" ወንድሚ ንጉሚ ቡልቾ ከብዙ አመታት በፊት counter reformation የሰጠው ትርጓሜ ነው:: አሁን ለውጦት ወይም አሻሽሎት እንደሆነም አላውቅም::

9 ገብረሀይወት ባይከዳኝ፤ "አጤ ምኒልክና ኢትዮጵያ" አስመራ 1904 ዓ.ም. ገጽ 23

አራት

ቅዱስ መንፈሱ እና ኢትዮጵያ

የቅዱስ መንፈሱ ድምፅ ወደ ቤተ ክርስቲያን የተመለሰበትን ሂደት ነው በሦስተኛው ምዕራፍ ውስጥ የተመለከትነው:: ጳንጠቆስጤአዊው ልምምድ በዚያ ወቅት ለአራት መቶ ጥቂት ፈሪ አመታት ያስቆጠረው የተሐድሶው እንቅስቃሴ አካል ነው:: ጳንጠቆስጤአዊው ልምምድ ከተሐድሶው እንቅስቃሴ የተለየና የተነጠለ ሳይሆን የተሐድሶው እንቅስቃሴ ውጤት ነው:: ጳንጠቆስጤአዊው ልምምድ የተሐድሶው እንቅስቃሴ ተሠውረው የነበሩ መሠረታዊ እውነቶችን፣ አንዱን በሌላው ላይ፣ ደረጃ በደረጃ፣ በቅደም ተከተል፣ እየገለጠ በዚያን ጊዜ የደረሰበት የዕድገት ደረጃ ነው:: ለተሐድሶው እንቅስቃሴ "ተራማጅ" የሚል ቅጽል ያወጣሁለት ለዚህ ነው::

የ"ቅዱስ መንፈሱ" ድምፅ ወደ ኢትዮጵያም ቤተ ክርስቲያን የተመለሰው በጳንጠቆስጤአዊው ልምምድ ውስጥ ነው:: ጳንጠቆስጤአዊው ሪቫይቫል በኢትዮጵያ ውስጥ በተከሰተበት ጊዜ እንዲከሰት በቤተ ክርስቲያን ውስጥና ከቤተ ክርስቲያን ውጭ መገጣጠም የነበረባቸው ብዙ ቅድመ ሁኔታዎች ነበሩ:: በዚህ በአራተኛው ምዕራፍ ውስጥ ከእነዚህ ቅድመ ሁኔታዎች ዋና ዋናዎቹን እናነሳለን::

ይህንን የምናደርገው ሁል ጊዜ በሥራ ላይ ያለችውን የእግዚአብሔርን ጣት በቤተ ክርስቲያንና በአንድ አገር ታሪክ ውስጥ ማስተዋል እንድንችል ነው:: በቤተ ክርስቲያን ውስጥና ከቤተ ክርስቲያን ውጭ የሚከናወኑ ታሪካዊ ድርጊቶች ሁሉ ትክክለኛ መልካቸውንና ትክክለኛ ትርጉማቸውን የሚያገኙት ከዚህ አንፃር ሲታዩ ብቻ መሆኑን ለማስገንዘብም ነው::

ኦርቶዶክሳዊ አስተዋጽዖ

በኢትዮጵያ በተከሰተ ጳንጠቆስጤአዊ ሪቫይቫል ውስጥ ስለ ኦርቶዶክሳዊ ተቃውሞ ካልሆነ በቀር ስለ ኦርቶዶክሳዊ አስተዋጽኦ ያውም አዎንታዊ

ስለሆነ አስተዋጽዖ መነገሩ የሚያስገርማቸውም፣ የሚያስቆጣቸውም ብዙ ሰዎች በሁለቱም በኩል ሊኖሩ ይችላሉ። ሆኖም በኢትዮጵያ ውስጥ ስለ ተከናወነ ክርስቲያናዊ ታሪክ የሚያወሳ ጽሑፍ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንን በበጎ ወይም በክፉ ብቻ ሳይሆን በሁለቱም ሳያነሳት ቢያልፍ ፍትሐዊ ሊሆን አይችልም።

በዚህ ስፍራ በበጎ ለመነሳትዋ ምክንያቱ ሪቫይቫል በወና ሁኔታ ውስጥ (in a state of vacuum) ተከስቶ አለማወቁ ነው። ዳራ ያስፈልገዋል። ከዳራዎቹም ሁሉ ቀዳሚው ዳራ የቤተ ክርስቲያን በስፍራው መኖር ነው። ሪቫይቫል የሚከሰተው በቤተ ክርስቲያን ማለትም በአማኞች መካከል ነውና።

ጳንጠቆስጤአዊው ሪቫይቫል በኢትዮጵያ በተለኮሰ ጊዜ ከፍተኛውን ማገዶ ያበረከተችው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ነበረች። በሪቫይቫሉ ውስጥ ሕይወታቸው ከተለወጠው መካከል በጸሐፊው ግምት ዘጠና ከመቶ የሚሆኑት ኦርቶዶክሳውያን ወጣቶች ነበሩ። የደህንነት ምሥጢር ገና ያልተገለጠላቸው ቢሆኑም እንኳን ስለ ጌታ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግንዛቤ ነበራቸው። እናቱ በድንግልና እንደ ወለደችው፤ ስለ አምላክነቱና ስለ ሰውነቱ፣ ስለ ሞቱ፤ ስለ ትንሳኤውና ስለ ዳግም ምጽአቱ ያውቃሉ። ይህንን ዕውቀት የሰጠቻቸው ተወልደው ያደጉባት የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ናት።

ይህም ቀላል ነገር አይደለም። አንድ ሰው ኃጢኣተኛ ሆኖ ቢወለድ በጣም ሰፊ ዕድል የሚኖረው የሺንቶ ወይም የቡዲሀስት እምነት ተከታይ ለመሆን ነው። ሕንዳዊ ሆኖ ቢወለድ የሒንዱ፣ ሳውዲ አረባዊ ሆኖ ቢወለድ ደግሞ የእስልምና እምነት ተከታይ ለመሆን ነው በጣም ሰፊ ዕድል የሚኖረው። እንደዚሁም እነዚህ ወጣቶች ኦርቶዶክሳዊ ክርስቲያን ለመሆን የቻሉት ኢትዮጵያዊ ሆነው ስለ ተወለዱ ነበር። ከእነርሱ ጋር የወንጌሉን ቃል ለመነጋገር አስቀድመው የሚያውቋቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶች በመነሻነት በጣም አገልግለዋል። በራሳቸው የሃይማኖት መጽሐፍ ውስጥ የተጻፈውን፣ የሚያውቁትን እውነት በሕይወታቸው እንዲለማመዱት ነው የሚመስከርላቸው።

የሕይወት ለውጥ ያገኙትና ነገሩን በትክክል የተረዱት እራሳቸውን የሚቆጥሩት ሃይማኖታቸውን እንደ ለወጡ አድርገው ሳይሆን ቀድሞ ስመ - ክርስቲያን እንደነበሩና አሁን ግን በእውነት ክርስቲያን እንደሆኑ አድርገው ነው። "ስመ-ክርስቲያን" ማለት በአጭሩ እራሱን ክርስቲያን እንደሆነ አድርጎ የሚቆጥር፣ ምናልባት ሌሎችም ክርስቲያን እንደሆነ አድርገው የሚቆጥሩት፤ ሕይወቱና አድራጎቱ ግን የክርስቲያን ያይደለ ሰው ማለት ነው። እንዲህ ዓይነቱ ሰው ወንጌላውያን ባልሆኑ

አብያተ ክርስቲያን ውስጥ ብቻ ሳይሆን በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያንም ውስጥ ይገኛል። እንዲህ ዓይነቱ ሰው ዳግም ያልተወለደ ብቻ ሳይሆን የዳግም ልደት ልምምድ ያለውም ሰው ሞምር ሊሆን ይችላል። "ስመ-ክርስቲያን" የሚለውን ቃሉን ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀመበት ጌታ ኢየሱስ እራሱ ነው። ይህንንም ያደረገው ወደ ሰማይ ከዓረገ ከስድሳ አመታት ገደማ በኋላ ለሰርዴስ ቤተ ክርስቲያን በላከላት ደብዳቤ ውስጥ ነው (ራእ 3:1-6)።

የሰርዴስ ቤተ ክርስቲያን "ስም ያላት" ነገር ግን "የሞተች" ቤተ ክርስቲያን ነበረች። "ስመ ክርስቲያን" ወይም "ስመ ቤተ ክርስቲያን" ነበረች ማለት ነው። ይህም ማለት ከምዕመናንዋ መካከል አብዛኞቹ ሕይወታቸውና ተግባራቸው የክርስቲያን አልነበረም ማለት ነው። እንዴት ነው ሰዎቹ ክርስቲያን ነን እያሉ ሕይወታቸውና ተግባራቸው ግን የክርስቲያን ያልነበረው? መቸም ቢሆን ተግባር ሕይወትን ነው የሚከተለው። ዛፍ በፍሬዋ ትታወቃለች (ማቴ 12:33)። ስለዚህ ሰዎቹ ክርስቲያን ነን እያሉ ተግባራቸው ግን የክርስቲያን ካይደለ አንደኛውና ዋኛው ምክንያት ክርስቲያን ስላልነበሩ ነው የሚሆነው።

ሰዎቹ ክርስቲያን ነን እያሉ እንዴት ክርስቲያን ላይሆኑ ይችላሉ? ክርስቲያን ለመሆን ሰው ማድረግ ያለበትን ነገር ካላደረጉ "ክርስቲያን ነን" ስላሉ ብቻ ሰዎች ክርስቲያን አይሆኑም። ክርስትና በደም አይተላለፍም። ወይም እንደ ንብረት ከወላጆች አይወረስም። ወይም "ኖን" በማለት ብቻ አይኮንም። ሰው ክርስቲያን የሚሆነው ዳግመኛ በመወለድ ነው (ዮሐ 3:3)። ዳግም መወለድ የሚቻለውም ኢየሱስን በመቀበልና በስሙ በማመን ነው (ዮሐ 1: 12-13)። ይህም የሚፈፀመው በወል ሳይሆን በነፍስ ወከፍ ነው።

የሰርዴስ ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን በሙሉ ዳግም ያልተወለዱ አልነበሩም። ልብሳቸውን ያላረከሱ "ጥቂት ሰዎች" በሰርዴስ ነበሩ። ልብሳቸውን ያላረከሱ ማለት ምን ማለት ነው? የመጽሐፍ ቅዱስ ዋና ተርጓሚ መጽሐፍ ቅዱስ እራሱ ነው ይባላል። በራእይ መጽሐፍ ውስጥ ". . . በደሙም ከኃጢኣታችን ለዋጀን" የሚል ቃል እናነባለን (1:5)። እንደገና ደግሞ ". . .ልብሳቸውንም በበጉ ደም አጥበው ነጭ አድርገውታል" ይላል (7:14)። ልብስ የሰው ሕይወት ምሳሌ መሆኑ ነው። የሰውንም ሕይወት የሚያቆሽሸው ኃጢአት ሲሆን፣ የሚያነፃው ደግሞ የበጉ ማለትም የኢየሱስ ደም መሆኑ ነው። በሰርዴስ ልብሳቸውን በኢየሱስ ደም አጥበው ነጭ ያደረጉ ጥቂት ሰዎች ነበሩ። እነዚህን ስም እያላቸው ነገር ግን ሞተዋል ከተባሉት ጋር አልደመራቸውም።

ለሰርዴስ ቤተ ክርስቲያን በላከላት ደብዳቤ ውስጥ ጌታ እራሱን ያስተዋወቀው "ሰባቱን የእግዚአብሔር መንፈሶችና ሰባቱን ኮከቦች የያዘው" በማለት ነው። የሰባቱ ኮከቦች ፍቺ በመጽሐፉ የመጀመሪያ ምዕራፍ የመጨረሻ ቁጥር ላይ ተሰጥቷል። ጌታ የሰርዴስን ቤተ ክርስቲያን በአንድ በኩል የሞትሽ ነሽ እያላት በሌላ በኩል ደግሞ በመካከልዋ እየተመላለሰ፣ መልአኳንም (መሪዋን?) በቀኝ እጁ እንደ ያዘ መሆኑ ያስገርማል። ስለ ክርስቲያን አይደለንም የምንል ሁሉ ስለ ራሳችን በትህትና እንድናስብ፣ ስለ ክርስቲያን ናቸው ስለምንላቸውም ሁሉ ተስፋ እንዳንቆርጥ ያደርገናል።

በጌታም እጅ ውስጥ ሰባቱ ኮከቦች ብቻ አይደሉም ያሉት። ሰባቱ የእግዚአብሔር መንፈሶችም ጭምር ናቸው እንጂ። ይህም በወደደ ጊዜ ሁሉ ለሞቱት ሕይወትን ለመስጠት በእጁ እንደሆነ ያሳየናል። ሕይወትን የሚሰጥ የእግዚአብሔር መንፈስ ነውና (ዮሐ 6፡33)።

በቤተ ክርስቲያን ዘመናት ቅደም ተከተል መሠረት[1] የሰርዴስን ቤተ ክርስቲያን የምትከተለው የፊላደልፍያ ቤተ ክርስቲያን ናት (ራእ 3፡7-13)። የፊላደልፍያ ቤተ ክርስቲያን ጌታ ደብዳቤ ከላከላቸው ሰባት አብያተ ክርስቲያን መካከል ምንም ዓይነት ነቀፋ ካልተነገረባቸው ከሁለቱ አንድዋ ናት። የፊላደልፍያ ቤተ ክርስቲያን ማንም ሊዘጋው የማይችለው የወንጌል በር በጌታ የተከፈተላት ነች። በሰርዴስ ስለ መሞት ከተነገረን በፊላደልፍያ ለመስማት የምንጠብቀው ስለ መቀበር ነው። የሚነገረን ግን በተቃራኒው እጅግ ስለምትነቃቃና ለወንጌልም በር በጌታ ስለ ተከፈተላት ቤተ ክርስቲያን ነው። በዘመናት ቅደም ተከተል የፊላደልፍያ ቤተ ክርስቲያን የምትከተለው የሰርዴስን ቤተ ክርስቲያን ከሆነ አባላትዋ ከየት መጡ?

ያለጥርጥር በሰርዴስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተሐድሶና ሪቫይቫል ሆኖአል ማለት ነው። ከሆነውም ተሐድሶና ሪቫይቫል የተነሳ ከሙታንም መካከል ብዙዎች ነፍስ ዘርተዋል ማለት ነው። የፊላደልፍያ ቤተ ክርስቲያን ከአስራ ስምንተኛው ምዕት አመት አጋማሽ ገደማ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ያለውን የቤተ ክርስቲያን ዘመን ነው የምትወክለው። ይህችም ቤተ ክርስቲያን ላለፉት ሁለት መቶ ሃምሳ አመታት በተራማጅ ተሐድሶና በተከታታይ ሪቫይቫል ውስጥ እያለፈች ያለችው ናት።

ሚስዮናዊ ሚና

ወደ ኢትዮጵያ ለመግባት የመጀመሪያው ፕሮቴስታንት ሚስዮናዊ ሉተራዊው ፒተር ሄይሊንግ እንደሆነ ነው ታሪክ ጸሐፊዎች ሁሉ

የተስማሙበት። ዘመኑ 1634 ሲሆን "የዘመናችው የሚስዮን እንቅስቃሴ አባት" (the father of modern missions) እየተባለ የሚጠራው ዊልያም ኬሪይ ከእንግሊዝ ወደ ህንድ ያደረገውን የሚስዮን ጉዞ በአንድ መቶ ስድሳ አመታት ይቀድመዋል። በፒተር ሄይሊንግ እና ከእርሱ በመቀጠል በሁለተኛ ተራ ወደ ኢትዮጵያ በገቡት ፕሮቴስታንት ሚስዮናውያን መካከል የአንድ መቶ ዘጠና ስድስት አመታት ርቀት አለ።

ከዚያ ጊዜ ጀምሮ በመጀመሪያ በአውሮፓ፣ ከዚያም ቀጥሎ በሰሜን አሜሪካ ከሚገኙ የተለያዩ የፕሮቴስታንት ሚስዮን ድርጅቶች የተላኩ ሚስዮናውያን በሰሜን፣ በደቡብ፣ በምሥራቅና በምዕራብ የአገሪቱ ድንበሮች በኩል ወደ ኢትዮጵያ ለመግባት ሙከራ አድርገዋል። ከእነዚህም አንዳንዶቹ በሙከራ ላይ እንዳሉ ሕይወታቸው በበሽታ ወይም በአደጋ አልፎአል። አንዳንዶቹ ታምመው ወይም ተስፋ ቆርጠው ወደ መጡበት ተመልሰዋል። አንዳንዶቹም ተሳክቶላቸው የኢትዮጵያን ድንበር አቋርጠው ወደ መሐል ገብተዋል።

ይህ ሁኔታ ፋሺስት ኢጣልያ ኢትዮጵያን እስከ ወረረችበት እስከ 1936 ድረስ ለአንድ መቶ ስድስት አመታት ያህል ያለማቋረጥ ቀጥሎ ሳለ በኢጣሊያ ወረራ ወቅት ተሳክቶላቸው ወደ መሐል አገር ዘልቀው ገብተው የነበሩትም ሁሉ ሳይቀሩ አገሪቱን ለቅቀው እንዲወጡ ግድ ሆኖባቸዋል። የሚስዮን ድርጅቶች ወደ ኢትዮጵያ ለመግባትና ለመሥራት የሚችሉበት ሁኔታ ለመጀመሪያ ጊዜ በህግ ተደንግጎ የወጣው ነሐሴ 21 ቀን 1936 ዓ.ም. ነው።

በዚያ ድንጋጌ መሠረት ወደ ኢትዮጵያ ከገቡት መካከል ሁለት ጳንጠቆስጤአዊያን የሚስዮን ድርጅቶች ይገኛሉ። እነርሱም የፌንላንድ ጳንጠቆስጤአዊ ሚስዮንና የስዊድን ፊላደልፍያ ቤተ ክርስቲያን ሚስዮን በመባል ይታወቃሉ። የመጀመሪያው በ1954 በወልመራ፣ ከዚያም በ1955 በአዲስ አበባ፣ ሁለተኛው ደግሞ በ1960 በአዋሳ ሥራቸውን ጀመሩ። እነዚህ ሁለት የሚስዮን ድርጅቶች ጳንጠቆስጤአዊው ሪቫይቫል ወደ ኢትዮጵያ እንዲደርስ፤ ከደረሰም በኋላ ሥር እንዲሰድድ፣ ግንባር ቀደም አስተዋፅኦ አድርገዋል።

ከአስተዋፅኦዎቻቸው መካከል የመጀመሪያውና በጊዜው ለነበሩት ሁለት የፌንላንድ ጳንጠቆስጤአዊ ሚስዮን ሚስዮናውያት ሊቆጠርላቸው የሚገባው በስብከታቸው ወደ ጌታ ያመጡአቸውንና አብረዋቸው የነበሩትን ኢትዮጵያውያን ወጣቶች ስለ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀትና ከዚያም ጋር ስለ ተያያዙ ጳንጠቆስጤአዊ ልምምዶች መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያደረጉት አስተዋጽኦ ነው። ይህንን ግንዛቤ በወጣቶቹ ውስጥ ለመፍጠርና ለማዳበር ሚስዮናውያኑ የተጠቀሙበት

ዘዴ በአሜሪካ፣ በአውሮፓና እንዲሁም በሌሎች አገሮች ስለ ተከሰቱ ጰንጠቆስጤአዊ ሪቫይቫሎች የተጻፉ መጻህፍትና መጽሔቶች ወደ አገር ውስጥ በገፍ ማስገባትና ወጣቶቹ እንዲያነብቡአቸው ማደፋፈር ነበር።

ወጣቶቹ በንባባቸው ስለ ደረሱበት የመንፈስ ቅዱስ ሥራ እየተደነቁ፣ እነርሱንም ጌታ እንደዚያ ወደ አለ የሕይወትና የአገልግሎት ልምምድ እንዲያደርሳቸው እየናፈቁ፤ ውስጣቸው እየተቀጣጠለ፣ ልባቸውም እየተቻኮለ ሄደ። ዳሩ ግን ጌታ የመጀመሪያዎቹን ደቀ መዛሙርት "ከላይ ኃይልን እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ" እንዳላቸው (ሉቃ 24፡49) እነዚህም ወጣቶች ሚስዮኑ መርካቶ መካከል ቦታ ከራየው ቤት ውስጥ እየተሰበሰቡ፣ መጽሐፍ ቅዱሳቸውን እያጠኑ፣ ጌታም በመንፈስ ቅዱስ እንዲያጠምቃቸው እየፆሙና እየጸለዩ ቆዩ።

የቆይታቸው ጊዜ ግን እንደ መጀመሪያዎቹ ደቀ መዛሙርት አስር ቀናት ብቻ አልነበረም። ማን ለምን ያህል ጊዜ እንደቆየ በትክክል ባይታወቅም፣ በመካከላቸው ለብዙ ወራት የቆዩ እንደማይጠፉ ይገመታል። እየጸለዩ እንዲቆዩ የሚመክሩአቸው በጊዜው የነበሩት ሁለት ሴቶች ሚስዮናዊያት ሲሆኑ፣ የቆይታውን ጊዜ እራሳቸው ለወጣቶቹ በመጸለይ፣ ወይም ደግሞ ሌላ ሰው እንዲጸልይላቸው ሁኔታዎችን በማመቻቸት፣ ወይም ደግሞ አንዱ ለአንዱ እንዲጸልይ በማደፋፈር ያላሳጠሩበትን ምክንያት በዚሁ ምዕራፍ ውስጥ ከጥቂት ገጾች በኋላ እጠቅሳለሁ። በኋላ ላይ ለአንዳንድ ወጣቶች ከሚስዮኑ መለየትና በዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች መካከል ከተነሳው ጰንጠቆስጤአዊ እንቅስቃሴ ጋር መቀላቀል አስተዋፅኦ ካደረጉት ምክንያቶች መካከል ይኸ ዋነኛው ነበር።

ሁለተኛውን አስተዋጽኦ ያበረከተው ሥራውን በአዋሳ የጀመረው የስዊድን ፊላደልፊያ ቤተ ክርስቲያን ሚስዮን ነው። ይህ ሚስዮን እንዴት ወደ ኢትዮጵያ እንደ መጣ ስትጽፍ ጉኒላ ናይበርግ አስካርሰን ከአልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪ መኮንን የ1924 የስዊድን ጉብኝት ነው የምትነሳው[2]። ራስ ተፈሪም በግለ ታሪካቸው ስቶክሆልም የገቡበት ቀን የጰራቅሊጦስ (የጰንጠቆስጤ) ቀን እንደነበረ፣ የኡፕሳላ ሊቀ ጳጳሳት ስለ በዓሉ በቤተ ክርስቲያን በሚደረገው የስብከትና የጸሎት ስብሰባ ላይ እንዲገኙ እንደ ጋበዙአቸው፣ እርሳቸውም ጥሪውን አክብረው እንደተገኙ፣ በዚያ ለተሰበሰበውም ህዝብ ንግግር እንዳደረጉ፣ በንግግራቸውም ውስጥ "በዓለም የሚኖሩ ክርስቲያኖች ሁሉ ምንም ባንዳንድ ትንንሽ ነገር ቢለያዩ መሠረታቸው አንድ ክርስቶስ መሆኑን የማያውቅ የለም . . . .ዛሬም በዚህ በትልቁ በዓለ ጰራቅሊጦስ ቀን ከስዊድን ህዝብ መተዋወቁ የሁለቱ መንግሥታት ወዳጅነት እየጸናና

እየሰፋ ለመሄዱ ዋና ምልክት ይሆናል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ" ማለታቸውን ጠቅሰዋል[3]።

ወደ ጉኒላ ስንመለስ ደግሞ ከዚያ ጊዜ አንስቶ የስዊድን ቤተ ክርስቲያን ለኢትዮጵያ ትጸልይ እንደነበረ . . .በ1936 (ኢትዮጵያ በኢጣሊያ የተወረረችበት አመት) ኤሎፍ ሑግሉንድ የተባለ ስዊድናዊ ለኢትዮጵያ እንዲጸልይ የተለየ ሸክም እንደ ተሰማው . . . እየጸለየም ሳለ በራእይ የኢትዮጵያን ካርታ፣ በካርታውም ላይ አንድ ጣት "ጅማ" የሚባልን ቦታ ሲያመለክተው እንዳየ ትናገራለች።

ኤሎፍ ከ1939 እስከ 1949 በላይቤሪያ የስዊድን ፊላደልፊያ ቤተ ክርስቲያን ሚስዮናዊ ነበር። ከዚያም በላይቤርያ የነበረበትን ኃላፊነት ለካርል ራምስትራንድ አስረክቦ ወደ አገሩ ተመለሰ። በ1950 ወደ ኢትዮጵያ እንዲልከው ለሚስዮኑ ያቀረበው ጥያቄ ሳይፈቀድለት ቀረ። ከአስር አመት በኋላ የሚስዮኑን ሥራ በአዋሳ የጀመሩት በላይቤርያ የሚስዮኑን አገልግሎት ከኤሎፍ የተረከቡት ካርል ራምስትራንድ ናቸው።

ካርልም በላይቤርያ ሳሉ በራእይ የዓለምን ካርታ እንዳዩ፣ በካርታውም ላይ ብርሃን ከላይቤርያ ተነስቶ ኢትዮጵያ ላይ ሲያርፍ እንደ ተመለከቱ አሜሪውተውት እንደነበረ መጋቢ ጌቱ አያሌው ያስታውሳል። ከዚያም ወደ አገራቸው ተመልሰው "ጌታ መንገዱን በሌላ ጥሪ እስኪከፍትልን ድረስ ለአራት አመት ቆየን" ይላሉ ሚስ ሩት ራምስትራንድ[4]። የተጠበቀውም ሌላ ጥሪ መጣ። ሲመጣም ብቻውን ሳይሆን ሁለት ሆኖ መጣ። ሁለቱም ተጨማሪ ማረጋገጫዎች የመጡት ለሩት ራምስትራንድ ነበር[5]።

ካርል የሚስዮኑን ጣቢያ መክፈት የፈለጉት ማስለ ከተማ (ባሌ ጠቅላይ ግዛት) ነበር። ሚስዮኑ ስራውን በማስለ ሳይሆን በአዋሳ እንዲጀምር ያግባቡት አንድ የኢትዮጵያ መንግሥት ባለ ሥልጣን ናቸው። ባለ ሥልጣኑም ይህንን ያደረጉት የሚስዮኑ በአዋሳ ሥራ መጀመር ገና በመቆርቆር ላይ ለነበረችው ከተማ ዕድገት ይረዳል ብለው ስላሰቡ ነው[6]። ይሁን እንጂ በዚያ ስፍራ በብዙ ኢትዮጵያውያን ወጣቶች ሕይወት ውስጥ እግዚአብሔር የሠራው ሥራ ዘመር ተብሎ ወደ ኋላ ሲስተዋል ሚስዮኑ ወደ ኢትዮጵያ የመጣው በጠራ መለኮታዊ ራእይ መሆኑ፣ በአዋሳም ሥራ የጀመረው በእግዚአብሔር ሉዓላዊ አሠራር መሆኑ አያጠያይቅም።

ሥራውን በአዋሳ የጀመረው የስዊድን ፊላደልፊያ ቤተ ክርስቲያን ሚስዮን ብዙም ጊዜ ሳያጠፋ ከ1962 ጀምሮ በየአመቱ በነሐሴ ወር በተከታታይ ለሦስት ሳምንታት የሚቆይ ኮንፈረንስ ማድረግ ጀመረ።

በዚያ ኮንፈረንስ እንዲካፈሉ ተማሪዎችን ከመላው ኢትዮጵያ ይጋብዛ
የግብኝው ዜና የሚሠራጨው ከሰው ወደ ሰው፣ በስሚ ስሚ ነው
ግብኝውን ተቀብለው ወደ አዋሳ ለሚመጡት ተማሪዎ
የትራንስፖርትና የምግብ ወጭአቸውን ሚስዮኑ በሙሉ ይሸፍናል
ሚስዮኑ ይህንን አሠራር እስከ 1973 ድረስ ለአስራ አንድ አመታ
የገፋበት ሲሆን፣ ከ1978 ጀምሮ ግን ለአንድ ሳምንት ቆይታ አርባ
ማስከፈል ጀምሮ ነበር።

ሚስዮኑ በሚያደርግላቸው እገዛ እየተደፋፈሩ በየአመቱ በነሐሴ ወ
ከአስራ አራቱም ጠቅላይ ግዛቶች[7] ብዙ ወጣቶች ወደ አዋሳ ከተ
ይጎርፉ ነበር። ያ ኮንፈረንስ ቤተ ክርስቲያኒቱ በኮሙኒስታዊ
መንግሥት እስከ ተዘጋችበት ጊዜ ድረስ ለሐያ አመታት ያ
ያለማቋረጥ ቀጥሏል። የአዙሳውን ጳንጠቆስጤአዊ ሪቫይቫል ወ
ኢትዮጵያ ለማስገባት እግዚአብሔር ከተጠቀመባቸው መንገዶች ዋነኛ
ያ ኮንፈረንስ ነበር። ለጳንጠቆስጤአዊው ሪቫይቫል በግለት መቀጠል
በትምህርትና በድርጅትም መጠናከር የአዋሳው ኮንፈረንስ ያደረገ
አስተዋጽኦ በብዙ ኢትዮጵያውያን ጳንጠቆስጤአውያን ዘንድ ሲዘከ
ይኖራል።

ሚስዮናዊው ሚና ከላይ በስም በተጠቀሱት ሁለት ጳንጠቆስጤአውያ
የሚሰዮን ድርጅቶች የተወሰነ አልነበረም። በሌላ ዓለማ በተዘጋጀ
እንደዚህ መጠነኛ በሆነች መጽሐፍ ውስጥ ሁሉንም መዘርዘ
አይቻልም እንጂ ብዙ የሚሰዮን ድርጅቶች፣ እነርሱም የመሠረቱአቸ
አብያተ ክርስቲያን እና ግለሰቦች እያወቁና ሳያውቁም፣ በቀጥታ
በተዘዋዋሪም፣ ብዙ አስተዋጽኦ አድርገዋል። ለምሳሌ በናዝሬ
አርቶዶክሳዊያኑ የአፄ ገላውዴዎስ ትምህርት ቤት ተማሪዎ
የሚሰበሰቡበትን "ቻፕል" የተከራየላቸው ሚኖናዊ ዶክተ
ሮሀረር ኤሽልማን ነበር። ያንንም ያደረገው አርቶዶክሳውያኑ ወ
ሚስዮናውያኑ ሰፈር ለመምጣት ፈቃደኞች እንደማይሆኑ ስለወቀ
በጊዜው በትምህርት ቤቱ በመማር ላይ የነበሩት ጥቂት ጌታን ያመ
አርቶዶክሶች ባልንጀሮቻቸውን በወንጌል ለመድረሻ እንዲገለገሉበ
በማሰብ ነበር።

የኤስ.አይ.ኤም. ሚስዮን በአዲስ አበባ ከተማ በአራት ኪሎ አካባ
የወጣቶች ማዕከል ነበረው። በአካባቢው በነበሩት ኮሌጆችና የሁለተ
ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለሚማሩት ተማሪዎች ወንጌልን በማድረስ
በመንፈሳዊ ሕይወታቸውም እንዲያድጉ በመርዳት ያ ማዕከል ከፍተ
አስተዋጽኦ አድርጓል። በዚያን ጊዜ በማዕከሉ ከተገለገሉት ወጣቶ
ብዙዎቹ የማዕከሉ ኃላፊዎች የነበሩትን ሚስዮናውያን፣ በተለይም ደግ
አልበርት ማንስኪን በባለውለታነቱ ያስታውሱታል።

ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ ኢየሱስ የኮሌጅ ትምህርታቸውን
ለመከታተል ወደ አዲስ አበባ የሚመጡ ተማሪዎች ከቤተሰብ እይታ
ርቀው ባሉበት በአጓጉል ልማዶች ተጠምደው ትምህርታቸውን
መከታተል ወደማይችሉበት ሁኔታ ውስጥ እንዳይገቡ በማሰብ በመጠነኛ
ወርሐዊ ኪራይ፣ በጸጥተኛና በመንፈሳዊ ከባቢ አየር (atmosphere)
ውስጥ እንዲኖሩበት ያሠራችው ሆስቴል ከ1959 ዓ.ም. ጀምሮ
በአምስት ኪሎ እንደነበራት ይታወሳል[8]። በአንዳንድ የጠቅላይ ግዛት
ከተሞችም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ለመቀጠል ከየአውራጃው
ለሚመጡ ተማሪዎች በተመሳሳይ ዓላማ የተሠሩ የወጣቶች ሆስቴሎች
ነበሩአት። እነዚህ ሆስቴሎች ለብዙ ወጣቶች በወንጌል መደረስ፣
በጳንጠቆስጤአዊውም እሳት መለኮስ ትልቅ አስተዋጽኦ አበርክተዋል።

ስረ መሠረቱ ከሚኖናይት ሚስዮን ጋር የተሳሰረው አንጋፋው ሚልዮን
በለጠ በመንግሥት ሥራ በተዘዋወረባቸው በባህር ዳር የመኖርያ ቤቱ፣
በመቀሌ ደግሞ ለዚሁ ጉዳይ ቦታ ተመርቶ የሠራው ቤት በተጠቀሱት
ከተሞች የነበሩት ጥቂት ወጣት ክርስቲያኖች የጳንጠቆስጤን ልምምድ
በሕይወታቸው ለመጀመሪያ ጊዜ የቀሰሙባቸው ነበሩ።

ግርማዊአዊ ግርዶሽ

በሦስተኛው ምዕራፍ ውስጥ ስለ ተራማጁ ተሐድሶ ስናገር ተሐድሶው
የብዙ ነገሮች መስተጋብር ውጤት ነው ብዬ ነበር። ስለ ሪቫይቫልም
ይኸ እውነት ነው። በመስተጋብሩ ውስጥ የሚካፈሉት በቤተ ክርስቲያን
ውስጥ የሚከናወኑ ድርጊቶች ብቻ አይደሉም። ከቤተ ክርስቲያን ውጭ
የሚከናወኑ ድርጊቶችም ጭምር እንጂ። መንፈሳዊ ጉዳዮች ብቻም
አይደሉም። ፖለቲካዊ፣ ኤኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮችም ጭምር
እንጂ።

ንጉሡ ያዝያን ሲሞት ሄዜ ኢሳይያስ የእግዚአብሔርን ክብር እንዳያይ
በፊቱ ተጋርዶ የነበረው ግርማዊአዊ ግርዶሽ ተገፈፈለት (ኢሳ 6፡ 1-
5)። በኢትዮጵያም በታህሣሥ ወር 1953 ዓ.ም. የተሞከረው
መፈንቅለ መንግሥት ለኢትዮጵያ ወጣቶች ዓይን ከፋች ነበረ ቢባል
ማጋነን አይሆንም። አዎን፣ ወጣቶቹ እንደ ኢሳይያስ በዚያው አመት
የእግዚአብሔርን ክብር አላዩም። ቢሆንም ያ የመፈንቅለ መንግሥት
ሙከራ ብዙ ወጣቶች የእግዚአብሔርን ክብር እንዳያዩ በዓይናቸው
ላይ ተጋርዶ የነበረውን ፖለቲካዊ ብቻ ሳይሆን መንፈሳዊም ግርዶሽ
እንደ ገፈፈላቸው አስባለሁ።

ምንም እንኳን ንጉሡ ከዚያ በፊትም ተቀናቃኞች እንደ ነበሩአቸው
ቢታወቅም፣ ሁሉም ከሹክሹክታ ደረጃ ያለፉ አልነበሩም። የታህሣሡ

ግን በይፋ፣ በመንግሥታዊው መገናኛ ብዙሃን፣ ለድፍን የኢትዮጵ
ሕዝብ የተላለፈ ነበር። መፈንቅለ መንግሥቱ ከሽፏል። ንጉሡ
ከዚያ በኋላ ከአስራ ሦስት አመታት በላይ በዙፋናቸው ላይ ቆይተዋል
ሆኖም "ኃይለ ሥላሴ ይሙት!!"፣ "በኃይለ ሥላሴ!!" እያ
በንጉሡ ስም በሚምሉትና በሚገዘቱት ብዙ ወጣቶች ሕይወት ውስጥ
የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ስለ ብዙ ነገሮች የአመለካከት ለው
አስከትሉ አልፎአል።

ኮሙኒስታዊውና ጸንጠቆስጤአዊው ንቅናቄዎች በቀዳማዊ ኃይለ ሥላ
ዩኒቨርሲቲ የአራት ኪሎና የስድስት ኪሎ ካምፓሶች ውስጥ ጎን ለጎን
የጎሪጥ እየተያዩና አንድ አንዴም እየተገፋፉ መንቀሳቀስ ሲጀም
ከመፈንቅለ መንግሥቱ ሙከራ በኋላ ገና አምስት አመታት እንኳ
አላለፉም። መንትዮቹ ወንድማማቾች መንፈሳዊው ያዕቆብና ሥጋዊ
ኤሳው በእናታቸው በርብቃ ማህፀን ውስጥ ለዘጠኝ ወራት ሲገፋ
እንደነበሩ (ዘፍ 25፡ 21-26)፣ ሁለቱ ንቅናቄዎች በቀዳማዊ ኃይ
ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ለዘጠኝ አመታት እየተገፋፉ አደጉ። እን
ያኔው ሁሉ አሁንም አስቀድሞ የተወለደው የትኛው እንደሆ
እናውቃለን። ምድራዊውና ሥጋዊው ነበረ። አገሪቱ ግን በተስ
ቃል ተረከዙን ይዞ ለተወለደው ለሰማያዊውና ለመንፈሳዊው
ተሰጥታለች። ተፈጥሮአዊው ሁልጊዜ ቀደም ማለቱ መለኮታዊ መር
ይመስላል (1ኛ ቆሮ 15፡46)።

እናንተ ወጣቶች፣ ወደ እኔ ኑ!

"እናንተ ደካሞች . . ." የሚለውን ነው በ"እናንተ ወጣቶች
የተካሁት (ማቴ 11፡28)። ወጣቶች ደካሞች አይደሉም አላልኩም
ባይሆን ደካማነታቸው ላይ ገና አልደረሱበትም ነው የምለው።
ጸንጠቆስጤአዊው ሪቫይቫል ወደ ኢትዮጵያ ሲመጣ የመጀመሪ
ሚላማው ያደረገው ወጣቶችን ነበር። ጎልማሶችም ሪቫይቫሉ
ተቀላቅለዋል። ያ የሆነው ግን ትንሽ ቆይቶ ነው።
በጸንጠቆስጤአውያኑ ሰፈር በዕድሜ ጠና ያሉ ሰዎች እንደ ብር
የሚታዩበትን ጊዜ ከሪቫይቫሉ ፍንዳታ አስር አመታት በኋላ የመጣሁ
እኔም በአንዳንድ አካባቢዎች ደርሼበታለሁ።

ለመሆኑ እግዚአብሔር ለአንድ የተወሰነ የሕብረተሰብ ክፍል የተለ
ፕሮግራም ወይም የወንጌል ሥርጭት ስልት (ስትራቴጂ) ይኖረዋ
ወይ? አሳምሮ!! ጳውሎስንና ሲላስን ወደ እስያ እንዳይሄዱ
ሲከለክላቸውና ወደ አውሮፓ ሲመራቸው (የሐዋ 16፡ 6-10) መንፈ
ቅዱስ ምንድነው እያደረገ የነበረው? ፊልጶስን ከሞቀው የሰማርያ

ሪቫይቫል ውስጥ አውጥቶ ወደ አንድ ኢትዮጵያዊ ሲልከው (የሐዋ 8፡26-32) ምንድነው እያደረገ የነበረው? በ1920 ዓ.ም. ለወንጌል አገልግሎት ወደ ጅማ ለመሄድ ከአዲስ አበባ የተንቀሳቀሰው በዶክተር ቶማስ ላምቤ የሚመራው የሚሲዮናውያን ቡድን መንገድ ተሳስቶ ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ የሄደውና የወላይታ፣ የከምባታ፣ የሐዲያ፣ የሲዳማ፣ የጌዴኦ እና እንዲሁም ሌሎች የክልሉ ሕዝቦች ወንጌልን እንዲቀበሉ ምክንያት የሆነው በአጋጣሚ ነበር ወይስ በእግዚአብሔር ሉዓላዊ ዕቅድ?

ልዩነቱ ያኛው በአህጉር፣ በአገርና በብሔረሰብ ሲሆን ይኸኛው ግን በዕድሜ የመሆኑ ጉዳይ ብቻ ነው። ያስ ቢሆን የእግዚአብሔር አሠራር አይደለም ለማለት ማን ይደፍራል? "እነሆ ታላቁና የሚያስፈራው የእግዚአብሔር ቀን ሳይመጣ ኤልያስን እልክላችኋለሁ። መጥቼም ምድርን በእርግማን እንዳልመታ እርሱ የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች፣ የልጆችንም ልብ ወደ አባቶች ይመልሳል" (ሚል 4፡ 5-6) የሚለውን የትንቢት ቃል እግዚአብሔር የሚፈጽመው አንድ ጊዜ ብቻ አይደለም። በተከታታይ ትውልዶች መካከል ብዙ ጊዜ የሚፈጠረውን የልብ መራራቅ (generation gap) እግዚአብሔር የሚያጠበው በኤልያስ መንፈስ ነው ማለት ነው። የኤልያስም መንፈስ የሪቫይቫል መንፈስ ነው። ይህም በኤልያስ በራሱ ዘመን የታየ ሲሆን (1ኛ ነገ 18፡ 41-46)፣ ከዚያ በኋላ ስምንት መቶ ሃምሳ አመታት ቆይቶ ደግሞ በኤልያስ መንፈስ እንደ ተነሳ መጽሐፍ ቅዱስ እራሱ በሚመሰክርለት በመጥምቁ ዮሐንስ ዘመን ታይቷል (ማቴ 11፡ 12-15)።

አሁን ነገሩ ካለፈ በኋላ ወደ ኋላ መለስ ብለን ስናስተውለው እግዚአብሔር በዚያ ሪቫይቫል ወጣቶችን ሚላማ ያደረገበትን የአጭርና የረዥም ጊዜ ምክንያቶች መረዳት የምንችል ይመስለኛል። የመጀመሪያው መቸም እሩቡን ከጥፋት ለማዳን ነው። አንድን ትውልድ እምሽክ ሊያደርግ ያለ ታላቅ አደጋ በአገሪቱ ወጣቶች ላይ በዚያን ጊዜ እያንጎበጎበ ነበርና። ያም አደጋ በጊዜው ከእግዚአብሔር በቀር ለሌላ ለማንም የሚታይ አልነበረም።

ከዚህ በተረፈ ግን አዲስ ነገር መቀበልና መለማመድ፣ ከአዲስ ነገር ጋር አብሮ መንጎድ ለወጣቶች የወላጆቻቸውን ያህል አይከብድባቸውም። የጸንጠቆስጤ ልምምድ "ምራቁን የዋጠ" ሰው በዋዛ የሚቀበለው ዓይነት አይደለም። ወጣቶች ያመኑትን ነገር በብጤዎቻቸው መካከል ማዛመትም ሆነ ያ ሊያስከትልባቸው የሚችለውን ትችትና ነቀፋ መሸከም ከወላጆቻቸው ይልቅ ይቀላቸዋል። እነዚህ ባህርያዊ የሆኑ ምክንያቶች ቢሆኑም፣ ለአጭርና ለረዥም ጊዜዎቹ ምክንያቶች ተፈፃሚነት በጣም የሚጠቅሙ ነበሩ።

ከአሜርና ከረዥም ጊዜ ምክንያቶች መካከል የሚከተሉት ሊጠቀ
ይችላሉ። በዘጠኝ አመታት ጊዜ ውስጥ መደብ የለሹን ብቻ ሳይ
እግዚአብሔር የለሹንም ሥርዓት በዓለም ሁሉ የመፍጠር ተል
ያነገበው ማርክሳዊ ሌኒናዊ ርዕዮተ ዓለም በኢትዮጵያ የመንግሥ
መመሪያ ሊሆን ነው። በገጠርና በከተማ፣ በደጋና በቆላ፣ እንዲያ
በምድሪቱ ሁላ፣ ሰዋች የተጨበጡ የግራ እጆቻቸውን ወደ ሰማ
እያወናጨፉ "እናወድማለን!" "እናሸንፋለን!" እያሉ ሲደነፉ ነው
እንደዚህ ለማለት ሀሊናቸው የማይፈቅድላቸው ሁሉ "የኤምፐርያሊስ
ቡችሎች!" "ፀረ አብዮተኞች!" እየተባሉ ሊንጓጠጡና ሊደፈጠ
ነው። "እንዴት አደራችሁ?" ሲባል "እግዚአብሔር ይመስገን" ብ
መመለስ ወደ ማይፈለግበት ብቻ ሳይሆን ወደ ሚያስፈራበትና ወ
ሚያሳፍርበት ዘመን ሊዘቀጥ ነው።

ያ ርዕዮተ ዓለም ፍላጎቱና ጥረቱ ሰውን ሁሉ በተለይም የነገ
ህብረተሰብ ገንቢ የሆነውንና ቀለም የቀሰመውን ወጣት በዳያሌክቲ
ማቴርያሊዝም ለማስታጠቅ፣ በቁስ አካላዊነት ለማጥመቅ ነበር
እንደዚያ ባለ ጊዜ ከ"ሞያ በልብ ነው" ባለፈ እምነት በእግዚአብሔ
ለማመን፣ ከብዙኃኑም ተነጥሎ ለብቻ ለመቆም፣ መንፈስ የሆነ
እግዚአብሔር ከቁስ የበለጠ ተጨባጭ የሆነለት ሰው መሆን ያስፈል
ነበር። ጸንጠቆስጤአዊው ሪቫይቫል በብዙ አማኞች ወጣቶች ዘን
የፈጠረው ይህንን ተጨባጭነት ነበር። በጊዜው ከወጣትነት የዕድ
ክልል እየወጣ የነበረው ይህ ጸሐፊ ኦሪጅናሉን የክርስትና እም
እንዳገኘው እርግጠኛ የሆነው በ1968 ዓ.ም. መጀመሪያ ላይ አማኞ
በልሳኖች ሲናገሩ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲሰማና ያም የመጀመሪያ
ክርስቲያኖች ልምምድ ለመሆኑ አዲስ ኪዳናዊ ማስረጃ በተደረደረለ
ጊዜ እንደነበር አይዘነጋም።

እዚህ ላይ አንባቢውን እማጠናለሁ። ጸንጠቆስጤአዊው ልምም
ያልነበራቸው አማንያን በዚያ ጊዜ ክርስትናቸውን ተጨባጭ ሆ
አላገኙትም ማለቱ አይደለም። ወይም በዚያ የመከራ ዘመ
በእምነታቸው ጸንተው ያለፉት ጸንጠቆስጤአዊው ልምምድ የነበራቸ
ብቻ ነበሩ ማለቱም አይደለም። ከቶውንም ጸንጠቆስጤአዊው ልምም
ካልነበራቸው ምዕመናን ቁጥር ጋር ሲነፃጸር የዚያን ጊዜ
የጸንጠቆስጤአዊያን ቁጥር ጭብጥ የማይሞላ የሚባል ዓይነት እንደነ
አውቃለሁ። በመከራው ውስጥ በጸኑት ብቻ ሳይሆን ባልጸኑት
መካከል ሁለቱም ዓይነት አማንያን እንደነበሩም ደግሞ አውቃለሁ።

ልል የፈለግሁት እንደዚህ ነው። ከአብዮቱ ፍንዳታ በፊት የነበሩ
ጥቂት አመታት የወጣቶች በተለይም ደግሞ የተማሩ ወጣቶች ል
ከቤተ ክርስቲያን መሸፈት የጀመረባቸው አመታት ነበሩ። ቤ
ክርስቲያን ስል ወንጌላውያኑን አብያተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን

ወንጌላውያን ያልሆኑትንም ጭምር ነው። በተለይም የኢትዮጵያ
ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በሃምሳ ሦስቱ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ
ጊዜ፣ በይፋ ከመንግሥት ጎን በመቆም ወረቀት መበተንዋ፣
የግልበጣውን ሙከራ ያደረጉትንና የሚተባበሩዋቸውን ሁሉ
ማውገዝዋ፣ በተማረው ወጣት ዘንድ እንደ አንድ የኋሊት ጎታች ኃይል
መቆጠርንና መጠላትን አትርፎላት ነበር። አዝማሚያው ሲታይ
የአብያተ ክርስቲያን የወደፊት ዕጣ የአረጋውያን አምባ ከመሆን
እንደማያልፍ ይመስል ነበር።

ይህ ሳያንስ "በዕንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ" እንዲሉ አምላክ አልበቸነትን
በአደባባይ የሚያስተምር መንግሥት መጣ። ሰዎችም ሁሉ ትምህርቱን
እንዲቀበሉ የተለያዩ ማባበያዎችና ማስገደጃዎች ታከሉበት። እምነትንና
አማኞችን በሰዎች ሁሉ ዘንድ የተጠሉ ለማድረግ መሰሪነትን የተሞሉ
የተለያዩ ዘዴዎችም ተጨመሩበት። የዚህ ሁሉ ድምር ለብዙ ሰዎች
ክርስትናን ያረጀና ያፈጀ፣ በአንድ ትውልድ ዕድሜ ውስጥ
የማይቀረውን የተፈጥሮ ሞት የሚሞት አስመሰለው። ዘላለማዊው
እግዚአብሔር ግን በጸንጠቆስጤአዊው ሪቫይቫል አማካይነት ለጥንታዊው
ክርስትና ዛሬአዊነትን ሰጠው። በልሳን እንደ መናገር፣ አጋንንትን
እያስጮሁ እንደ ማስወጣት ባሉት ልምምዶቹ ለ"ተምኔታዊው" እምነት
ተጨባጭአዊነትን ቸረው። ይህንን ልል ነው የፈለግሁት።

ወጣቶች ከጎልማሶች ይልቅ ረዥም ዕድሜ ይኖራቸዋል። ብዙ የማየት፣
ብዙ የማወቅ፣ ብዙ የመለማመድ፣ ብዙም የማገልገል ዕድል አላቸው።
በወጣቶች የሚጀመር ሥራ ቀጣይነቱ (sustainability) አስተማማኝ
ነው።

ከዚህ በዓይን ከሚታየው ዓለም በስተጀርባ ሌላ መንፈሳዊ ዓለም አለ።
በሚታየው ዓለም ውስጥ ከሚሆኑት ነገሮች አንዳንዶቹ በመንፈሳዊው
ዓለም የሚፈፀሙ ነገሮች ነፀብራቅ ናቸው። ከዚህ አንፃር ሲታይ ከዚያ
ኢትዮጵያን ጨምሮ በብዙ አገሮች ላይ ከነፈሰው የማርክሲዝም ሌኒኒዝም
ርዕዮተ ዓለምና ካስከተለው ጥፋት በስተጀርባ ሰብዓዊ ያልሆኑ ኃይላት
አልነበሩም ማለት አይቻልም። እነዚህንም መንፈሳዊ ኃይላት ለመዋጋት
እግዚአብሔር በዚያ ሪቫይቫል አማካይነት መንፈሳዊ ሠራዊት ሊያስነሳ
ፈልጎ ቢሆን የሚያስገርም ነገር አይሆንም። የእግዚአብሔር መንፈሳዊ
ሠራዊት መላእክት ብቻ እንዳይደሉ፣ ይልቁንም አማኞች ሰዎችም
ጭምር እንደሆኑ ይታወቃልና (ኤፌ 6፡10-20)።

"አልቃሻዎች" የሚል የቅጽል ስም እስኪወጣላቸው ድረስ በአገሪቱ
ባሉት ጸንጠቆስጤአውያን ወጣቶች ሁሉ ላይ በወቅቱ ወድቆ የነበረውን
እጅግ አስደናቂ የሆነ የጸሎትና የምልጃ መንፈስ ከዚህ አንፃር ካላየነው
በስተቀር የተሟላ ትርጉም ልናገኝለት የምንችል አይመስለኝም።

ከመንፈስ ቅዱስ መሆኑ ፈጽሞ ስለማያጠያይቀው ስለዚያ እንባ ባይ
ኖሮ ያ ርዕዮተ ዓለም በኢትዮጵያና ምናልባት በሌሎችም አገሮች ሞ
ከቆየው ይልቅ የበለጠ ይቆይ ነበር ይሆን? በወደቀበትስ ጊዜ እንደ
የሰው እጅ ሳይነካው፣ በአንድ ጊዜ፣ እንደ እንቧይ ካብ ክርብትና
በማለት አይሆን ነበር ይሆን? ማን ያውቃል?

ከጥቂት አመታት በኋላ ብዙ ኢትዮጵያውያን በታሪካቸው ከዚያ በፊ
ተመሳሳይ በማይገኝለት ሁኔታ ወደ ዓለም ሁሉ ሊሰደዱ ነው። ብ
ልጆች ከወላጆቻቸው፣ ብዙ ወላጆችም ከልጆቻቸውና ከእርስ በራሳቸ
ተለያይተው፣ ቀያቸውንና አገራቸውን ትተው፣ እግራቸው
አደረሳቸው ወደ የትም ሊፈልሱ ነው። በሂደቱም ውስጥ እን
አይተውት፣ ሰምተውትም ለማያውቁት ጉስጉተ የስደት ሕይ
ሊጋለጡ ነው። "ከእኛ ወዲያ" የሚለውና ያልተፈተነው ኢትዮጵ
ዕጣቸው ሊፈርጥ ነው።

እነዚህን ሁሉ በየደረሱበት በእግዚአብሔር ፍቅር፣ በክርስቶስ ወን
የሚደርሳቸው ሠራዊት መዘጋጀት አለበት። ያም ሠራዊት ከሦ
አስቀድሞ ክርስትናን ከወላጆቹ የወረሰ ሳይሆን በግሉ የቀመሰ መ
አለበት። ቀጥሎም ወደፊት ሊያገለግላቸው ያሉት ሰዎች ሊያልፉ
ባለው ውጣ ውረድ ሁሉ ቀድሞአቸው ያለፈ መሆን አለበት። በዚህ
ሂደት ውስጥ የእግዚአብሔርን ጸጋ፣ የእግዚአብሔርን ሁሉን ቻይነ
የእግዚአብሔርን ታማኝነት በግሉ በተጨባጭ የተረዳ መሆን አለበት።

በኬንያ፣ በሱዳንና በጅቡቲ የስደት ካምፖች፤ በግብፅ፣ በደቡብ አፍሪ
በምዕራብና በምሥራቅ አውሮፓ አገሮች፣ በሰሜን አሜሪካ ከተሞች
በአውስትራሊያና በኒውዚላንድ፤ የእግዚአብሔርን ፍቅር ለወገኖቻቸ
ከሰበኩት ብዙዎቹ እንደዚያ ያሉ ወጣቶች ናቸው። በስብከታቸ
ከተማረኩትና እየተማረኩ ካሉትም ብዙዎቹ እንደዚህ ያሉ ሰ
ናቸው።

"ከናዝሬት መልካም ነገር ሊወጣ ይችላልን?"

ናዝሬት ከአዲስ አበባ በስተ ደቡባዊ ምሥራቅ አንድ መቶ ኪሎ ሜት
ርቀት ላይ የምትገኝ ከተማ ነች። በየትም አገር እንደሚሆነ
በኢትዮጵያም ከተሞች መንገድን ተከትለው ይከተማሉ። ወይ
መንገዶች ከተሞችን ተከትለው ይቀየሳሉ። በናዝሬት ሁለቱም እ
የሆነው። ናዝሬት መንገዶችን ተከትላ ተከትማለች። መንገዶች
ናዝሬትን ተከትለው ተቀይሰዋል።

ከጅቡቲ ተነስቶ ብዙ ከተሞችን እያቆላለፈና እያቆራረጠ ወደ ላይ ወደ
ደጋው እስከ አዲስ አበባ ድረስ የተዘረጋው የባቡር ሐዲድ በናዝሬት
ነው የሚያልፈው። ከአዲስ አበባ ተነስቶ ወደ ሐረር ወይም ወደ ቀይ
ባህር የሚጓዘው አውራ ጎዳና አዋሽ ላይ ለሁለት ከመከፈሉ በፊት
ናዝሬትን ለሁለት ከፍሏት ነው የሚያልፈው። ከአዲስ አበባ ወደ
አሰላ፣ ወደ ወንጂ፣ ወደ ሶደሬ፣ ለመድረስም ናዝሬትን መርገጥ የግድ
ነው።

በእነዚህ ምክንያቶች ናዝሬት ሞቅና ደመቅ ያለች ከተማ ነች።
የሾፌሮች፣ የኮንትሮባንዲስቶች፣ የወዝ አደሮች፣ የሴተኛ አዳሪዎች፣
እንዲያው ያላፊው ያግዳሚው ሁሉ መናኸሪያ ነች። የከተማ ሕይወት
በወጣቶች ላይ ለሚያሳድረው በጎ ያልሆነ ተጽዕኖ የናዝሬት ወጣቶች
ከብዙ የኢትዮጵያ ወጣቶች ይልቅ የተጋለጡ ናቸው። እንደ ሜት
መቃም፣ አልኮል መቀምቀም፣ ትምባሆ ማጨስ፣ መዝፈንና መደነስ፣
ያለው "ያራዳ ልጅ" መንፈስ የናዝሬትን ወጣቶች ገና በጧቱ ነው
የሚጠናወታቸው።

የኢትዮጵያዋ ናዝሬት በሰው እይታ እንደ ገሊላዋ ናዝሬት ሁሉ
"ከናዝሬት መልካም ነገር ሊወጣ ይችላልን?" ታስኛለች (ዮሐ 1:47)።
ዳሩ ግን ጎጢአት በበዛበት በዚያ መጠን ጸጋውን ይበልጥ
እንደሚያበዛው እንደ እግዚአብሔር ሆነና (ሮሜ 5:20)፣ በ1957
ዓ.ም. መግቢያ ላይ ጳንጠቆስጤአዊው ኑፋቄ በመጀመሪያ ከነፈሰባቸው
ከተሞች አንድዋ ናዝሬት ሆነች።

በኢትዮጵያ በአዙሳው ኑፋቄ ያልተቀሰቀሱ ካልኣቸው ኑፋቄያት መካከል
አንዱ ይኸ በናዝሬት የነፈሰው ኑፋቄ ነው። ኑፋቄ ከሚባል ይልቅ
አውሎ ነፋስ ቢባል ነው ወደ እውነቱ የሚጠጋው። በነገራችን ላይ ያ
ኑፋቄ ከነፈሰ ከሐያ አምስት አመታት በኋላ በናዝሬት ሌላ ኑፋቄ መንፈስ
ጀምሮአል። ይኸኛውም ኑፋቄ መንፈስ የጀመረው በቀጥታ
አርቶዶክሳውያኑ ሰፈር ውስጥ ነው። ከዚህኛው ኑፋቄ ጋር አብረው
በመንፈስ ላይ ያሉት ከሐያ አምስት አመታት በፊት እንደነዋው
ወጣቶች ብቻ ሳይሆኑ ጎልማሶችና አረጋውያንም ቁምር ናቸው።

ይኸኛው ኑፋቄ ከአውሎ ነፋስነት ይልቅ ለነፋስነት ይቀርባል።
አብረውት ነፉኞቹ እንደ ቀድሞው በመቶዎች ሳይሆኑ በሺዎች
ይቆጠራሉ። ሽውታውም እንደ ቀድሞው በወንጂና በወለንፌቲቱ ብቻ
ሳይሆን በሩቅ ባሉ ከተሞችም ይሰማል። ስሙን "አማኑኤል መንፈሳዊ
ማህበር" ይሉታል። ቁልስ "የሪቫይቫሉች ምድር" እንደ ተባለችው
የኛይቱም ናዝሬት "የሪቫይቫሉች ከተማ" ልትባል ይሆን?

ወደ 1957 ዓ.ም. ልመለስ። የአዬ ገላውዴዎስ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በሃይማኖተ አበው መንፈሳዊ ማህበራቸው[9] አማካይነት "ቻፕል" እያሉ በሚጠሩት ቤተ ውስጥ መንፈሳዊ ስብሰባ ማድረግ ይጀምራሉ። ጠዋት ጠዋት ወደ ክፍል ከመግባታቸው በፊት፣ ቀን ቀን አብዛኞቹ ምሳቸውን እየተው፣ ማታ ማታ ደግሞ ከክፍል በኋላ። ጥቂት እንደቆዩ በዕረፍት ጊዜአቸውና በሰውነት ማጠንከሪያ ክፍለ ጊዜ ሜምር። መጀመሪያ ላይ ጊዜውን ሁሉ የሚያሳልፉት በጸሉት ነበር። በኋላ ላይ ከመካከላቸው አንድ አንድ ከፍ ከፍ ያሉ ወጣቶች ከመጽሐፍ ቅዱስ አንድ አንድ ጥቅሦችን ወይም አንቀጾችን እያወጡ ሊያነቡ ጀመሩ። ሲያነቡም ብዙ ጊዜ እንባ እየተናነቃቸው፣ ሳግ እያቋረጣቸው ነበር።

በጸሉት ጊዜ እንደ መዝሙረ ዳዊት፣ ውዳሴ ማርያም፣ መልክዓ ማርያም ያሉትን በቤተ ክርስቲያናቸው የተለመዱትን የጸሉት መጻሕፍት አይደግሙም። እያንዳንዱ የየራሱን ጸሉት ይጸልያል። ሁሉም በቀጥታና በአንድ ጊዜ የየራሳቸውን ጸሉት ለእግዚአብሔር ይናገራሉ። እንዳንዴ የራሳቸው ኃጢአተኛነት እየታሰባቸው፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ የጌታ ሕማማት ትዝ እያላቸው፣ አንዳንዴም በማይገባቸው ምክንያት ተንሰቅስቀው ያለቅሳሉ። በየሳምንቱ ሰኞ፣ ረቡዕና ዓርብ ይፆማሉ። "ይፆማሉ" ማለት ወተትና ቅቤ ከመሳሰሉት እንደ መከልከል ካለው ከተለመደው ኦርቶዶክሳዊ ፆም በተጨማሪ ቁርስና ምሳ አይበሉም ማለት ነው።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ማክሰኞና ሐሙስ ማታ ማታ የመልዕክት ጊዜ እንዲኖራቸው አደረጉ። መልዕክቱን የሚያቀርቡት ከመካከላቸው በቅድሚያ የሚመደቡ ተማሪዎች ናቸው። መልዕክታቸው ስለ መላእክት ወይም ስለ ሰማዕታት ሳይሆን ስለ ጌታ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ነበር። ስለ በዓላት ወይም ስለ አጽዋማት ሳይሆን ስለ ኃጢአትና ለኃጢአትም ማስተስረያ ይሆን ዘንድ ስለ ተከፈለው ዋጋ ነበር። መልዕክት አቅራቢዎቹ መልዕክታቸውን የሚያቀርቡት እንደተለመደው ከድርሳናትና ከገድሎች ሳይሆን ከመጽሐፍ ቅዱስ ነበር። ብዙ ተማሪዎች በሚሰሙት በዚህ እያወቁ ባላወቁት አዲስ እውነት ልባቸው በኃይል እየተነካ እጃቸውን እያሉ ሕይታቸውን በፈቃዳቸው ለጌታ ለኢየሱስ ክርስቶስ ያስማርኩ ነበር።

ተማሪዎቹ እንዴት እንደዚህ ወዳለ ሁኔታ ውስጥ እንደገቡ በውል አያውቁትም። አስበውበትና አቅደውት ግን አልነበረም። ስለ እጅግመሩ የሚያውቁ ሁለትና ሦስት የሚሆኑ ቢኖሩም እነርሱም እንደዚህ ይሆናል ብለው አልመው ሳይሆን ቃኘተውም አያውቁም። ሃይማኖታቸውን እንዳልለወጡ ግን በጊዜው የትምህርት ቤቱ የሃይማኖተ አበው መንፈሳዊ ማህበር ፕሬዚዳንት የነበረውን ተማሪ ሰሎሞን ከበደን

ጨምሮ ሁሉም እርግጠኞች ናቸው። እየተማሩና እያስተማሩ ያሉት ኦርቶዶክሳዊ ትምህርት እንደሆነ፣ እንዲያውም እያደር መላው የናዝሬት ከተማ ህዝበ ክርስቲያን ፈለጋቸውን እንደሚከተል ነበር ተሰፋ የሚያደርጉት። ሲጀምሩ ሦስትና አራት የነበረው ቁጥራቸው ዕለት በዕለት እየጨመረ ሄዶ በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ ስምንት መቶ ገደማ መድረሱ ይህንን ተስፋቸውን የሚያጠናክር ሆኖ ነበር ያገኙት።

ሆኖም በመካከላቸው እየሆነ ያለውን ነገር ሙሉ በሙሉ "ሃይማኖተ አበውዋዊ" ነው ለማለት እንደማይቻልም ሳይገባቸው የቀረ አይመስልም። ለዚህም ሳይሆን አይቀርም ለራሳቸው "የሰማይ ብርሃን ጣቶች ማህበር" የሚል ሌላ ስያሜ የሰጡት። በማህበር ውስጥ ሌላ ማህበር ማለት ነው።

ያ ስብሰባ ለጀመሩትና እየመሩትም ላሉት ተማሪዎች ድንገት ግድቡን ነድሎ ባልተጠበቀ አቅጣጫ መፍሰስ እንደ ጀመረ የውሀ ሙላት ነበር የሆነባቸው። በየጊዜው እያደገ የሚመጣውን የተሳታፊዎች ቁጥር ባለ ሁለት ክፍል በሆነችው "ቻፕል" ውስጥ እንዴት እናስተናግዳለን? ከሚለው አንስቶ የጸሉቱን ስብሰባ አብረው በሚካፈሉት ወንዶችና ሴቶች ወጣቶች መካከል የሚፈጠረው መቀራረብ መንፈሳዊነቱን እንዳይለቅ እንዴት እንጠብቃለን? እስከሚለው ድረስ፤ ተማሪዎቹ በመንፈሳዊ ፕሮግራሞቹ መሳተፋቸውን ሳያቋርጡ ትምህርታቸውን ግን ሲሆን ሲሆን ከቀድሞው በተሻለ፣ አለበለዚያም ከቀድሞው ባላነሰ ትጋት እንዲከታተሉ እንዴት እናደርጋቸዋለን? ከሚለው አንስቶ፣ ያልተጠበቁና የማይታወቁ ሁኔታዎች ቢከሠቱ ምን እናደርጋለን? እስከሚለው ድረስ ያሉ ጥያቄዎች በቅድሚያ የታሰበባቸው አልነበሩም።

አዳዲስ ነገሮች በመካከላቸው በመጡ ጊዜ እንደ አመጣጣቸው በየዋህነትና በግልጽነት ይስተናገዳሉ። ችግሮችም በተከሰቱ ጊዜ በተረዱት መጠን በመንፈሳዊ መንገድ ሊፈቷቸው ይሞክራሉ። ስህተቶችም በተፈጠሩ ጊዜ ባልተለመደ ዓይነት ቅንነትና ትህትና ይታረማሉ። ተማሪዎቹ በጊዜው ከደረሱበት የዕድሜና የዕውቀት፣ የመንፈሳዊ ብስለትና የልምድ ደረጃ አኳያ ሲታይ ከዚህ የተሻለ እንዲያደርጉ አይጠበቅባቸውም። ሆኖም እነዚህ የእርምት እርምጃ ዎች ሁሉ የሚወሰዱት ነገሮች ከሆኑ በኋላ በመሆኑ ጉዳት እንዳይደርስ አስቀድሞ በመጠንቀቅ ረገድ የሚጠቅሙ አልነበሩም።

ለምሳሌ አንዳንድ ተማሪዎችን በውስጣቸው የሚኖሩ ርኩሳን መናፍስት ሊያስጮሁአቸው በጀመሩ ጊዜ የሆነው ነገር በትምህርት ሰሞኑ ሲጠቀስ የሚኖር ነው። ክስተቱ ርኩሳን መናፍስቱ ያለ ተቀናቃኝ፣ ተደላድለው በሚኖሩባቸው በእነዚያ ተማሪዎች ውስጥ ከእንግዲህ ወዲህ ሊኖሩ ያለመቻላቸው ምልክት ነበረ። የርኩሳን መናፍስቱ መንግሥት

የመናወጡ፣ ከእነርሱ የበረታ የመምጣቱና ምርኮአቸውን ሊያስጥላቸው የመፈለጉ ምልክት ነበረ።

ይሁን እንጂ ለተማሪዎቹ ይህ ፈጽሞ የማያውቁት እንግዳ ክስተት ነው የነበረው። ትምህርት የሚሰጣቸው ወይም ልምዱን የሚያጋራቸው ሌላ ማንም በአጠገባቸው አልነበረም። ስለዚህም በማህበራቸው ውስጥ የተፈጠረ ነገር መሆኑን ሳይገልጽላቸው ሰሎሞን ከበደ አባቱን በተዘዋዋሪ መንገድ የጠይቃቸዋል። እርሳቸውም በናዝሬት ከተማ ውስጥ የሚኖር አንድ የታወቀ "ዓዋቂ" ርኩሳን መናፍስትን እየገረፈ እንደሚያባርራቸው ይነግሩታል። እርሱም ከአባቱ የሰማውን ለባልንጀሮቹ ይናገራቸውና አጋንንት የሚያስጮሃቸውን መግረፍ ይጀመራል።

ይህ ዘዴ አልሠራ ሲል ሰሎሞን አሁንም አባቱን በሾርኒ እንደገና ይጠይቃቸዋል። እርሳቸውም የናዝሬቱ "ዓዋቂ" እራሱ በርኩሳን መናፍስት ኃይል የሚሠራ ስለሆነ የእርሱ አሠራር አምላካዊ ሊሆን እንደማይችል፣ ይልቁንም የወሊሶው አባ ወልደ ትንሳኤ ርኩሳን መናፍስትን የሚያወጡት ጠበል በመርጨት መሆኑን ያወጉታል። ተማሪዎቹ ይሽኛውንም ዘዴ ሞክረውታል። በአንድ ወቅት ርኩስ መንፈስ ሲለፈልፍ "ምሴ አተላ ስለሆነ ስጡኝና ለቅቄ እወጣለሁ" ስላለ አተላ ፍለጋ መንደር ለመንደር እንደዞሩ አበበች ዓለሙ አጫውታኛለች። እንዲህ እንዲህ እያሉ ነበር "በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ" የሚለውን የጌታን ቃል ወደ መረዳትና ወደ መለማመድ የደረሱት።

ሁኔታው በቅጡ ባይገባቸውና በጊዜው የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ወይም ጸንጠቆስጤአዊ ልምምድ ብለው ሊጠሩት ባይችሉም እንኳን ተማሪዎቹ በሚያካሄዷቸው ስብሰባዎች ውስጥ ሌሎችም ሁኔታዎች መታየት ጀመረው ነበር። ለምሳሌ በልሳን የሚናገሩ፣ ትንቢት የሚተነብዩ፣ ራእይ የሚታያቸው ወጣቶች በመካከላቸው ብቅ ብቅ ማለት ጀመረው ነበር። ሆኖም ከእውቀት እጦት ከመነጨ የአያያዝ ጉድለት የተነሳ ለሪቫይቫሉ ብርቱ አጋዥ ሊሆኑ የነበሩት እነዚህ ክስተቶች የሪቫይቫሉ ከባድ እንቅፋት የሆኑበትም ጊዜ ነበር።

ኬንያዊ ክብረት

የአዙሳው ጸንጠቆስጤአዊ ፍንዳታ ወደ ኢትዮጵያ ሲደርስ በመጀመሪያ ያስተጋባው አዋሳ ላይ እንደነበረ አንስቼአለሁ። በኢትዮጵያ ለተቀጣጠለው ጸንጠቆስጤአዊ እሳት ከፍተኛ ማገዶ ያበረከተችው የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን እንደነበረችም

ተናግሬአለሁ። ያንን ማገዶ ለማቀጣጠል እግዚአብሔር እንደ ክብረት የተጠቀመበት ሰው ደግሞ አማሂ ቻቻ ይባላል። በዜግነቱ ኬንያዊ ነው።

በጊዜው በኢትዮጵያ ካሉት ሁለት ጸንጠቆስጤአውያን የሚሲዮን ድርጅቶች ጋር ለነበሩት ኢትዮጵያውያን ጸንጠቆስጤአዊውን አስተምህሮ ከጸንጠቆስጤአዊው ልምምድ ጋር ያስታረቀላቸው ኬንያዊው አማሂ ቻቻ ነው። ይህንንም ያደረገው በአዋሳው የስዊድን ፊላደልፊያ ቤተ ክርስቲያን እና በመርካቶው የፊንላንድ ሚስዮን የተሰባሰቡ ኢትዮጵያውያን በመንፈስ ቅዱስ እንዲጠመቁ በጸለየላቸው ጊዜ፣ ከተጸለየላቸውም ብዙዎቹ ወዲያው በመንፈስ ቅዱስ ተጠምቀው በልሳኖች በተናገሩ ጊዜ ነው። ሁለቱ የሚሲዮን ድርጅቶች ጸንጠቆስጤአውያን ቢሆኑም እንኳን እስከዚያን ጊዜ ድረስ ጸንጠቆስጤአዊውን ልምምድ ለኢትዮጵያውያኑ አላካፈሉአቸውም ነበር።

ያላካፈሉባቸውን ምክንያቶች አሁን እናንሳቸው። የመጀመሪያው ፍርሃት ነው። የጸንጠቆስጤ ልምምድ ማለት የመንፈስ ቅዱስ እሳት በሰዎች ላይ መውረድ ማለት ነው። ይህ እሳት አንድ ጊዜ ከነደደ ማንም ሊቆጣጠረው እንደማይችል ያውቃሉ። ወዴት ሊዘልፍ፣ ወዴት ሊዛመት፤ ምን ሊሆን፣ ምንስ ሊከተል እንደሚችል በቅድሚያ መገመት በፍፁም አይቻልም። ያለ ጥርጥር እሳት ይኖራል። የመንፈስ ቅዱስ እሳት ብቻም አይደል የሚኖረው። የሥጋም እሳት ይኖራል። የነገር፣ የውዝግብ እሳት። የኢትዮጵያ መንግሥት ምን ይላል?

ቀድመዋቸው ወደ ኢትዮጵያ የገቡት የሚሲዮን ድርጅቶችስ ምን ይላሉ? በስዊድን ሉተራን ቤተ ክርስቲያንና በስዊድን ፊላደልፊያ ቤተ ክርስቲያን መካከል ቀደም ሲል (በቃል ነው አሉ) የተደረሰ ስምምነትም አለ። ሉተራኑ በኢትዮጵያ ጸንጠቆስጤአውያኑ በታንዛንያ ሊንቀሳቀሱ። አንዱ ወደ ሌላው ክልል እግራቸውን ላያነሱ። ኢሉፍ ሑግሉንድና ካርል ራምስትራንድ የሚሲዮኑን ሥራ በኢትዮጵያ ለመጀመር በተገለጠላቸው ራእይ ፊት ለፊት የተጋረጠው ደንቃራ ይህ እንደ ነበረ በኢትዮጵያ የሚሲዮኑ ኃላፊ የሆነው ገርት ፋለስቴን አጫውቶኛል።

የፊንላንድ ጸንጠቆስጤአዊ ሚስዮንም ተመሳሳይ ችግር ይኖርበት እንደሆነ አልታወቀም። በጸንጠቆስጤአዊነት ለመታወቅ ግን ብርቱ ፍርሃት እንደ ነበረበት ይታወቃል። በመርካቶው ጸሎት ቤት መጋቢ (ፓስተር) የነበረችው ሔልቪ ሔለን ሐልሜ ወደ ኢትዮጵያ መግባት የቻለችው በሚሲዮናዊነት ሳይሆን የልዑል ራስ አስራት ካሣ ልጆች አስተማሪ ሆና ነው። በጸንጠቆስጤአዊ ሚሲዮናዊነት ላለመታወቅ ብርቱ ጥንቃቄ

ታደርግ እንደነበረ ለአራት አመታት የአማርኛና የሲዳምኛ ቋንቋዎች አስተርጓሚዋ የነበረው ወንጌላዊ እንዳለ ገ/መስቀል አጫውቶኛል።

የምትጠቀምበት ማህተም እንኳን ሳይቀር የሚለው Scripture Mission እንደ ነበረ እንዳለ ያስታውሳል። በሲዳማ አውራጃ የገነትን ቤተ ክርስቲያን የመሠረተችው ይህች እህት ናት። በጸንጠቆስጤአዊነቷ ልትኮራ እንጂ ልታፍር እንደማይገባት ብዙ ጊዜ እንደ ሞገስ እንዳለ ያስታውሳል። ያኔ እርሱ የአዋሳው ሕይወት ብርሃን ቤተ ክርስቲያን ወንጌላዊ ነበር። እርሱም ችግርዋን ሊረዳላት፤ እርስዋም ልታስረዳው የሚችሉበት ሁኔታ ላይ አልነበሩም። ይህም ሁሉ ይባል እንጂ ሁለቱ የሚሰዮን ድርጅቶች እግዚአብሔር ሁኔታዎችን እንዲለውጥላቸው እየጸለዩ፣ የእርሱንም ጊዜ በናፍቆትና በትዕግሥት እየተጠባበቁ እንደ ነበር መገመት እንችላለን። ጸሎታቸው እንደ ተመለሰ ትዕግሥታቸውም እንደ ተካሰ እናውቃለን።

በሁለቱም የሚሰዮን ድርጅቶች ዘንድ፣ ማለትም በአዋሳም ሆነ በመርካቶ ይህንን ፈር ቀዳጅ የሆነ አገልግሎት ለመስጠት እግዚአብሔር የተጠቀመበት ሰው አማሄ ቻቻ መሆኑን ለማስተባበል የሞከረም ይሁን የሚሞክር ሚሰዮናዊም ሆነ ኢትዮጵያዊ እስካሁን አላጋጠመኝም። ይሁን እንጂ ይህንን መጽሐፍ ሳዘጋጅ ያጋጠመኝ ትልቁ ችግር አማሄ መጀመሪያ ወደ ኢትዮጵያ የመጣበትን ትክክለኛ ጊዜ ለማወቅ ያጋጠመኝ ችግር ነው። ቶርሞድ ኢንገልስቪክን "Molo Wongel: A Documentary Report on the Life and History of the Independent Pentecostal Movement in Ethiopia, 1960-1975" በሚለው መጽሐፉ፦

> ወንጌላዊው አማሄ ቻቻ ወደ ኢትዮጵያ የመጣው በ1963 ከኬንያ ነው። በዚያ አመት በአዋሳ በሚደረገው የበጋ የመጽሐፍ ቅዱስ ኮንፈረንስ ላይ ተናጋሪ እንዲሆን በስዊድን ፊላደልፊያ ሚሰዮን ተጋብዞ ነበር። ከኮንፈረንሱ በኋላ አዲስ አበባ መርካቶ በፊንላንድ ሚሰዮን ውስጥ የነበሩትን ጥቂት ወጣቶችንም ጎብኝቷል።

ይላል[10]። በፈረንጆቹ "1963 በጋ" በእኛ "1955 ክረምት" ማለት ነው።

አማሄ ቻቻ ለመጀመሪያ ወደ ኢትዮጵያ የመጣው በ1955 ዓ.ም. ክረምት ነው መባሉን የሚቃወሙ ኢትዮጵያውያን አጋጥመውኛል። ከሚቃወሙት መካከል በጊዜው በቦታው የነበሩትና ዛሬም የአዋሳ ሕይወት ብርሃን ቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች የሆኑት ወንጌላዊ ሚልኪያስ ቦረና እና አቶ አለማየሁ ጣሰው ይገኛሉ። እነዚህ አገልጋዮች አማሄ ካስተማረው ትምህርትና ከታየውም ልምምድ የተነሳ በወቅቱ ችግር ተፈጥሮ፣ የቤተ ክርስቲያኒቱም መሪዎች ለሁለት ተከፍለው እንደነበረ

ያስታውሳሉ። እነርሱም እራሳቸው የአማሄን ትምህርት ከተቃወሙት መካከል እንደነበሩ ይናገራሉ።

አማሄና ሌሎች ጥቂት ኢትዮጵያውያን በያምና በጸሎት ከቆዩ በኋላ፣ ነሐሴ 21 ቀን 1957 ዓ.ም. አማሄ ፈቃደኞች ለሆኑ ለአንዳንዶች ለመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት እንደ ጸለየላቸው፣ ያን ዕለት በመንፈስ ቅዱስ ተጠምቀው በልሳን ከተናገሩትም መካከል ወንጌላዊ ሚልኪያስና ወንጌላዊ ሻኛ እንደሚገኙ ይመሰክራሉ። አቶ ዓለማየሁ አማሄ ሁለተኛ ወደ ኢትዮጵያ በመጣ ጊዜ በ1958 ዓ.ም. በመንፈስ ቅዱስ እንደ ተጠመቀ ነው የሚናገረው።

እነዚህና ሌሎች የአዋሳ ሕይወት ብርሃን ቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች አማሄ ወደ ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ የመጣው በ1955 ዓ.ም. ላለመሆኑ የሚሰጡት ሌላም ምክንያት አላቸው። የስዊድን ፊላደልፍያ ሚሰዮን በአዋሳ ኮንፈረንስ ማድረግ የጀመረው በ1954 ዓ.ም. ነው። በተመሠረተ በሁለተኛ አመቱ ማለት ነው። በመጀመሪያዎቹ ሁለት አመታት የኮንፈረንሱ ተካፋዮች ቁጥር በጣም ትንሽ ነበር። ስለ ኮንፈረንሱ ወሬ እየሰሙ፣ ሰዎች ከሌሎች ከተሞች መምጣት የጀመሩት በ1956 ዓ.ም. እና ከዚያ በኋላ ነው። አማሄም በአዋሳው ኮንፈረንስ ላይ እንዲያገለግል ተጋብዞ የመጣው በነሐሴ ወር 1957 ዓ.ም. ነው። ያኔ ከአገር ውጭ የመጣ እርሱ ብቻ ነበር። በአመቱ ግን እርሱ ከኬንያ፣ ማትሰን ቦዚ ከአሜሪካ መጡ ይላሉ።

የእነዚህ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ቃል የዓይን ምስክሮች ቃል ነው። ወንጌላዊ ሚልኪያስ እንዲያውም ከረዥም ጊዜ ጀምሮ የየዕለት ሁኔታዎችን በማስታወሻ ደብተሩ ላይ እየጻፈ በመያዝ በዙሪያው ባሉ አገልጋዮች ሁሉ ዘንድ ይታወቃል። ስለ ሆነም ቃላቸው ክብደት ሊሰጠው ይገባል። አማሄ ወደ ኢትዮጵያ የመጣበትን የመጀመሪያ ጊዜ በተመለከተ ያጋጠመኝን ችግር ግን የእነዚህ የዓይን ምስክሮች ቃል አንዴ እና ለመጨረሻ ሊያስወግድልኝ አልቻለም። ሊያስወግድልኝ ያልቻለውም በአራት ምክንያቶች ነው።

አንደኛ ከላይ የተጠቀሰው የቶርሞድ ኢንገልስቪክን መጽሐፍ የምርምር ጽሑፍ ነው። ጸሐፊው የኖርዌጅያን ሉተራን ሚሰዮን ሚሰዮናዊ ሆኖ ከ1971 እስከ 1973 ድረስ በኢትዮጵያ ውስጥ በመካነ ኢየሱስ ሴሚናሪ የቲኦሎጂ መምህር ነበር። ለምርምር ጽሑፉ በምንጭነት የተጠቀመው ከጸንጠቆስጤአውያኑ መሪዎች፣ ከሌሎች ክርስቲያን መሪዎችና ሚሰዮናውያን ጋር በግንባር ያደረገውን ብዙ ሰዓቶች የፈጀ ቃለ ምልልስ እንደ ሆነ በመጽሐፉ መግቢያ ላይ ጠቅሷል። ጽሑፉን ያጠናቀቀው በአገስት 1975 እንደ ሆነም ይናገራል። እንደ እኔ ከነገሩ ከሰላሳ አምስት አመታት በላይ ርቆ ሳይሆን ወደ ነገሩ ከአስራ ሁለት አመታት

በታች ቀርቦ ነው የሚጽፈው። ስለ ሆነም የሚላቸው ነገሮች በቀላሉ የሚጣሉ ሆነው አላገኘሁአቸውም።

ሁለተኛ ከላይ ያነሳናት ጉኒላ ናይበርግ አስካርሰን በመጽሐፏ ውስጥ አማሄ ቻቻ ወደ ኢትዮጵያ የመጣው ሦስት ጊዜ ሲሆን የመጀመሪያው በ1963፣ ሁለተኛው በ1964፣ ሦስተኛው በ1966 እንደነበረ ታትታለች። ለመጀመሪያ በመጣ ጊዜ ከአሜሪካዊው ከማትሰን ቦዜ ጋር አብረው እንደነበሩም ትናገራለች። ሆኖም ሦስት ጊዜ መጣ መባሉን የማይስማሙበት ኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆኑ ስዊድናውያንም አጋጥመውኛል። በ1966 በጋ ላይ አማሄ ቻቻ እና ማትሰን ቦዜ በአዋሳ እንደ ነበሩ ግን ብዙዎች ይስማሙበታል። የሰነድ ማስረጃም አለ - በዚያ አመት በአዋሳ የሚሰጠውን የሦስት ሳምንታት ትምህርት ለተከታተሉ ወጣቶች በማትሰን፣ በአማሄና በካርል ፊርማ የተሰጠ የምስክር ወረቀት።

የቀሩትን ሁለት ምክንያቶች በዚሁ ምዕራፍ ውስጥ በሚቀጥሉት ሁለት ንዑሳን ርዕሶች ስር በየተራ አነሳቸዋለሁ። የአማሄ የአዋሳ አገልግሎት ብርቱ ችግር ያጋጠመው ቢሆንም እንኳን በጣም ስኬታማ ነበር። ስለ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የሚያስተምረውና የሚጸልየው ለሁሉ ሰው በአንድ ጊዜ አልነበረም። ስለ ነገሩ በደንብ ያልተረዱትንና ጥያቄ ያላቸውን በአንድ ከፍል ውስጥ ለብቻ አስቀምጦ ያስተምራቸዋል፣ ጥያቄአቸውን ይመልሳል። ጥቂት የተረዱትንና እንዲጸለይላቸው ፈቃደኛነት የሚያሳዩትን ሰብሰቦ በሌላ ከፍል ውስጥ ለብቻ ይጸልይላቸዋል። በአገልግሎቱ ብዙ ወጣቶች ሕይወታቸውን ለጌታ ሰጥተዋል። ብዙዎች ስለ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የነበራቸው ጥያቄ ተመልሶላቸዋል። ብዙዎች እጁን ሳይጭንባቸው እንኳን በመንፈስ ቅዱስ እየተጠመቁ በልሳኖች ተናግረዋል።

በአዋሳ የሆነው ነገር አዲስ አበባ መርካቶ በሚገኘው የፊንላንድ ሚስዮን ሰፈር ወዲያው ተሰማ። ሚስዮናውያኑ የምሥራቹን በስልክ ሳያበስሩአቸው አልቀሩም። አማሄም የአዋሳውን አገልግሎት እንዳጠናቀቀ የመርካቶዎቹን ወጣቶችም እንዲጎበኛቸው ተጠየቀ። ቀደም ሲል እንደ ተጠቀሰው የመርካቶዎቹ ወጣቶች ስለ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ያውቃሉ። ለረዥም ጊዜም የጸሉት ርዕሳቸው ሆኖ ቆይቷል። የማያውቁት በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ እንዴት እንደሚቻል ነበር። ይህንን እንደ ሰማይ የራቀባቸውን ነገር አማሄ አቀረበላቸው። እጅግ ከብዷቸው የነበረውን ነገር አማሄ እጅግ አቀለለላቸው።

የአማሄ ትምህርት በጣም ግልጽ፣ በጣም ቀላልና ማንም የሚረዳው ዓይነት ነበር። መጽሐፍ ቅዱሳዊና ገቢራዊም (practical) ነበር። ወጣቶቹ ከጎጢአታቸው በኢየሱስ ደም እንዲነጹ፣ መንፈስ ቅዱስን

እንዲጠሙ፣ ወደ አጥማቂውም ወደ ኢየሱስ በእምነት እንዲቀርቡና በቅዱስ መንፈሱ እንዲያጠምቃቸው እንዲጠይቁት ያደፋፍራቸዋል። ወጣቶቹ መንፈሳቸው ወዲያውኑ ይነሳሳል። ለተዘጋጁት እዚያው እጁን እየጫነ ይጸልይላቸዋል። አማሄ አዲስ አበባ በቆየባቸው የሁለት ሳምንታት ጊዜ ውስጥ በቁጥር አርባ የሚሆኑ ወጣቶች በመንፈስ ቅዱስ እየተጠመቁ በልሳኖች ተናግረዋል። አንዳንዶች ተንብየዋል። አንዳንዶች በሚተረጎሙ ልሳኖች ተናግረዋል። አንዳንዶች ተርጉመዋል። አንዳንዶች ጌታን በሙሉ ጊዜአቸው ለማገልገል ወስነዋል።

የአዙሳውን እሳት በኢትዮጵያም እንዲያቀጣጥል እግዚአብሔር የተጠቀመበት ሰው ኪንያዊው ኦማሄ ቻቻ ነው። እንደዚህ ማለት ግን ከአማሄ ቻቻ መምጣት በፊት በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቁ ኢትዮጵያውያን አልነበሩም ማለት አይደለም። ነበሩ። በፊንላንድ ሚስዮን ውስጥ (ምናልባትም በወልመራ) አንድ ሰው ነበረ። በአዋሳም አንድ ቀን፦

> ልጆች ከሚጸልዩበት ቤት ውስጥ አንድ የተለየ ድምጽ ተሰማ። ካርል ምንድነው ብለው ለማየት ሮጡ። ወጣቶች በሙሉ በወለል ላይ ወድቀዋል። እየጮሁ እግዚአብሔርን ያመሰግኑ ነበር። በአዲስ ቋንቋም ይናገሩ ነበር። የአስራ አንድ አመት ልጃችን ክርስቲናም እዚያ ነበረችና በልሳን እየተናገረች በእንግሊዝኛ ትንቢት ተናገረች። ሁኔታው ድንቅ ነበር። በዚያን ወቅት አምስት ወጣቶች በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ። አንዱ ደግሞ በስዊድንኛ ቋንቋ ትንቢት ይናገር ነበር። ይህም የመጀመሪያው የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ወቅት ነበር። የእኛም የመጀመሪያ ዙር የአዋሳ ቆይታ ዘመን አራት አመት በዚህ አይነት ተጠናቀቀ[11]።

ሩት የአዋሳ ቆይታቸውን በዙሮች ከፋፍለውታል። ወደ አዋሳ የመጡት በ1959 መጨረሻ ላይ ስለሆነ (በወርሐ ኖቬምበር) የመጀመሪያው ዙር የሚሉት የአራት አመታት ጊዜ 1963 መጨረሻ ላይ ይጠናቀቃል። ሁለተኛውም የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ወቅት የሆነው በዚሁ ዙር ውስጥ ይሆን? ከሆነ ከቶርሞድ ጋር ይስማማሉ።

ያላወቅነው ሌላው ነገር ሚስዮኑ እንዴትና ለምን አማሄ ቻቻን እንደ ጋበዘው ነው። ሚስዮኑ የስዊድን ፊላደልፍያ ቤተ ክርስቲያን የውጭ የወንጌል ስርጭት ክፍል ነው። የቤተ ክርስቲያኗ መስራች ታዋቂው ሌዊ ጴጥሮስ ነው። ሌዊ ጴጥሮስ ጰንጠቆስጤአዊውን ልምምድ ያገኘው ከኖርዊጅያኑ ከቶማስ ባራት ነው። ቶማስ ባራት ደግሞ ወደ ኣዙሳ ተጉዘው ልምምዱን በቀጥታ ከዚያ ከተቀበሉት ቀደምት ጰንጠቆስጤአውያን አንዱ ነው።

የስዊድን ፊላደልፍያ ቤተ ክርስቲያን እስከ ሐያኛው ምዕት አመ
አጋማሽ ድረስ በዓለም በትልቅነት የመጀመሪያውን ደረጃ የያዘች
ጰንጠቆስጤአዊት ቤተ ክርስቲያን ነበረች። በአገልግሎቷ ሁሉ በን
የሚሳተፉ 6500 አባላት ነበሩአት። በዕሑድ የጎልማሶች የሰንበ
ትምህርት ላይ ደግሞ 5000 ሰዎች ይካፈላሉ[12]። እንደዚህ ዓይነ
የሚስዮን ድርጅት ለኢትዮጵያ አገልግሎቱ ከንያዊ የጋበዘ
ለምንድነው? ስለ ጂኦግራፊያዊ ቅርበቱ ሲል ነው? ወይስ
ኢትዮጵያዊ ቀለሙ? ወይስ ስለ ጸጋ ስጦታው?

በሚስዮኑና አማሂ ቻቻን በላከችው የምስራቅ አፍሪቃ ጰንጠቆስጤአዊ
ቤተ ክርስቲያን (East African Pentecostal Church) መካከልስ ም
ዓይነት ግንኙነት ነበረ? ምናልባት ምንም ዓይነት ግንኙነት አልነበረ
ይሆናል። ግንኙነቱን የፈጠሩት ማትሰን ቦዜ ሳይሆኑ አልቀሩም
ጉኒላ በመጽሐፍዋ ውስጥ አማሂ ቻቻ በአንድ ወቅት የማትሰን ቦ
ተማሪ እንደነበረ ጠቅሳለች። ለመጀመሪያ ወደ ኢትዮጵያ በመጣም ጊ
አብረው ነበሩ ማለትዋ የሚዋጥልኝ ለዚህ ነው። በሚስዮኑ የኢትዮጵ
አገልግሎትና በደቀ መዝሙራቸው በቻቻ መሐከል ድልድይ ነ
የሆኑት ማለት ነው። ስለ ጂኦግራፊያዊ ቅርበቱ፣ ስለ ኢትዮጵያ
ቀለሙም፣ ስለ ጸጋ ስጦታውም ሲሉ።

ሐረር

በአዙሳው ኑሉስ ያልተቀሰቀሱ ሌሎች ጰንጠቆስጤአዊ ኑሳት በኢትዮጵ
መንፈሳቸውንና ከእነዚህም አንደኛው ከ1957 ዓ.ም. መጀመሪያ ጀም
በናዝሬት የነፈሰው መሆኑን በዚሁ ምዕራፍ ውስጥ ቀደም ሲ
ጠቅሻለሁ። ሌላው በሐረር መምህራን ማሰልጠኛ ተቅዋም ውስ
መንፈስ የጀመረው ነው።

የሐረር መምህራን ማሠልጠኛ ተቅዋም በአዲስ አበባና በጠቅላይ ግዛቶ
ከተሞች ውስጥ ባሉ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የዘጠነኛን ክፍ
ያጠናቀቁ ተማሪዎችን እየመለመለ ለሦስት አመታት በመምህርነት ሞ
ያሰለጥናል። በጊዜው በኢትዮጵያ ብቸኛውም ባይሆን እንኳን ታዋቂ
የመምህራን ማሠልጠኛ ተቅዋም ነበር።

በ1956 ዓ.ም. በዚያ ተቅዋም ከሚሰለጥኑት እጩ መምህራን ውስ
ወንጌላውያን ክርስቲያኖች የሆኑ ነበሩ። ከእነዚህ አንዱ የአዲስ አበባ
ጌታቸው ምክረ ሲሆን የተቀሩት በሙሉ የናዝሬት መጽሐፍ ቅዱ
አካዳሚ ልጆች ናቸው። ጌታቸው በመርካቶው የፊንላንድ ሚስዮ
ጌታን ያመልኩ ከነበሩት ወጣቶች መካከል አንዱ ነው።

ከአመቱ መጀመሪያ አንስቶ እነዚህ "መጽሐፍ ቅዱስ እናጥና
እየተባባሉ መገናኘት ይጀምራሉ። ባልንጀሮቻቸውንም ወደ ጥናታቸው

ይጋብዛሉ። በተደጋጋሚ ግብዣ ከተደረገላቸው አንዱ ዘለቀ ዓለሙ
ነው። ዘለቀ የናዝሬት ልጅ ሲሆን በዚያ አመት የአስራ አንደኛ ክፍል
ተማሪ ነበር። ዘለቀ አባቱ ቄስ የነበሩ፣ እርሱም በልጅነቱ ዲያቆን
የነበረ ቢሆንም በኋላ ላይ ግን ዓይነተኛ (typical) የሚባል "የናዝሬት
ልጅ" ወጥቶታል። ምናልባት ስለዚህ ይሆናል አማኞቹ ወደ መጽሐፍ
ቅዱስ ጥናታቸው እንዲመጣ በተደጋጋሚ የሚጋብዙት።

"ደጋግመው ይጋብዙኝ የነበሩት ጌታቸው ምክረና ዘውዱ ከበደ ነበሩ"
ይላል ዘለቀ። ዘውዱ እንደርሱው የናዝሬት ልጅ፣ በናዝሬትም
ጓደኛው የነበረ ወጣት ነው። "በመደጋገም ለሚጋብዙኝ መልሴ
ሁልጊዜም ይኸ ነገር ከእኔ ጋር አይሄድምና ተውኝ" የሚል ነበር ይላል
ዘለቀ። አንድ ቀን ተሳካላቸው። ዘለቀ ግብዣቸውን ተቀብሎ ወደ
ጥናታቸው ስፍራ አብሮአቸው ሄደ። ለጥቂት ጊዜ ካዳመጣቸው በኋላ
ስብሰባው ሳያልቅ አቋርጦ ወጣ። መሄድ ወደ ፈለገበት ሳይደርስ ግን
በፍፁም ያልተጠበቀ ነገር አጋጠመው።

የኃጢአተኛነት ስሜት እንደ መርግ ተጫነው። ፈጽሞ እንደ ጠፋ፣
ምንም ዓይነት ተስፋ እንደሌለው፣ ተሰማው። እግሮቹ ሊሽከሙት
አቃታቸው። ተንበረከከ። ወደቀ ማለት ወደ እውነቱ ይቀርባል።
"በዚያ ጊዜ ራእይ አየሁ. . . ጌታ የተሰቀለበትን መስቀል አየሁ. . .
መስቀሉ ባዶ ነበር. . . ማለት በላዩ ጌታ አልነበረም. . .ያን ጊዜ ለእኔ
ለኃጢአተኛው እዘንልኝ. . .ለእኔ ለኃጢአተኛው ራራልኝ እያልኩ
ጮህኩ. . .ከዚያ በኋላ የሆነውን በደንብ አላስታውስም" ይላል ዘለቀ።
መንፈስ ቅዱስ ነበር የወረደበት። "በልሳን የተናገርኩት ግን ከሁለት
ሳምንታት በኋላ ነበር።"

ዘለቀ ያንን ቀን አይረሳውም። ህዳር 5 ቀን 1956 ዓ.ም. ምሽት ላይ
ነበር። ያን ሰሞን ዘለቀን ያዩት ወንድሞች አንዳንድ እንግዳ ነገሮችን
ያደርግ እንደነበረ ይናገራሉ። ለምሳሌ በሰውነቱ ላይ ትቢያ እየነሰነሰ
ትንቢት ይናገር ነበር ይላሉ። ብዙዎች እስከ ዛሬም ድረስ ያንን
ድርጊት ከመንፈሳዊ ብስለት ማነስና ከቁጥጥር ውጭ ከተለቀቀ
ስሜታዊነት ጋር ያያይዙታል። ይህ ጸሐፊ ግን ይህንን አመለካከት
አይጋራም። የማይጋራውም አለምክንያት አይደለም።

ከዚያ በፊት ዘለቀ ማንም ጰንጠቆስጤአዊ አማኝ ምንም ሲያደርግ
አይቶና ምናልባትም ሰምቶም አያውቅም። እንደ ተባለው ዓይነተኛ
"ዓለማዊ" ወጣት ነው። "ስሜታዊነት"፣ "አለመብሰል" የሚባሉት
መግለጫዎች እንደዚህ ላለ ሰው አግባብነት የላቸውም። ትቢያ መነሰነስ
በብሉይ ኪዳን የማዘን፣ የመጸጸት፣ ራስን የማዋረድ ምልክት ነው።
አዲስ ኪዳናዊው ንስሐ ልባዊ እንጂ አፍአዊ (ውጫዊ) እንዳይደለ

ቢታወቅም፣ የውስጡ በውስጥ ብቻ አለመቅረቱ፣ ይልቁንም በው
መታየቱ ደግሞ እውነት ነው።

ይህም ብቻ አይደለም። ኢዚያት የሚተነበዩት ሁል ጊዜ በቃል ብ
እንዳይደለ፣ ብዙ ጊዜ በተምሳሌትም ሞምር እንደሆነ ይታወቃል
በብዙ ሰዎች ላይ ወደ ፊት ሊመጣ ያለውን ክፉ ነገር እግዚአብሔ
አስቀድሞ በኢዚያቱ ላይ ያመጣባቸዋል። ብዙ ሰው ወደ ፊት ሊሆነ
ያለውን ነገር ኢዚያቱ አስቀድመው ይሆኑታል። ምልክት ያደርጋቸዋ
ማለት ነው። በይሁዳ ሰዎች ላይ ሊመጣባቸው ላለ ብዙ ክፉ ነገ
ኢዚዩ ሕዝቅኤል ምልክት ሆኖላቸው እንደነበረው ማለት ነው (12፡6
12፡11፤ 24፡24፤ 24፡27)። እግዚአብሔር ዘለቀን ለእ
ለኢትዮጵያውያን ምልክት ሊያደርገው ፈልጎ ቢሆንስ?

ዘለቀ በተቅዋሙ ተማሪዎች መካከል ወዲያው የወሬ ርዕስ ሆኖ ባደ
ልክ በአመቱ በህዳር ወር አሰፋ ዓለሙ ጌታን ተቀበለ። አሰፋ ከዚያ
ተቅዋም ተመርቆ በዚያ ጊዜ በሐረር ከተማ ውስጥ በሞዴል ትምህርት
ቤት በመምህርነት እያገለገለ ነበር። "የመሰከረልኝ ጌታችው ምን
ነው. . . ሚስዮን ትምህርት ቤት ስለተማርኩ የወንጌል ነገር ለእ
እንግዳ አልነበረም. . .ያመኝም ስለነበረ The Voice of Healing
የሚባል መጽሔት አነብብ ነበር. . .ከመጽሔቱ አዘጋጆችም ጋር አጻጻ
ነበር" ይላል አሰፋ።

የሐረሩ ሥራስ ተጠናክሮ መንፈስ የጀመረው አማኞች ተማሪዎ
የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናታቸውን ሐረር ከተማው ውስጥ ወዳለው ወ
አሰፋ ዓለሙ ቤት ባዘሩበት ጊዜ ነበር። "በመጀመሪያው ቀን አራ
ብቻ ነበርን - እኔና ባለቤቴ፣ ዘለቀና ጌታቸው . . . ከዚያ እየሰ
ሄደ" ይላል አሰፋ። እየሰፋ ለመሄዱ ዋናው ምክንያት ተሳታፊዎ
ባልንጀሮቻቸውን እየጋበዙ ያመጡአቸው ስለ ነበረና የመጡትም ጌታ
ይቀበሉ፣ ከህመማቸው ይፈወሱ፣ በመንፈስ ቅዱስም ይጠመቁ ስለ ነ
ነው። በመጀመሪያው ሰሞን ተጋብዘው ከመጡት አንዱ ቤ
መንግሥቱ ነበረ።

ቤተን የጋበዘው አሰፋ ነው። ቤተ በዚያን ጊዜ የሐረር መምህራ
ማለልጠኛ ተቅዋም የመጨረሻ አመት ተማሪ ነበር። "ታማሚ ነበር
ይላል አሰፋ። "ሐኪሞች ያልቻሉት ሕመም ነበረበት. . .በመንፈ
ቅዱስ በተጠመቀ ጊዜ ነው የተፈወሰው . . .ከዚያ በ
አላመመውም።" አሰፋ እራሱ በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቀው በጥ
ወር 1957 ዓ.ም. አዲስ አበባ ነው። "በውሀ በተጠመቅሁ በዚያ
ጊዜ ነበር በመንፈስ ቅዱስም የተጠመቅሁት. . .በውሀ ያጠመቀኝ ከ
ወልደ ማርያም ነበር. . .ከውሀው ስወጣ እራሴን በልሳን እየተናገርኩ

አገኘሁት . . . በመጀመሪያ የተናገርኩበት ልሳን የሚተረጎም ልሳን
ነበረ . . . ከበደ ተረጎመው. . .የመተርጎም ስጦታ ነበረው. .
.ትንቢት ነበር፣ ጌታ ለአገልግሎት የጠራኝ ያን ጊዜ ነበር. . እኔ ግን
ሳልወጣ ትንሽ ዘገየሁ" ይላል አሰፋ።

በዚያው አመት ትምህርት ቤት ለትንሳኤ በዓል ሲዘጋ ዘለቀና አሰፋ
ለአገልግሎት ከሐረር ወደ ናዝሬት መጥተው ነበር። ለናዝሬቶቹ
"የሰማይ ብርሃን" ወጣቶች ስለ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት
ሊመሰክሩላቸው፣ እጆቻቸውንም እየጫኑ ሊጸልዩላቸው ፈልገው ነበር።
ናዝሬቶች ግን ፈቃደኞች አልነበሩም። አንደኛ ያ ሰሞን ከትንቢት ጋር
በተያያዘ ከባድ ቀውስ ደርሶባቸው፣ ግራ ተጋብተውና ተበታትነው
በቁጥር በጣም ጥቂቶች ብቻ የቀሩበት ነበር። ሁለተኛ ዘለቀ የናዝሬት
ልጅ ስለሆነ በሰውነቱ ላይ ትቢያ እየነሰነሰ ትንቢት የመናገሩ ወሬ
በናዝሬቶች ዘንድ ተሰምቷል። ዘለቀና አሰፋ አንዳንዶቹን በየቤታቸው
እየፈለጉ አነጋገሩአቸው። ፈቃደኞች ሆነው ላገኙአቸውም እጆቻቸውን
እየጫኑ ጸለዩላቸው። ቁጥራቸው ባይታወቅም ከተጸለየላቸው ውስጥ
ብዙዎቹ በመንፈስ ቅዱስ እየተጠመቁ በልሳኖች ተናገሩ።

አማሂ ቻቻ ለመጀመሪያ ወደ ኢትዮጵያ የመጣበትን ትክክለኛ ጊዜ
ለማወቅ ያጋጠመኝን ችግር በተመለከተ አነሳለሁ ያልኩትን ሦስተኛ
ምክንያት አሁን ላንሳ። አሰፋን በውሀ ያጠመቀው ከበደ መርካቶ
ከሚገኘው የፊንላንድ ሚስዮን ጋር ከነበሩት ወጣቶች አንዱ ነው። ይህ
ጸሐፊ ከበደን አግኝቶ አላነጋገረውም። ብዙዎች እንደሚሉት ግን
በአማሂ የመጀመሪያ ጉብኝት ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ ከተጠመቁት
የፊንላንድ ሚስዮን ወጣቶች መካከል አንዱ ነው።

እንደ አሰፋ ከሆነ ከበደ ከጥር ወር 1957 ዓ.ም. በፊት በመንፈስ ቅዱስ
ተጠምቆ በልሳን ይናገር ነበር። የአሰፋን ልሳን መተርጎም የቻለው
በዚህ ምክንያት ነው። እንደነ ወንጌላዊ ሚልክያስ ከሆነ ደግሞ ከበደ
እስከ 1957 ዓ.ም. መጨረሻ ወይም እስከ መስከረም ወር 1958 ዓ.ም.
ድረስ በመንፈስ ቅዱስ አልተጠመቀም። በውሀና በመንፈስ ቅዱስ
የተጠመቀበትን ጊዜ በተመለከተ አሰፋ ተሳስቷል እንዳንል በ1957
ዓ.ም. የትንሳኤ በዓል ሰሞን ከዘለቀ ጋር አብረው በናዝሬት
ማገልገላቸው በብዙዎች ተረጋግጦአል። ተጨማሪ ማጣራት የሚጠይቅ
አንድ ነጥብ እዚህ ውስጥ ይቀራል። እርሱም ከበደ በመንፈስ ቅዱስ
የተጠመቀው በእውነትም በአማሂ አገልግሎት ጊዜ የመሆኑ ወይም
ያለመሆኑ ጉዳይ ነው።

ጎዳናዎች ሁሉ ወደ አዲስ አበባ ይነጉዳሉ

"መንገዶች ሁሉ ወደ ሮም ያመራሉ" የሚል የእንግሊዝ እንደሆነ እንሰ
የቆየ ብሂል አለ። ያ ብሂል ስለ ሮም ከተማ እውነት እንደ ነበረ ሁሉ
ይሽኛውም ስለ አዲስ አበባ እውነት ነው። ጳንጠቆስጤአዊው
ሪቫይቫል ወደ ኢትዮጵያ የገባባቸውን ሁለት በሮችና ከኢትዮጵያ
የተነሳባቸውን ሁለት ከተሞች ተመልክተናል። እነርሱም አዋሳና አዲ
አበባ ናዝሬትና ሐረር ናቸው። ሆኖም በኢትዮጵያ የሪቫይቫሉ ማዕከ
ሆና የተገኘችው ዋና ከተማዋ አዲስ አበባ ናት። ለምን እንደዚ
ሊሆን እንደቻለ መለኮታዊና ሰብአዊ ምክንያቶች አሉ። ብዙውን ጊ
መለኮታዊው ሰብአዊውን መሳሪያው ስለሚያደርግ ሁለቱን ለያይ
ማመልከት ያስቸግራል። ስለ ሆነም ይኸ መለኮታዊ፣ ይሽኛው ደግሞ
ሰብአዊ ሳይሉ እንዲያው በጥቅሉ ዋነኞቹን ምክንያቶች መመልከ
ይሻላል።

አዲስ አበባ የንጉሡና የንጉሣውያኑ፣ የመሳፍንቱና የመኳንን
መኖሪያ ናት። የህግ መወሠኛውና የህግ መምሪያው ምክር ቤቶ
የሚገኙት እዚህው አዲስ አበባ ውስጥ ነው። የካቢኔና የዲፕሎማቲ
ኮር አባላቱ፣ የአገር ውስጥና የውጭ አገር ዜና የሚዘግቡ ጋዜጠኞች
የራዲዮና የቴሌቪዥን ጣቢያዎች የሚገኙት አዲስ አበባ ውስጥ ነው።
የመንግሥታዊዋ ቤተ ክርስቲያን አመራር ሰጭ አካላትም ያሉት አዲ
አበባ ውስጥ ነው። በኢትዮጵያ በአገር አቀፍና በዓለም አቀፍ ደረ
ትኩረት እንዲስብ የሚፈለግ ማናቸውም ነገር መከናወን ያለበት ያ
ጥርጥር አዲስ አበባ ውስጥ ነው።

አዲስ አበባ የመንግሥት መቀመጫ ናት። አገሪቱ የምትመራባቸው
ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና አስተዳደራዊ ፖሊሲዎች
የሚመከርባቸውና የሚከርባቸው አዲስ አበባ ውስጥ ነው። ፖሊሲ
አውጪዎቹ የዛሬዋን ብቻ ሳይሆን የነገዋንና የከነገ ወዲያዋን ኢትዮጵ
እንዲያስቡ፣ በፊትዋም የተጋረጡትን ችግሮች እንዲገነዘቡ፣ ቁሳዊውን
ብቻ ሳይሆን መንፈሳዊውንም መፍትሔ ግምት ውስጥ እንዲያስገቡ
ለጳንጠቆስጤአዊው ሪቫይቫል ማዕከል ሊሆን የሚገባው ከአዲስ አበ
በቀር ሌላ ማነው?

በአሊዩ በኤልያስ ዘመን እስራኤል የአስደንጋጭ ፍርድና የአስደናቂ
ሪቫይቫል ምድር ሆና አገር። ታዲያ ስለ ሁለቱም በቅድሚያ እንዲሰ
በእግዚአብሔር የተፈለገው ሰው ንጉሡ አክአብ አገር (1ኛ ነገ 17:1
18:1፤ 18:41-48)። በኢትዮጵያም ላይ እየመጣ ስለ አገረው ቁጣ
ያንንም ቁጣ እንዲቀድመውና ከተቻለም እንዲያስቆመው በእግዚአብሔር
ስለ ተላከው ጳንጠቆስጤአዊ ሪቫይቫል በቅድሚያ ማወቅ ያለበት ከንጉሡ

ይልቅ ሌላ ማነው? ንጉሡም ያውቁ ዘንድ ለጳንጠቆስጤአዊው
ሪቫይቫል ማዕከል መሆን የሚገባው ከአዲስ አበባ የተሻለ ሌላ ማን
ይኖራል?

ሪቫይቫሉ የተቀሰቀሰው በተማሪዎች መካከል ነው። አዲስ አበባ ደግሞ
ከዛሬም ይልቅ ያኔ የተማሪዎች መናኸሪያ ነበረች። በየጠቅላይ ግዛቱ
ከተሞች ትምህርታቸውን ያጠናቀቁ ተማሪዎች የኮሌጅ ትምህርታቸውን
ለመቀጠልም ሆነ ሥራ ለመፈለግ ወደ አዲስ አበባ ነው የሚመጡት።
አዲስ አበባ መናኸሪያነትዋ ለተማሪዎች ብቻም አይደለም። ከአገሪቱ
አራት ማዕዘኖች ሻጩና ሸማቹ፣ ደጀ ጠኚውና ተሟጋቹ፣ ዘመድ
ጠያቂውና ብልጭልጭታ ናፋቂው ሁሉ የሚረግጣት ከተማ ናት።
ማንም በማንም መታወቅ ቀርቶ መታየት የማይችልባት ዱር ናት።
ጳንጠቆስጤአዊውን ሪቫይቫል ብዙዎች እንዲያዩት ዕድል ለመስጠት፣
በአጭር ጊዜ ውስጥም በአገሩ ሁሉ ለማዳረስ ከአዲስ አበባ የተሻለ
የማሰራጫ ማዕከል የት ይገኛል?

በመስከረም ወር 1958 ዓ.ም. ተካ ገብሩ፣ ያቅባዝጊ ስዩም፣ ብርሃኔ
አብርሃና ፊልጶስ ኪሜሬ የተባሉ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ
ተማሪዎች አብረው ሊኖሩ ይወስናሉ። አንዲት ባለ ሁለት ክፍል ቤት
በሐያ አምስት ብር ወርሐዊ ኪራይ በአራት ኪሉ አካባቢ ይከራያሉ።
አራቱም አማኞች ናቸው። ያቅባዝጊ ቀደም ሲልም የወንጌል ነገር
የገባው የአስመራ ከኒሻ[14] ነው። ፊልጶስ የደቡብ ልጅ ሲሆን ሁለተኛ
ትውልድ ወንጌላዊ ክርስቲያን ነው። ተካና ብርሃኔ ጌታን የተቀበሉት
በሰኔ ወር 1956 ዓ.ም. የሁለተኛ አመት የመሐንዲስ ኮሌጅ ተማሪዎች
ሆነው ነው።

ለቆዩትም ሆነ ለአዲሶቹ ክርስትናን አዲስ ያደረገ ነገር በቅርቡ
በመካከላቸው ተከስቶአል። ያም የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ነው። ያ
ቅባዝጊ ባለፈው ክረምት ለዕረፍት አስመራ ሄዶ በመንፈስ ቅዱስ
ተጠምቆ ተመልሶአል። ስለዚህ አዲስ ክስተት የመሰከሩለትና በመንፈስ
ቅዱስ እንዲጠመቅ የጸለዩለት የሐረር መምህራን ማሠልጠኛ ተቅዋም
ምሩቆቹ ቤተ መንግሥቱና ዓለም ብሥራት ናቸው። ብርሃኔም ባለፈው
ክረምት ለኮንፈረንስ አዋሳ ወርዶ በመንፈስ ቅዱስ ተጠምቆ ተመልሷል።
የጸለዩለት የናዝሬቶቹ የሰማይ ብርሃን ወጣቶች ናቸው። ፊልጶስ አባቱ
በመጀመሪያ የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን በኋላም በአዋሳ የሰዊድን
ፈላደልፍያ ቤተ ክርስቲያን ወንጌላዊ ናቸው። እርሱም በአዋሳ አካባቢ
በሚሆን ጊዜ ሚስዮናውያኑን በማስተርጎም ያገለግል ነበር። ከመንፈስ
ቅዱስ ጥምቀት ጋር የተዋወቀው በዚያን ጊዜ በአዋሳ ሳይሆን እንዳልቀረ
ነው የሚታመነው። ተካ ገና ነው። ግን በጣም ይፈልጋል።
ለመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ይጸለያል በሚባልበት ቦታ ሁሉ አይጠፋም።

እነዚህን ያገናኛቸው የትምህርት ገበታ ነው። አብረው ለመኖ
ያበቃቸው ግን በሕይወታቸው የፈሰሰው አዲስ ፍቅር ነው። እንደዚ
ያፈቀራቸውን ጌታ የበለጠ ለማወቅ የመጣባቸው አዲስ ጉጉት ነው
ሌሎች ባልንጀሮቻቸውን ከዚህ ጌታ ጋር ለማስተዋወቅ ያደረባቸው ብ
ፍላጎት ነው። ስለዚህም ማክሰኞና ሐሙስ እራት በዩኒቨርሲቲ
ካፌቴሪያ ከበሉ በኋላ በጋራ ቤታቸው ውስጥ የጸሉት ጊ
እንዲኖራቸው ይስማማሉ። በመጀመሪያዎቹ ጥቂት ቀናት አራቱ ብ
ነበሩ። ከዕለታት በአንደኛው ቀን እራሳቸውን ለጌታ አስረክቡት
ለሌሎች ስለ እርሱ በመናገር ሊያገለግሉት እንደሚፈልጉ ነገሩት
ሕይወታቸውን ለክብሩ እንዲቀድሰውና ሌሎችን ሊያሰናክል ከሚችል ነ
ሁሉ እንዲያጠራው ለመኑት። ቤታቸውንም እንዲጠቀምበ
አሳልፈው ሰጡት። ከዚያ በኋላ በዩኒቨርሲቲው ግቢ ውስ
መመስከሩንና ባልንጀሮቻቸውን ወደ ጸሉት ስብሰባቸው መጋበዙ
ተያያዙት።

እንደ "312 አዙሳ ጎዳና" በኢትዮጵያ ለጳንጠቆስጤአዊው ሪቫይቫ
ፍንዳታ በእግዚአብሔር የተመረጠችው ስፍራ ይህች ቤት ሆነች። ከላ
እንዳየነው የመጀመሪያዎቹ ገባር ጎርፎች የተጠረቃቀሙት ከአስመራ
ከአዋሳና ከአዲስ አበባ ነው። ቀጥለው ወደ ወንዙ የፈሰሱት በዚያ
ጊዜ በዩንቨርሲቲው በመማር ላይ የነበሩ የናዝሬት ሰማይ ብርሃ
ወጣቶች ናቸው። በአካባቢው ከነበሩት ትምህርት ቤቶችም በመቶዎ
የሚቆጠሩ ጌታን እየተቀበሉ በመንፈስ ቅዱስ ተጠምቀዋል። ከአራ
ኪሎና ከስድስት ኪሎ ኮሌጆች፣ ከበዕደ ማርያም፣ ከቀዳማዊ ኃይ
ሥላሴ የአርሶች ማሰልጠኛ ተቅዋም፣ ወዘተ. . . ወዘተ። ተካ ገብሩ
በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቀው በዚህችው እራሱ በተከራያት ቤት ውስ
ነበር።

በዚያች ቤት ውስጥ የሆነው ነገር ግን ይህ ብቻ አልነበረም። ሰዎ
በጸሉት ከበሽታ ይፈወሱ፣ ከአጋንንት እስራት ይፈቱ፣ ለተለያ
ችግሮቻቸው መፍትሔ ያገኙ ነበር። ይህም ከትምህርት ቤቶች ብ
ሳይሆን በዙሪያ ካሉት መንደሮችም ሁሉ ሰዎችን መሳብ ጀመረ
ከመርካቶው የፊንላንድ ጳንጠቆስጤአዊ ሚስዮን አንድ አንድ ወንድሞ
ጠቅልለው የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎቹን ንቅናቄ የተቀላቀሉት በዚህ ጊ
ነበር። ከወዲህ ብርቱ ስበት ነበረባቸው። እየሆነ ያለውን ነገር በጣ
ወደውታል። ከወዲያ ደግሞ ብርቱ ግፊት ነበረባቸው። በጊዜ
በመርካቶው ጸሉት ቤት በዋናነት ከሚያገለግሉት ፊንላንዳዋያት እህቶ
ጋር በብዙ ጉዳዮች ላይ መጣጣም አቅቷቸው ነበር።

አማዜ ቻቻ ወደ ኢትዮጵያ ከመጣበት ጊዜ ጋር በተያያዘ ላጋጠመ
ችግር አራተኛውንና የመጨረሻውን ምክንያት እዚህ ላይ ላንሳው።
በ1957 ዓ.ም. ክረምት በአዋሳ በነበረው ኮንፈረንስ ላይ ከሐረር እን

አሰፋ ዓለሙ፣ ከአራት ኪሎው የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ እነ
ብርሃኔ አብርሃ፣ ከመርካቶው የፊንላንድ ሚስዮን እነ ከበደ
ወልደማርያም ተካፍለዋል። ምናልባት ከሌሎች ቦታዎች ሌሎችም
ሳይካፈሉ እንዳልቀሩ መገመት ይቻላል። እነዚህን ሁሉ ወጣቶች በዚያ
አመት ወደ አዋሳ እንዲሄዱ የሳባቸው ነገር ምን ይሆን? ምናልባት ከዚያ
በፊት ከነበሩት ኮንፈረንሶች በአንዱ ላይ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት
ተከስቶ፣ የዚያም ወሬ በብዙ ቦታ ተሰምቶ እንደሆን ብዬ ነው።

አማዜ ቻቻ ለመጀመሪያ ወደ ኢትዮጵያ የመጣበትን ጊዜ በተመለከተ
ልል የፈለግሁትን ሁሉ ብያለሁ። የተሻለና ወሳኝ መረጃ ያላቸው
ሰዎች የሁላችንንም ልብ የሚያሳርፍ ነገር ይዘው ወደ ፊት ብቅ ይላሉ
ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። ከአማዜ ከራሱ አፍ ለመስማትም ሙከራ
አድርጌ ነበር። ነገር ግን ወደ ጌታ እንደ ሄደና ቤተሰቹም የሚኖሩት
ከናይሮቢ ውጭ መሆኑን ስለ ሰማሁ በዚያ በኩል የሚደረገው ጥረት
ውጤት አልባ ሆኖአል።

ወደ አራት ኪሎ እንመለስ። ያቺ ቤት በሰዎች ተሞላች። ችግር
ተፈጠረ። አንድ ነገር መደረግ አለበት። በዚያች ባለ ሁለት ክፍል
ትንሽ ቤት ውስጥ ለሚሰጠው አገልግሎት እራሱን በራሱ ተጠሪ
አድርጎ ያስቀመጠ፣ ወይም በሌሎች የተመረጠ፣ የነጠላም ሆነ የወል
አመራር ሰጭ አካል አልነበረም። የሚደረገው ሁሉ የሚያረገው
በፍቅር፣ በፈቃደኛነትና በፍላጎት ነበር። የውስጥ ሊባሉ የሚችሉ
ወንድሞች ግን ነበሩ። በእነርሱ አካባቢ ብዙ ሰዎች መያዝ የሚችል
ቤት የማግኘቱ ጉዳይ የዘወትር የጸሉት ርዕስ ሆነ። ብዙም ሳይቆይ
ናዝሬት ትምህርት ቤት ፊት ለፊት አንድ ቤት ተገኘ።

"ቤቱን ልናይ የሄድን ወጣቶች በቁጥር አስራ ሦስት ነበርን . . . ጎን
ለጎን ሳይሆን ፊትና ኋላ ሆነን በሰልፍ ስንሄድ እስከ አሁን ድረስ በዓይነ
ህሊናዬ ይታየኛል" ይላል ሰሎሞን ከበደ። ለቤቱ የተጠየቀው ወርሐዊ
ኪራይ 250 ብር ነበር። ከየት መጥቶ እንደሚከፈል ሁለቱም ወገኖች
የሚያውቁት ነገር ባይኖርም፣ አከራዮች በቂ ተያዥ ተቀብለው፣
ተከራዮችም ጌታን አምነው ውል ተዋዋሉ።

አገልግሎቱ ወደ ሁለተኛው "ቻፕል"[15] የዞረው በዚያው አመት
አጋማሽ ገደማ ላይ ነው። በመጀመሪያው ቻፕል ውስጥ ይደረጉ
የነበሩት ነገሮች ሁሉ በዚህኛውም ውስጥ ተጠናክረው ቀጥለዋል።
ረቡዕና ዓርብ ከቀድሞም ጀምሮ የያምና የጸሉት ቀናት ነበሩ። ቁርስና
ምሳ አይበላባቸውም ማለት ነው። ከዚህ በተጨማሪ በሁለተኛው ቻፕል
ውስጥ የአዳር ጸሉት ተጀመረ። ቢያንስ በሳምንት አንድ ቀን ብዙ
ሰዎች እየጸለዩ ያድራሉ። በዚህ በሁለተኛው ቻፕል የዕድሜ ዘመን
ሪቫይቫሉን ለዘለቄታው አዲስ አቅጣጫ ያስያዙት ሁለት ነገሮች

ተከናውነዋል። አንደኛው የዕሑድ አገልግሎት መጀመር ነው። ቀደም ሲል ዕሑድ ዕሑድ ወጣቶቹ ለመደበኛው የቤተ ክርስቲያን አምልኮ ወደ ተለያዩ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያን ነበር የሚሄዱት። ሁለተኛው በዚያው አመት በሐምሌ ወር መጨረሻ ላይ የተደረገው የመጀመሪያው ብሔራዊ ጳንጠቆስጤአዊ ኮንፈረንስ ነው። ሁለቱንም እንመለስባቸዋለን።

መንግሥታዊ መጓጓዣ

አዲስ ኪዳን እንደሚለው ጌታ ኢየሱስ የተወለደው "የተወሰነው ዘመን በደረሰ ጊዜ" ነው (ገላ 4:4)። አንድ አንድ ትርጉሞች "ጊዜው ሲሞላ" ነው የተወለደው ይላሉ። የተወሰነው ዘመን በደረሰ ጊዜ ወይም ጊዜው ሲሞላ ማለት በእግዚአብሔር ልብ ውስጥ የነበረ አንድ የሆነ ቀን ከሆነ ቦታ ተነስቶ፣ ሲጓዝ ሲጓዝ ቆይቶ፣ የሆነ ቦታ ሲደርስ ማለት አይደለም። መሰናዶው ሲያልቅ፣ ዝግጅቱ ሲጠናቀቅ፣ ቅድመ ሁኔታዎች ሲሟሉ፣ ማለት ነው።

"ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ፣ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ" የሚለው የጌታ ትዕዛዝ በተግባር ይተረጎም ዘንድ በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቁ ደቀ መዛሙርት መኖራቸው ያለጥርጥር አስፈላጊ ነበር። በቂ ግን ያለ ጥርጥር አልነበረም። ወደ ዓለሙ ሁሉ ለመዘዋወር ምቹ የሆነ ፖለቲካዊ ሁኔታ፣ ከቦታ ወደ ቦታ ለመጓጓዝ የሚያስችል የየብስና የባህር መገናኛ፣ በየአገሩ ከሚኖሩት ሕዝቦች ጋር ለመግባባት የሚቻልበት የጋራ ቋንቋ ያስፈልጋሉ። ለመነሻነት የሚያገለግል መንፈሳዊ ሁኔታም መገኘት አለበት።

የመጀመሪያዎቹ ደቀ መዛሙርት ወንጌልን ለመስበክ ወደ ዓለም ሁሉ እንዲሄዱ የታዘዙት በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ እነዚህ አራት ነገሮች ተሟልተው የተገኙበት ነበር። ሮማውያኑ ዓለሙን የመግዛቱን ሥልጣን በእጃቸው ካስገቡ ዘጠና አመታት አልፎአቸዋል። በእነዚህም አመታት ውስጥ በግዛታቸው ውስጥ ሥርዓትንና ጸጥታን አስፍነዋል። የሚገዙአቸውንም አገሮች በጎዳናዎች አገናኝተዋል። በመካከላቸውም ሀብረትንና አንድነትን አጠናክረዋል። በቋንቋ ረገድ በዚያን ጊዜ ዓለሙ ሁሉ የግሪክ ቋንቋ ይናገር ነበር። የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት በግሪክ ቋንቋ የተጻፉት ጸሐፊዎቹ በሙሉ ግሪካውያን ስለ ነበሩ አይደለም። ግሪክኛ የዓለሙ ቋንቋ ስለነበረ እንጂ። አይሁድና የአይሁድ እምነትም የዚያን ጊዜውን ዓለም ሞልተውት ነበር። በየከተማው የነበሩት የአይሁድ ምኩራቦች ለወንጌል ስብከት ምቹ መረማመጃ ሆነዋል።

በኢትዮጵያ የፈነዳው ጳንጠቆስጤአዊ ሪቫይቫል በጣም በጥቂት አመታት ጊዜ ውስጥ ነበር ወደ ኢትዮጵያ ከተሞች ሁሉ የተሰራጨው። ዛሬም ቢሆን ጉልህ የሆነ የመገናኛ ችግር ባለባት ኢትዮጵያ በዚያን ጊዜ ሪቫይቫሉ የተሰራጨበትን ፍጥነት ስናስተውል ሪቫይቫሉ የፈነዳው በእውነትም በእግዚአብሔር "የተወሰነው ዘመን በደረሰ ጊዜ" ነበር እንድንል እንገደዳለን። በዚያ ሪቫይቫል እግዚአብሔር ሊያገኛቸው የፈለገው ወጣቶችን እንደ ነበረ ተመልክተናል። ወጣቶችን ሊያገኛቸው መፈለጉን የምናውቀው ሪቫይቫሉ በትምህርት ተቅዋማት ውስጥ በመፈንዳቱ ብቻ አይደለም። የተዘጋጀለት መጓጓዣም በአብዛኛው ወደ ትምህርት ትቋማት የሚያደርሰው ሆኖ በመገኘቱም ጭምር ነው።

በ1956 ዓ.ም. የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ብሔራዊ አገልግሎት የሚባል ፕሮግራም በኢትዮጵያ ተጀምሮ ነበር። የዚህ አገልግሎት ዓላማ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የሦስተኛ አመት ትምህርታቸውን ከጨረሱ በኋላ ለአንድ አመት በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በማስተማር እንዲያገለግሉ ነው። መንግሥት በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሚያስተምሩ መምህራን ረገድ ያለበትን እጥረት በዚህ ይሸፍናል። መምህራኑን ከውጭ አገር ለማስመጣት የሚያስፈልገውን ከፍተኛ ወጭም ያድናል። የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎቹም አገራቸውን ይውቁበታል። የሥራ ልምድ ያገኙበታል። መንግሥታቸው ያለበትንም ኃላፊነት ከብደቱን ይረዱበታል።

"የከፍተኛ ትምህርት ተቅዋማት ተማሪዎች በሙሉ የከሸፈው መፈንቅለ መንግሥት ደጋፊዎች የሆኑት አገራቸውንና ችግሮችዋን በደንብ ስለማያውቁ፤ በመንግሥት ጫንቃ ላይ ያለው ኃላፊነትም ክብደቱ ስለማይሰማቸው ነው። የብሔራዊ አገልግሎቱ ለነዚህ ሁኔታዎች አጥጋቢ ምላሽ ይሰጣል" የሚሉ አማካሪዎች ምክር ከፕሮግራሙ በስተጀርባ ነበር ይባላል። ሌሎች ደግሞ ፕሮግራሙ ከላይ እንደ ተጠቀሱት ባሉ ማር መሳይ ምክሮች የተሸፈነ የኮሙኒስቶች ሴራ ነበር ይላሉ። ኮሙኒስቶቹ የኮሙኒዝምን ጽንሰ ሀሳብ በሁለተኛ ደርጃ ትምህርት ቤቶች ለማሠራጨት፣ እስከ አሁን ከኮሌጆች አጥር ያልዘለለውን የተማሪዎች አብዮታዊ ንቅናቄ ወደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ አስርጎ ለማስገባት ሲሉ የፈጠሩት ዘዴ ነበር ይላሉ።

ያም ሆነ ይህ ፕሮግራሙ የተጀመረበትና ሪቫይቫሉ የፈነዳበት ጊዜ መገጣጠሙ የአጋጣሚ ጉዳይ ሊሆን አይችልም። ከ1957 ዓ.ም. ጀምሮ በነበሩት ተከታታይ አመታት ብዙ ጳንጠቆስጤአውያን ተማሪዎች በብሔራዊ አገልግሎት ፕሮግራም ለአንድ አመት በየጠቅላይ ግዛቱ ወደሚገኙ የሁለተኛ ደርጃ ትምህርት ቤቶች ሄደዋል። በሄዱባቸውም ትምህርት ቤቶች ጳንጠቆስጤአዊውን እሳት አቀጣጥለዋል።

ጳንጠቆስጤአዊውን እሳት በአገሪቱ በማድረስ የሚጠቀሱት ሌሎቹ የሞያ ማሰልጠኛ ተቅዋማት ናቸው። ከእነዚህም መካከል የሐረርና የደብረ ብርሃን መምህራን ማሰልጠኛዎች፣ የባህር ዳር ፖሊቴክኒክ ኢንስቲትዩት ይጠቀሳሉ። ያቅባዝጊ ከአዲስ አበባ ወደ አስመራ ለዕረፍት በሄደበት ከሐረር ወደ አስመራ በመምህርነት ከተላኩት ከእቴተ መንግሥቱና ከነዓለም ብሥራት ጋር መገናኘቱን ቀደም ሲል ጠቅሰናል። በዚያ ክረምት በአስመራ በመንፈስ ቅዱስ ከተጠመቁት አንዱ ጋይም ክብረአብ ነው። እርሱ ጌታን ያገኘው በዚያው አመት የፖሊቴክኒክ ተማሪ በነበረበት በባህር ዳር ነበር። ወደ አስመራ የሄደው ለዕረፍት ነው።

ጳንጠቆስጤአዊው እሳት ከስፍራ ወደ ስፍራ የተጓዘባቸው መንገዶች እነዚህ ብቻ አይደሉም። ትምህርት ቤቶች ሲዘጉ ለዕረፍት ወደ ቤተ ሰቦቻቸው በሚሄዱ የሁለተኛ ደረጃና የከፍተኛ ትምህርት ተቅዋማት ተማሪዎች አማካይነት እሳቱ ወደ ብዙ ከተሞች ተዳርሷል። ከመምህርነት ጋር ባልተያያዘ መንገድ የጤና፣ የግብርና፣ የእንስሳት ሳይንስ ተቅዋማት ምሩቃን ለሥራ ወደ ተመደቡባቸው ከተሞች አብርአቸው ተጉዟል። ለዕረፍት ወደ ቤተሰቦቻቸው ከሚሄዱት ተማሪዎች በስተቀር የተቀሩት ሁሉ ግን ወደ ሄዱባቸው ከተሞችና ትምህርት ቤቶች የሄዱት ለመንግሥታዊ ሥራ በመንግሥት እየተላኩ በአብዛኛው በመንግሥት ወጭ ነበር።

"ያገሩን ሰርዶ ባገሩ በሬ"

የሐያኛው ምእት አመት ሁለተኛ አጋማሽ በሦስተኛው ዓለም አገሮች ውስጥ በምዕራባውያን ሚስዮናውያን የሚደረግ እንቅስቃሴ ሁሉ በጥርጣሬና በጥያቄ ውስጥ የወደቀበት ጊዜ ነበር። ያ ወቅት ቁጥራቸው ጥቂት ያይደለ የሦስተኛው ዓለም አገሮች ከምዕራባውያን ቅኝ ገዥዎቻቸው ጋር የሞትና የሽረት ፀረ ኮሎኒያሊስት ትግል የሚያደርጉበት ነበር። ያ ጊዜ የሰውን በሰው መበዝበዝ ለማስቀረት ብቸኛው መፍትሔ በማርክሲዝም ፍልስፍና በመመራት የሠርቶ አደሩ የበላይነት ማረጋገጥ እንደሆነ በብዙዎች ዘንድ የታመነበትና ፀረ ኢምፔርያሊስት ትግል የተጧጧፈበት ነበር። ያ ዘመን ዓለሙ በሙሉ በገገር እና በተገገር፣ በጨቋኝና በተጨቋኝ፣ በበዝባዥና በተበዝባዥ ለሁለት ተከፍሎ እርስ በራሱ የሚፋለምበት ዘመን ነበር። ፍልሚያውም ይካሄድ የነበረው በቤት፣ በሰፈር፣ በትምህርት ቤት ፣ በሥራ ስፍራ፣ በቤተ ክርስቲያን፣ በከተማና በገጠር፣ እንዲያው በሁሉ ቦታ ነበር።

በዚያ ወቅት በሦስተኛው ዓለም አገሮች ውስጥ በመንቀሳቀስ ላይ የነበሩት ሚስዮናውያን ሁሉም የነዚያኑ አህጉራት ከሚባሉት ከአውሮፓ (በተለይም ምዕራብ አውሮፓ)፣ ከአሜሪካ (በተለይም ሰሜን

አሜሪካ)፣ ከአውስትራሊያና ከኒውዚላንድ ነበር የመጡት። ሁሉም ግን ምዕራብ አውሮፓውያን ነበሩ። ምክንያቱም በአሜሪካ፣ በአውስትራልያና በኒውዚላንድ የሰፈሩት ምዕራብ አውሮፓውያን ነበሩና ነው። እነርሱም የሰፈሩባቸውን አገሮች ለዘለቄታው የራሳቸው ለማድረግ በአገሬዎቹ ላይ ያደረሱት ግፍ ለተገፉ ሕዝቦች ሁሉ ተገልጧል። "ቀይ ሕንዳውያን" በአሜሪካ፣ አቦሪጅኖች በአውስትራሊያ፣ ማኦሪዎች በኒውዚላንድ የሆኑትንና እየሆኑ ያሉትን የዓለም ጭቁን ሕዝቦች ጆሮ ጠግቦታል። በደቡብ አፍሪቃም "ዳቶቼ" የዘረጉት የአፓርታይድ ፖሊሲ ነሮች ለጥቁሮች ያላቸውን ኢሰብአዊ አመለካከት በግልጥ አሳይቷል።

ጥርጣሬውና ጥያቄው የነበረው በሚስዮናውያኑ ላይ ብቻም አልነበረም። በራሱ በእምነቱ ላይም ነበር። የኮሎኒያሊስቶችና የኢምፔርያሊስቶች ሃይማኖት የሆነው ወንጌላዊ ክርስትና እንዴት እውነት ሊሆን ይችላል? እውነት ከሆነስ ክርስቲያኖች እንዴት ኮሎኒያሊስት ወይም ኢምፔርያሊስት ሊሆኑ ይችላሉ? ትንታኔው ከዚህ የሚያልፍ ግን አልነበረም። ወንጌላዊ ክርስትና እውነት በመሆኑና በተከታዮቹ መካከል ኮሎኒያሊስቶችና ኢምፔሪያሊስቶች የሆኑ በመገኘታቸው በእነዚህ ሁለት የተራራቁ ጫፎች መካከል ያሉትን መለኮታዊ፣ ሰብአዊ፣ ታሪካዊና፣ ሌሎችም ሁኔታዎች ለማስተንተን ብዙዎቹ ብቃቱም፣ ፍላጎቱም፣ ትእግሥቱም ያላቸው አልነበሩም። እነዚህ ያሏቸው ጥቂቶቹ ደግሞ በነገሮች ሂደት ላይ ተጽዕኖ ለማድረግ ችሎታው አልነበራቸውም።

ሚስዮናውያኑ እንደ ማንኛውም ሰው በልደት፣ ወይም በምርጫ የአንድ አገር ዜጎች ናቸው። በዘር መድልዎም ሆነ በሌሎች ጉዳዮች ላይ የመንግሥታቸውን ፖሊሲ አጥርተው የሚያውቁና የሚደግፉ በመካከላቸው አሉ። "ዘር ከልጓም ይስባል" እንደሚባለው የአባቶቻቸውን አመለካከት የሚጋሩ፣ የዚያም አመለካከት ኢክርስትያናዊነት የማይታያቸው በመካከላቸው ነበሩ። እንዲያውም ለዚያ አመለካከት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ሊሰጡት የሚቃጣቸውም አይጠፉም። ሆኖም ሚስዮናውያኑ ሁሉ እንደዚያ ያሉ አልነበሩም። ቁጥራቸው ብዙ አይደለም እንጂ እንደዚህ ስላሉት ችግሮች አስቀድመው ያነቡ፣ በጥሞናም ያሰቡ፣ አስተምህሮአቸውንም ከእውነታው ጋር በጥንቃቄ ያገናዘቡ፣ ከዚያም በመነሳት የራሳቸውን ብሔራዊና ቀለማዊ ስሜት ያለዘቡ፣ በመካከላቸው ነበሩ። የአብዛኞቹ ግን ዓይናቸው የተገለጡትና ከችግሮቹ ጋር ፊት ለፊት የተያዩት በየመጡባቸው አገሮች ውስጥ ነው። ከጥርጣሬውና ከጥያቄው ጋር ገና በየግላቸው ይፋጠጣሉ። ከራሳቸውና የራሴ ከሚሉት ነገር ሁሉ ጋር ገና በየግላቸው ይታገላሉ። ወድቀው ወይም ጥለው ገና የየግላቸውን አቋም ይይዛሉ።

ለሁሉም የማስጠንቀቂያው ደወል ተደውሏል። በሦስተኛው ዓለም አገሮች ውስጥ ወንጌል በምዕራባውያን ሚስዮናውያን አማካይነት የሚሠራጭበት ዘመን አብቅቷል። ከእንግዲህ ወዲህ ወንጌል የማሠራጨቱን ሥራ በየአገሮቹ የሚገኙት አማኞች መረከብ አለባቸው። ወንጌላዊ ክርስትና የምዕራባውያን አገሮች እምነት ሆኖ መታየቱ መቆም አለበት። የኮሎኒያሊስቶችና የኢምፔርያሊስቶች የመበዝበዣ መሣሪያ ተደርጎ መቆጠሩ መቅረት አለበት። "ያገሩን ሰርዶ ባገሩ በሬ" እንደሚባለው የወንጌል እውነት በሕዝቡ ዘንድ ስር እንዲሰድድ፣ "መጤ" ተደርጎ እንዳይቆጠር፣ ከምዕራባውያን ሚስዮናውያን መፋታት አለበት። የሕዝቡ ቋንቋ፣ ባህል፣ ስነ ልቦና የራሳቸው በሆነ "የአገር ልጆች" መሰበክ ነው ያለበት።

እንደዚህ ስንል ከምዕራብ አገሮች የሚመጡ ሚስዮናውያን ከእንግዲህ ወዲህ በኢትዮጵያ በሚደረግ የእግዚአብሔር መንግሥት ሥራ ውስጥ የሚያበረክቱት ምንም ዓይነት ድርሻ አይኖርም ማለታችን አይደለም። ዘመኑ ተለውጧል ማለታችን ነው። በቀድሞው ዘመን ወደ ኢትዮጵያ በመጡበት ዓይነት ከእንግዲህ ወዲህ ቢመጡ ተፈላጊነታቸውና ውጤታማነታቸው የቀድሞውን ያህል አይሆንም ማለታችን ነው። ከዚህ ይልቅ የአገሬዋን ቤተ ክርስቲያን ዓቅም በሚያጎለብቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች እንደ መክፈት፣ አሜሞር ስልጠናዎች እንደ መስጠት ባሉ አገልግሎቶች ከጎንዋ ቢቆሙ የበለጠ ይጠቅማሉ ማለታችን ነው። በሌሎችም "የድንኳን ሰፊዎች" አገልግሎቶች (tent makers' ministries) በኢንቨስተርነት ወይም በተቀጣሪነት ቢመጡ ገና ያልተነካ ሰፊ የአገልግሎት መስክ በፊታቸው አለላቸው ለማለት ነው።

እንደዚህ ያለ ቀን መምጣት እንዳለበት ያስተዋሉ አንዳንድ ሚስዮናውያንም ነበሩ። ለምሳሌ የ"ሠራዊተ ክርስቶስ ማህበሩ" ዴቪድ ስቶክስ "እግዚአብሔር ሆይ! የአገሩን ስዎች አስነሳ" እያለ አዘውትረው ይፆሙና ይጸልዩ እንደ ነበረ ከቀደምት ጳንጠቆስጤአውያን አንዱ የሆነውና በጀርመን አገር የሚኖረው ተወልደ ዮሐንስ አጫውቶኛል። ተወልደ ይህንን የሰማው "እማማ ጀማነሽ" ከሚላቸው በአስበ ተፈሪ ከሚኖሩ እህት ነው። በአዋላ የ1958 ዓ.ም. የክረምት ኮንፈረንስ ላይ ካርል ራምስትራንድ ስለ ቤተ ክርስቲያን በሰጡት ተከታታይ ትምህርት ቤተ ክርስቲያን እራስዋን በራስዋ የምታራባ የምትረዳና የምታስተዳድር[17] መሆን እንደሚገባት እንዳስጨበጡአቸው በውጭ አገር የሚሰጉ ድርጅቶች ላይ መደገፍዋን እንዳጣጣሉት፣ ያን ትምህርት ለወጣቶቹ በጊዜው ዓይን ከፋች እንደ ነበረ በኮንፈረንሱ ላ የነበረው ግርማ ተሰማ አጫውቶኛል።

እንደ ዴቪድ ስቶክስና እንደ ካርል ራምስትራንድ ያሉ ጥቂ ሚስዮናውያን የነበሩትን ያህል፣ ስለዚህ ጉዳይ ፈጽሞ አስበው

የማያውቁ፣ ስለ ወደፊቱ ምንም ዓይነት ራእይ ያልነበራቸው፣ የመሠረቷቸውን አጥቢያ አብያተ ክርስቲያን እንደሚገባ ያላደራጁ፣ ከአገሬዎቹ አማንያን መካከል ተተኪ ያላዘጋጁ፣ እንዲያውም ብቅ ብቅ የሚሉትን በስጋት የተመለከቱ፣ ላለመተካት (አድራጊ ሳይሆን ተደራጊ) የታከቱ ብዙ ሚስዮናውያን ነበሩ።

የታሪክ ባለቤት የሆነው እግዚአብሔር ግን በኢትዮጵያ ላይ እንዲሆን የፈቀደው ከመሆኑ ዘጠኝ አመታት ቀደም ብሎ ጳንጠቆስጤአዊውን ሪቫይቫል ላከ። ያም ሪቫይቫል በሁለተኛው ቻፕል ውስጥ የእሁድ አምልኮ ማድረግ ሲጀመር የራሱን ቅርጽና የራሱን አቅጣጫ መያዝ ጀመረ። እንዴት እንደዚህ ወዳለ ውሳኝ ውሳኔ እንደ ተደረሰ ዝርዝሩን አናውቅም። ከላይ ስለ ኮሎኒያሊስቶች ያልናቸው ነገሮች በኢትዮጵያ እውነት አልነበሩም[18]። የሪቫይቫሉ ባለቤት ማለትም መንፈስ ቅዱስ ለሪቫይቫሉ የቀየሰለት ጎዳና ይኸ ስለ ነበረ ነው ብለን ልባችንን ከማሳረፍ በስተቀር ሌላ አማራጭ የሚቀርልን አይመስልም።

የመጀመሪያው ብሔራዊ ጳንጠቆስጤአዊ ኮንግሬስ

በሁለተኛው "ቻፕል" ውስጥ ከተከናወኑትና ሪቫይቫሉን ለዘለቂታው የራሱን ቅርጽና አቅጣጫ ካስያዙት ክንዋኔዎች ሁለተኛው የመጀመሪያው ብሔራዊ ጳንጠቆስጤአዊ ኮንግሬስ ነው። የመጀመሪያውን ብሔራዊ ጳንጠቆስጤአዊ ኮንፈረንስ "ኮንግሬስ" ብዬ የጠራሁት እኔ ነኝ። ኮንፈረንስም፣ ኮንግሬስም "ጉባዔ" ናቸው። ሁለቱም ለሁለቱም ዓይነት ስብሰባዎች ያገለግላሉ - ለመንፈሳዊም ለዓለማዊም። በኮንግሬስ ወስጥ ጉባዔተኞቹ ተወካዮች የመሆናቸው ነገር ትንሽ ጎላ ይላል መሰለኝ።

እነዚያን ጉባዔተኞች "ተወካዮች" ያልኳቸው ግን እኔ አይደለሁም። ከመጀመሪያውም እንደዚያ ነበሩ። ተወካዮች ቢባሉ ይሆን ወይም ተጋባዦች ትክክል ይሆን የነበረው እርግጠኛ አይደለሁም። በአንድ በኩል በዚያ ኮንግሬስ ላይ መክሉን ብሉ የላካቸው በማናቸውም ደረጃ የተደራጀ አካል አልነበረም። በሌላ በኩል የሪቫይቫሉ እንቅስቃሴ ደርሰባቸዋል በሚባሉት ከተሞች ውስጥ ግንባር ቀደም ናቸው ተብለው ነው ተጋብዘው የመጡት። የየከተሞቻቸው ተወካዮች ነበሩ ማለት ነው። ያልተወከሉ ተወካዮች።

የተጋባዦች ቁጥር በትክክል አይታወቅም። ሊመጡ ያልቻሉ ብዙዎች እንደነበሩ ግን እናውቃለን[19]። ከተጋበዙት ውስጥ የመጡት አንድ

መቶ ያህሉ ብቻ ናቸው። እንደ ቢሮ፣ ጸሐፊ፣ ስልክ፣ ፖስታ ሳጥን፣ ባሉ የመገናኛ ዘዴዎች ለመገልገል የሚያስችል ድርጅታዊ አሠራር በሌለበት፣ ከዚያ በፊት ታይቶ፣ የሚያስናፍቅ ትዝታ አስቀርቶ፣ በማያውቅ የመጀመሪያ ጉባዔ ላይ የዚያን ያህል ተወካዮች መገኘታቸው በማናቸውም መመዘኛ ቢሆን ከሚጠበቀው በላይ ነው።

ኮንግሬሱ የተካሄደው ከሐምሌ 28 ጀምሮ ለአራት ተከታታይ ቀናት ነው። ቀን ቀን የሚካሄዱት ስብሰባዎች የጸሎት፣ የአምልኮ፣ የስብከት ነበሩ። ለማንም ክፍት ናቸው። የመጀመሪያ በሆነ ኮንግሬስ ላይ የቀረቡ ከ ሰ ሆናቸው በስተቀር ከወትሮው ብዙ የተለዩ አልነበሩም። እንደ ት ቢት፣ ልሳንና ትርጉም፣ ያሉት እግዚአብሔር ሕዝቡን በመንፈሱ በቀጥታ የሚናገርባቸው መንገዶችም ቢሆኑ በዚያን ጊዜ ያልተለመዱ አይደሉም።

የምሽቱ ጊዜ በአብዛኛው የውይይት ነበር። ተሳታፊዎቹም የአዲስ አበባው ቻፕልና የሌሎች ከተሞች ተወካዮች ናቸው። ተወካዮቹ በያሉበት አካባቢ እግዚአብሔር እያደረገ ስላለው ነገር ሪፖርት ሳይሆን ምስክርነት ይሰጣሉ። ልምዳቸውን ያካፍላሉ። ወንጌልን ስለ ማሰራጨት፣ የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት ለብዙዎች ስለ ማስተዋወቅ፣ ስለ አጋጣሙአቸው ችግሮች፣ ሕብረታቸውን ስለ ማጠናከር፣ ይመካከራሉ። ብዙ ያከራከራቸው ጉዳይ "እንቅስቃሴ" (movement) እንደ ሆንን እንቅር? ወይስ በቤተ ክርስቲያን መልክ እንደራጅ? የሚለው ጥያቄ ነበር። የጉባዔተኞቹን ሁሉ ስምምነት ያገኘ የመሰለው አሳብ ዘቤተ ክርስቲያን መልክ እንደራጅ የሚለው አማራጭ ነው።

ሆኖም በኮንግሬሱ ማብቂያ ላይ ይህንንም ሆነ ጉባዔው የተነጋገረባቸውን ሌሎች ጉዳዮች በተመለከተ የተላለፈ ውሳኔ ወይም በፊርማ የጸደቀ ቃለ ጉባዔ አልነበረም። በቃላት ሳይቀመጡ፣ ለብዙዎች ግን የተገለጡ (ግልጽ የሆኑ) አንዳንድ ነገሮችም ነበሩ። ለምሳሌ በኢትዮጵያ ከእንግዲህ ወዲህ የወንጌል ሥርጭት ከሚስዮናውያን እጅ ወጥቷል። በኢትዮጵያውያን እጅ ገብቷል። ከሚስዮናውያን አራስ ላይ ወርዷል። ኢትዮጵያውያኑ ጫንቃ ላይ ተጭኖአል። አምልኮውና የወንጌል አሠረጫጨት ስልቱ፣ የምዕራባውያኑን ዘይቤ ለቅቆአል። አገራዊ አቅጣጫ ይዟል። ከሁለት አመታት በኋላ ዝማሬውም ያንኑ ፈለግ ተከትሏል።

እንዴት እንዴት እንደሚያደርጉት ንድፉ በእጃቸው ቀርቶ በሀሳባቸውም ውስጥ ገና የለም። አይኑር እንጂ ያንን ኮንግሬስ አጠናቅቀው ከተወካዮቹ አንዳንዶቹ ወደየመጡበት ሲመለሱ፣ ሌሎቹም ወደ አመታዊው የአዋሳ ኮንፈረንስ ሲገሰግሱ፣ በእነዚህ ባለፉት ቀናት ውስጥ፣ በዚያ ኮንግሬስ ላይ፣ እግዚአብሔር አንድ አዲስ ራእይ

እንዳሳያቸው እርግጠኞች ነበሩ። ራእዩ እንዴትና መቼ እውን ይሆናል? ይህ ራእይ ጮቤ ያስረግጣል? ወይስ ያስደነግጣል? ምን ይጠይቃል? ወይስ ምን ያስከፍላል? እነዚህ ወደፊት እያንዳንዳቸው በየመታጠፊያው፣ በየመንታ መንገዱ ላይ ሲደርሱ ለየራሳቸው የሚመልሷቸው ጥያቄዎች ይሆናሉ።

የሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን

በዚያን ዘመን በኢትዮጵያ ስለ ፈነዳው ጳንጠቆስጤአዊ ሪቫይቫል የሚያትት ጽሑፍ ስለ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን ሳያነሳ ቢቀር ሙሉ አይሆንም። ያ ሪቫይቫል በዚያን ጊዜ የነበሩትን አብያተ ክርስቲያን ሁሉ በቀጥታና አዎንታዊ በሆነ መንገድ ነክቷል። ከዚያ በኋላ በአገር ውስጥና ከአገር ውጭ ከተቋቋሙትም አብያተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙዎቹን በተዘዋዋሪ መንገድ ነክቶአቸዋል። የሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን ግን የዚያ ሪቫይቫል የበኩር ልጅ ናት። የዚያ ሪቫይቫል ተዘዋዋሪ ሳይሆን ቀጥተኛ ውጤት ናት። ወደፊት የአገራችንን የቤተ ክርስቲያን ታሪክ የሚጽፉ ሰዎች እስከሚሉና ስለ ሪቫይቫሉም ሆነ የሪቫይቫሉ የበኩር ልጅ ስለ ሆነችው ስለ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን በሰፋት እስከሚጽፉ ድረስ ስለ አመሠራረትዋ ጥቂት ነገር ብሉ ማለፍ ግድ ይሆናል።

የምሥረታው ስብሰባ የተካሄደው ከመጀመሪያው ኮንግሬስ በኋላ ብዙም ሳይቆይ፣ ምናልባትም በዚያው አመት ላይ ነበር። ጳንጠቆስጤአዊው ሪቫይቫል በኢትዮጵያ ካጋጠሙት ውስጣዊ ፈተናዎች የመጀመሪያው የተከሰተው በዚህ ጊዜ ነው። ሪቫይቫሉ ያንን ፈተና አልፎአል? ወይስ በዚያ ፈተና ወድቆአል? ያ ፈተና ሪቫይቫሉን ጠቅሟል? ወይስ ጎድቷል? ተፈታኞቹስ ከዚያ ፈተና ተምረዋል? ወይስ ሳይማሩበት ቀርተዋል? እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ የሚቻልበት የጊዜ እርዝመት ላይ ነው አሁን የምንገኘው። ሆኖም ያ የዚህች መጽሐፍ ዋና ጉዳይ አይደለም። ስላይደለም እነዚህ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊዎች ወደፊት የሚመልሷቸው ጥያቄዎች ይሆናሉ።

ሕጋዊነት ያለው አንድ "ማህበር" ለመመሥረት ያን ጊዜም ቢሆን ዛሬ መሥራቾቹ ማሟላት ካለባቸው ነገሮች አንዱ ለሚመሠረተው ማህበር ስያሜ መስጠት ነው። በዚህ መሠረት የአዲስዋ ቤተ ክርስቲያን መጠሪያ እንዲሆኑ ለምርጫ የቀረቡት "የሰማይ ብርሃን" እና "ጥንቷቲት የእግዚአብሔር ማህበር" የሚሉ ስሞች ነበሩ። "ማህበር" ማለት የተፈለገው በዚያን ጊዜው የኢትዮጵያ መንግሥት ዘንድ "ቤተ ክርስቲያን" የሚለው ስያሜ ተቀባይነት እንደማይኖረው ስለታወቀ ነው። ለነገሩ ዛሬም እንደዚያው ነው።

የመጀመሪያውን ስም ለምርጫ ያቀረቡትን ማንነት አንባቢው ሊገም
ይችላል። አዎ አሁን በዩኒቨርሲቲ ተማሪነትና በሌላ ምክንያት አዲ
አበባ የሚኖሩ የናዝሬት ልጆች ናቸው። ናዝሬቶች ለምርጫ ያቀረቡ
ስም ሳይመረጥላቸው ይቀራል። በምርጫው ያሸነፈውን ሁለተኛው
ስም ያቀረበው የምስረታውን ስብሰባ በሰብሳቢነት የመራው ከበደ ወል
ማርያም ነበር ይባላል። እርሱ ለምርጫ ያቀረበው ስም እንዲመረጥለ
በምርጫው ሂደት ላይ ተጽዕኖ አድርጓል የሚሉ የናዝሬት ልጆ
አጋጥመውኛል።

ናዝሬቶች በዚህ አዝነውና ቅር ተሰኝተው እያሉ ቅሬታቸውን የሚያባ
ሌላ ነገር ተፈጠረ። ማህበሩን በመንግሥት ለማስመዝገብ ጥያ
በሚቀርብበት ጊዜ ማህበሩ የሚንቀሳቀስባቸውን ከተሞች ስም በገርጌ
ማስመዝገብ ያስፈልጋል። አስመዝጋቢዎቹ ግን የሌሎቹን ከተሞ
ስሞች ሲያስመዘግቡ ናዝሬትን ሳይጨምሩ ይቀራሉ። አንዳንዶ
ናዝሬት ያልተጨመረችው በገንጋኤ ነበር ይላሉ። ሌሎች
ናዝሬቶች "ከሰማይ ብርሃን" ውጭ ሌላ ስም እንደማይቀበሉ ስለ ታመ
ሆን ተብሎ ነበር የተተወችው ይላሉ።

በዚያም ሆነ በዚህ ቀድሞውኑ በቋፍ ከነበሩት ናዝሬቶች ብዙዎ
የቀድሞ ስማቸውን እንደ ያዙ ለመቆየት ወሰኑ። ቆይተው
ከሚኖሩበት ጋር[20] ተቀላቀሉ። የ"ጥንታዊት የእግዚአብሔ
ማህበር" እና "የሰማይ ብርሃን" ደጋፊዎች እዚህ ላይ አንዱ ከሌላ
ተለያዩ። አቅባዝጊ ስዩምም እዚህ ላይ ከሁለቱም ተለየ። አቅባዝ
"ሌላ ተጨማሪ ዲኖሚኔሽን ማቋቋም ለምን ያስፈልጋል? ከዚያ ይ
አዲስ ያገኘነውን ይህንን የመንፈስ ቅዱስ እሳት ይዘን ቀድሞ መ
ነበርንባቸው አብያተ ክርስቲያን ብንመለስና ብናቀጣጥላቸው ይሻላ
የሚል አቋም ነበረው። ሀሳቡ ተቀባይነት ሳያገኝ ቀረ። አቅባዝጊ
ከዚያ በኋላ ከጳንጠቆስጤአውያኑ ጋር አልቀጠለም። ወደ ቀድሞ ቤ
ወደ መካነ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ተመለሰ።

የአቅባዝጊ ጥያቄ ግን በዚያ ጊዜ ተነስቶ፣ በዚያ ጊዜ ወድቆ የቀ
ጥያቄ አይደለም። እስከ ዛሬም ድረስ ብዙ ሰዎች የሚያነሱት ጥያ
ነው። ጥያቄውን የሚያነሱትም የሌሎች ዲኖሚኔሽኖች አባላት ብ
ሳይሆኑ የሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን አባላትም ጭ
ናቸው። ጥያቄው የሚነሳባቸው ምክንያቶችም ከአንድ በላይ ናቸው
ከእነዚህም ዋነኛው የዲኖሚኔሽኖች በቁጥር እየበዙ መሄድ በው
ያሉትን የበለጠ ያደናግራል፤ በውስጥ ያሉትንም የባሰ ይከፋፍላል የሚ
ነው። ሊሠራ የተፈለገውን ሥራ ከአንድ ወይም ከብዙ ዲኖሚኔሽኖ
ጋር አብሮ መሥራት እስከ ተቻለ ድረስ ሌላ አዲስ ዲኖሚኔ
መመሥረት ለምን ያስፈልጋል? አስቀድመው የተቋቋሙትን ቤ
በማሳደግ ጊዜ፣ ጉልበትና ወረት (resource) ሳይባክን ሊሠራ

የሚችለውን ሥራ እዚያን ወደ ጎን ትቶ ሌላ አዲስ ተቅዋም በማቋቋም
ለመሥራት መድከም ለምን ያስፈልጋል? የሚል ነው።

ለእዚህ ጥያቄዎች ምናልባት እስከ ወዲያኛውም ድረስ ሁሉንም ወገን
የሚያጠግብ ምላሽ መስጠት አይቻልም ይሆናል። ለአቅባዝጊ ጥያቄ
በጊዜው አሉታዊ ምላሽ ለሰጡት ሰዎች ፍትሐዊ (fair) ለመሆን ግን
የዚያን ጊዜውን ሁኔታ መረዳት ያስፈልጋል። ከመነሻው በቂ ግንዛቤ
ሊያገኙ የሚገባቸው ቢያንስ ሦስት ነጥቦች አሉ። የመጀመሪያው ያ
ሪቫይቫል የራሱን ስብሰባ ማድረግ ከጀመረ በዚያ ጊዜ ሁለት አመታት
ያስቆጠረ መሆኑ ነው። በእዚህ ሁለት አመታት ውስጥ በብዙ
መቶዎች የሚቆጠሩ ወጣቶች ጌታን ተቀብለዋል። በመንፈስ ቅዱስ
ተጠምቀዋል። እጅግ አስደናቂ በሆነ ሁኔታ ሕይወታቸው ፈጽሞ
ተለውጧል። ብዙዎች ደግሞ ተአምራዊ በሆነ መንገድ ከብዙ በሽታ
ተፈውሰዋል። ከአጋንንት እስራት ተላቅቀዋል። እንደዚህ ፍሬአማ
የሆነውን ስብሰባ ማስቆምም ሆነ ለመንግሥት ሳያሳውቁ መቀጠል
የማይቻልበት ደረጃ ላይ ነበር አሁን የተደረሰው።

ሁለተኛውና ሦስተኛው ነጥቦች በአንድነት ሊታዩ ይችላሉ።
ከጳንጠቆስጤአውያኑ መካከል እጅግ አብዛኞቹ የመጡት ከኦርቶዶክስ
ቤተ ክርስቲያን የመሆኑ ጉዳይ አንደኛው ሲሆን፣ ያ ጊዜ
ጳንጠቆስጤአዊነት በወንጌላውያኑ አብያተ ክርስቲያን ዘንድ የኑፋቄ
ትምህርት ተደርጎ የሚታይበት የመሆኑ ጉዳይ ደግሞ ሁለተኛው ነው።
ከእዚህ ሁለት ነጥቦች በመነሳት የእነ አቅባዝጊን ጥያቄ በሌላ ጥያቄ
መመለስ ይቻላል።

ጌታን አምነው ዳግም የተወለዱ ሁሉ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ማደግና
የጌታ ደቀ መዛሙርት መሆን አለባቸው። ከእዝያ ጳንጠቆስጤአውያን
ወጣቶች ውስጥ አብዛኞቹ የመጡባቸው የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንም
ሆነች ወይም ጥቂቶቹ የመጡባቸው ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያን
እነዚህን ወጣቶች ጳንጠቆስጤአዊውን ልምምዳቸውን ሳያስጥሉአቸው
ሊያሳድጉአቸውና ደቀ መዛሙርት ወደ መሆን ሊያደርሷቸው ይችሉ
ነበር ወይ? የእኔ መልስ አይችሉም ነበር የሚል ነው። ወደ ኦርቶዶክስ
ቤተ ክርስቲያን የሚመለሱት እንዲያውም ደህንነታቸውን እንኳን
ጠብቀው ሊቆዩ የመቻላቸው ጉዳይ በጣም አጠያያቂ ነው የሚሆነው።
ወይስ ደህንነት መጠበቅ የሌለበት ነገር ነው?

የእነ አቅባዝጊን ጥያቄ በሌላ መልክ መመልከትና መመለስም ይቻላል።
የሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን በምዕመናን ብዛት ዛሬ
በኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያን መካከል ከቃለ ሕይወት፣
ከመካነ ኢየሱስና ከሕይወት ብርሃን ቀጥሉ በአራተኛነት ደረጃ ላይ ነው
ያለችው[21]። እንደ አንድ ቤተ ክርስቲያን ሆና ባትደራጅ ኖሮ፤

የመጀመሪያዎቹ ምዕመናኗ በጊዜው በዙሪያቸው በነበሩት ወንጌላውያ
አብያተ ክርስቲያን ውስጥ ተውጠው ቀርተው ቢሆን ኖሮ፤ ያ ሪቫይ
በአገራችን የወንጌል ሥርጭትና የቤተ ክርስቲያን ዕድገት ላ
ያሳደረውን ያህል አዎንታዊ ጫና (impact) ማሳደር ይችል ነበር ወይ
የእኔ መልስ አሁንም አይችልም ነበር የሚል ነው።

በሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን ምሥረታ መንፈስ ቅዱ
ያሳየን የአሠራር ሞዴል ጠቃሚነቱ ከእርስዋ በፊት ከተመሠረቱ
ይልቅ ከእርስዋ በኋላ ለሚመሠረቱት ነው የሚሆነው። ለም
ከወንጌል ሥርጭትና ከድርጅት የትኛው ይቀድማል? መመስ
ይቀድማል ወይስ መዋቀር? ወንጌል ሳይሰበክና ኃጢአተኞች ሳይድ
የቤተ ክርስቲያን ተከላ ብሎ ነገር አለ ወይ? የእግዚአብሔር መንግሥ
ሳትሰፋ ቤተ ክርስቲያን እደገች ሊባል ይቻላል ወይ? የእኔ መ
አይቻልም የሚል ነው። ይህም ሞዴል አዲስ ሳይሆን የአዲስ ኪ
ሞዴል ነው። ከኢየሩሳሌም ጀምሮ በይሁዳ፣ በሰማርያ፣ በሲር
በአውሮፓና በእስያ የተመሠረቱት የመጀመሪያዎቹ አብያተ ክርስቲያ
እንዴት እንደ ተመሠረቱ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ እናያለን
በሁሉም ስፍራ የቀደመው የወንጌል ስብከት ሲሆን ያመኑትን ሰ
በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መልክ የማደራጀቱ ሥራ የመጣው ያ
እየተከተለ ነው።

ወደ ተነሳንበት ጉዳይ እንመለስ። "ጥንታዊት የእግዚአብሔር ማህበ
በሚለው ስያሜ ያልተደሰቱት ናዝሬቶች ብቻ አልነበሩም። ስ
በሌሎቹም ምዕመናን ዘንድ ተቀባይነት ያገኘ አይመስልም። ምናልባ
በስሙ አመራረጥ ላይ ናዝሬቶች የነበራቸውን ቅሬታ ወደ ሌላ
ማጋባት ችለው ነበር ይሆናል። ምናልባት ከዚያ ስም የተ
ከመጀመሪያው ጀምሮ አብረው በነበሩ ወንድማማቾች መካ
የደረሰውን መጎዳዳትና መለያየት ስለሚያስታውስ ይሆናል። በዚያ ስ
ለቤተ ክርስቲያንዋ ዕውቅና ለማስገኘት የተደረገውም ሙከራ የመ
ሽታ ሆኖ ስለ ቀረም ጭምር ይሆናል።

እነዚህን ሁኔታዎች ግምት ውስጥ በማስገባት ሊሆን ይችላል
ክርስቲያንዋ ከተመሠረተች ከሦስት አመታት በኋላ ስም ለማውጣት
ስብሰባ መጥራት ያስፈለገው። በዚህ በሁለተኛው ስብሰባ
የተጠቆሙት ስሞች ብዙ ሲሆኑ ዋና ተፎካካሪ ሆነው የቀረቡት
"የሙሉ ወንጌል አማኞች ማህበር" እና አሁንም "የሰማይ ብርሃ
ነበሩ። "የሙሉ ወንጌል አማኞች ማህበር" የሚለው ስም በከፍ
የድምፅ ብልጫ የተመረጠ ሲሆን ስሙን የጠቆመው ኃይሌ ወ
ሚካኤል ነበር ይባላል።

ቤተ ክርስቲያንዋ ከተጠነሰሰችበትና አራቱ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች
ከተከራዩአት "ቻፕል" ጀምሮ የግል ንብረትዋ በሆነ ቤት ውስጥ
መሰብሰብ እስከ ቻለችበት እስከ 1971 ዓ.ም. መጀመሪያ ድረስ ሙሉ
አስራ ሦስት አመታት አልፈዋል። ከእነዚህ አመታት ውስጥ በነፃነት
እና በይፋ መሰብሰብ የቻለችባቸው አመታት ቁጥር በድምሩ ከስድስት
አይበልጥም። በስድስቱ አመታት ውስጥ በጸሎት ቤትነት
ልትገለገልባቸው የተከራየቻቸው ቤቶች በቁጥር ሰባት ነበሩ።
የመጀመሪያው ዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት፣ ሦስተኛው ሁለተኛ
ፖሊስ ጣቢያ፣ አራተኛው አፍንሎ በር፣ ስድስተኛው ያሬድ ሙዚቃ
ትምህርት ቤት አጠገብ ሲሆኑ፣ የተቀሩት ሦስቱ ናዝሬት ትምህርት ቤት
አካባቢ ነበሩ። የመጀመሪያዎቹን ሁለቱንና ስድስተኛውን ሰው ስለ
በዛና ቤቶቹ ስለ ጠበቡ ወድዳ ስትለቅቃቸው፣ ሌሎቹን ግን ተሰድዳና
ተገዳ ነው የለቀቀቻቸው።

የመጀመሪያዎቹ ሽማግሌዎች የተመረጡትና የመጀመሪያው ስም
የወጣው ቤተ ክርስቲያንዋ በሦስተኛው ጸሎት ቤት ውስጥ በነበረችበት
ጊዜ ነው። ዘመኑ 1959 ዓ.ም. ሲሆን በዚያ ጊዜ "ቻፕል" የሚለው
አጠራር እየቀረ፣ "ጸሎት ቤት" የሚለው አጠራር ግን እየተዘውተረ
በመምጣት ላይ ነበር። ከመጀመሪያዎቹ ሰባት ሽማግሌዎች ውስጥ ዘለቀ
ዓለሙ፣ አሰፋ ዓለሙና ቤተ መንግሥቱ ቀደም ሲል እንዳየነው
ከሐረር ሲሆኑ፣ በዚህ ጊዜ ሦስቱም አዲስ አበባ በሚገኘው የአሜሪካን
ሚስዮን ትምህርት ቤት መምህራን ነበሩ። ከበደ ወልደ ማርያም፣
መለሰ ወጉ እና ፋንታሁን ገብሬ ከመርካቶው የፊንላንድ ሚስዮን ሲሆኑ
ፊልጶስ ኬሜሬ ከአዋሳ ፊላደልፊያ ቤተ ክርስቲያን ነበር።

እጅ በመጫን ሥርዓት የመጀመሪያዎቹን ሽማግሌዎች የሹመት ሥርዓት
የፈፀሙት ካርል ራምስትራንድ ነበሩ። ቀደም ሲል እንደ አንድ አዲስ
ቤተ ክርስቲያን የመደራጀት እንቅስቃሴ በተደረገበት ጊዜ ሁለቱም
ጳንጠቆስጤአውያን የሚሰዮን ድርጅቶች እንቅስቃሴውን በስራቸው
የማደረግ ግልጽና የእጅ አዙር ሙከራ አድርገው እንደ ነበረ በጊዜው
የነበሩ ያስታውሳሉ። የመጀመሪያዎቹ ሽማግሌዎች ከተመረጡ በኋላም
ከስዊድን ፊላደልፍያ ሚሰዮን ጥያቄው ቀርቦላቸው እንደ ነበረና
ሽማግሌዎቹም ፈቃደኞች አለመሆናቸውን በፍቅር እንዳስረዱአቸው፣
ይህም ቀጣዩን ግንኙነታቸውን ፈጽሞ እንዳላሻከረው አሰፋ ዓለሙ
ይናገራል።

ሁለተኛው ስም የወጣው ቤተ ክርስቲያንዋ በአራተኛው ጸሎት ቤት
ውስጥ በነበረችበት ጊዜ ሲሆን ዘመኑ 1962 ዓ.ም. ነው። አምስተኛው
ጸሎት ቤት ቤተ ክርስቲያንዋ እስከ ታሪካዊው የነሐሴ 21 ቀን 1964
ዓ.ም. ስደት ድረስ የቆየችበት ነው። ይኸኛውን ስደት በተለይ ለምን
ታሪካዊ እንደምለው በሚቀጥለው ምዕራፍ ውስጥ እናገራለሁ። እነዚህ

ሰባቱ ጸሎት ቤቶች የተጠቀሱት የቤተ ክርስቲያኗ ዋነኛ መሰብሰቢያዎ
ስለ ነበሩ እንጂ ከሁለተኛው ቻፕል ዘመን ጀምሮ፣ በተለይም ደግ
በሦስተኛውና በአራተኛው ጸሎት ቤቶች ዘመን መካከል በተለያዩ ስፍ
የሚጠሩ ሌሎች መለስተኛ ጸሎት ቤቶች በጊዮርጊስ፣ በአቧሬ፣ በኦ
ስልክ፣ በዱሮው አውሮፕላን ማረፊያ፣ በአርበኞች መንገድ፣ በመርካቶ
በተክለ ሃይማኖት፣ በካዛንቺስ፣ በአቃቂ ተከፍተው ነበር። ከእነዚህ
አንዳንዶቹ የምዕመናን መኖሪያ ቤቶች ነበሩ።

አምስተኛው ጸሎት ቤት ጌታን በሙሉ ጊዜአቸው እንዲያገለግሉ
መለኮታዊ ጥሪ የደረሳቸው የመጀመሪያዎቹ የሙሉ ጊዜ ወንጌላውያን
የወጡበት ነው። በጣም ተቀራራቢ በሆነ የጊዜ ልዩነት ከወጡ
መካከል ኃይሌ ወልደ ሚካኤል፣ አሰፋ ዓለሙ፣ ዘለቀ ዓለሙ፣ ከ
ደጉ፣ ምክሩ በቀለ፣ ተክሉ ከበደ፣ አሸናፊ ዘማት፣ መርዕድ ለ
ይገኛሉ። የመጀመሪያዎቹ ሦስቱ ቀደም ሲል ሽማግሌዎችም ስለ ነበሩ
በሙሉ ጊዜ ወንጌላዊነት ሲለዩ፣ ከሽምግልና አገልግሎታቸው
እንዲለዩ ተደርገዋል።

የመጀመሪያዎቹ የቤተ ክርስቲያኒቱ መዘምራንም የተደራጁት በ
ክርስቲያንዋ በዚህ በአምስተኛው ጸሎት ቤት ውስጥ በነበረችበት ዘመ
ነው። የመዘምራኑን ቡድን በማደራጀት ረገድ እስከ ዛሬ ድ
ብዙዎች ስሙን በብዙ ትዝታና በብዙ ፍቅር የሚጠሩት ጌታቸው ም
ነው። ጌታቸው መጀመሪያ ከመርካቶው የፊንላንድ ሚስዮን
ቀጥሎም በሐረር መምህራን ማሰልጠኛ ተቅዋም ውስጥ የነበረ ት
መስካሪ እንደ ነበረ ቀደም ሲል ተመልክተናል። በመድሃኔ ዓ
ትምህርት ቤት መምህር በነበረ ጊዜ ቢሮው ድረስ እየሄደ ሙዚ
ይማር እንደ ነበረ ደበበ ለማ ይናገራል። "አኮርዲዮን አሳ
ይጫወት ነበር" ይላል።

እኔ እስከማውቀው ድረስ በኢትዮጵያ የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲ
ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያዋ አገር በቀል ቤተ ክርስቲያን የሙሉ ወን
አማኞች ቤተ ክርስቲያን ናት። ይህንን የምለው በአንድ ወ
እትብታቸው ከውጭ አገር ከመጡ የሚስዮን ድርጅቶች ጋር ታ
የነበረውን አብያተ ክርስቲያን በምንም ዓይነት ለማሳነስ አይደለ
ሊያንሱም ደግሞ በፍፁም አይችሉም። ወይም ደግሞ አገር በቀ
ቤተ ክርስቲያን ከሚስዮናውያኑ ያገኘችው ምንም ዓይነት ጥቅም የ
ለማለትም አይደለም። በመሠረቱ እንዲህ ብሎ ነገር የለም። ነ
ሁሉ እንዴት እርስ በርሱ እንደ ተያያዘ በዚሁ ምዕራፍ ውስጥ ቀ
ሲል ተጠቅሷል። ይህንን የምለው እውነቱ እንደዚህ ስለሆነ ብቻ ነ
ይህም እውነት የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያን ታሪክ አ
ነው ብዬ ስለማምን ብቻ ነው።

አገር በቀልዋ ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችው በ1959 ዓ.ም. ቢሆንም
እስከ 1984 ዓ.ም. ድረስ ለሐያ አምስት አመታት በኢትዮጵያ ውስጥ
ህጋዊነት አልነበራትም። ህጋዊነት አልነበራትም ማለት ግን ታዋቂነትም
አልነበራትም ማለት አይደለም። በአብዮቱ የመጀመሪያ አመታት
ኢህአፓዎቹን ከጸንጠቆስጤዎቹ ለመለየት ሲባል ለጸንጠቆስጤዎቹ የታወቀ
የመሰብሰቢያ ስፍራ በመንግሥት እንዲሰጣቸው የሆነባቸውን አንድ
ሁለት ከተሞች አውቃለሁ። በአዲስ አበባም በስድስተኛውና
በሰባተኛው ጸሎት ቤቶች በይፋ መሰብሰብ የተቻለው በ1967 ዓ.ም.
መጀመሪያ ላይ ከአዲስ አበባ ፖሊስ ጽሕፈት ቤት በተገኘ ፈቃድ
ነበር። ቤተ ክርስቲያንዋ በአሮጌው አውሮፕላን ማረፊያ አካባቢ
የራስዋን የጸሎት ቤት እንድትሠራበት ቦታ የተሰጣት ታዋቂነት እንጂ
ህጋዊነት ባልነበራት በደርግ ዘመን ነበር።

የጥንትዋ ቤተ ክርስቲያን እስከ 313 ድረስ በሮማ መንግሥት ግዛት
ውስጥ በማናቸውም ስፍራ ታዋቂነት እንጂ ህጋዊነት አልነበራትም።
ለሁለት መቶ ሰማንያ አመታት ያህል ማለት ነው። እነዚያ አመታት
ግን ቤተ ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስና በስደት እሳት እየተንቀለቀለች
በዙሪያዋ ለነበረው ጨለማ ዓለም አንፀባራቂ ብርሃን የሆነችባቸው ነበሩ።
ህጋዊነትን ስትላበስ ግን አንፀባራቂነትዋ እየከሰመ፣ ብርሃንዋም
እየጨለመ ሄዶ በዓለምና በእርስዋ መካከል ምንም ዓይነት ልዩነት
ወዳልታየበት ወደ መካከለኛውና ወደ ጨለማው ዘመን ደረሰች። ዛሬም
ህጋዊነትን ተከትሎ በመምጣት ላይ ያለው የብርሃን መደብዘዝ ያንን
ከስተት ለሁልጊዜም የማይለወጥ ኦሪጂ እውነታ አስመስሎታል።

ደቀ መዛሙርትም በኢትዮጵያ "ጴንጤ" ተባሉ

በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ "ደቀ መዛሙርትም መጀመሪያ
በአንጾኪያ ክርስቲያን ተባሉ" የሚል እናነባለን (11:26) ከዚህ አባባል
"ክርስቲያን" ስለሚለው ስያሜ አንዳንድ ቁም ነገሮችን እንጨብጣለን።
ከምንጨብጣቸውም ቁም ነገሮች የመጀመሪያው "ክርስቲያን" የሚለው
ስያሜ መጀመሪያ የወጣው ከሮማ መንግሥት ጠቅላይ ግዛቶች አንደዋ
በነበረችው በሲርያ ዋና ከተማ በአንጾኪያ መሆኑን ነው። ዘመኑ 44
ገደማ ይሆናል። ከምንጨብጣቸው ቁም ነገሮች ሁለተኛው ይህ ስያሜ
የተሰጠው ለጌታ ደቀ መዛሙርት መሆኑ ነው። የጌታ ደቀ
መዛሙርት ማለት የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ተማሪዎች፣ የእርሱ
ተከታዮች ማለት ነው። ሦስተኛው ቁም ነገር ለደቀ መዛሙርቱ
ይህንን ስም ያወጡላቸው ሌሎች ሰዎች መሆናቸው ነው። "ተባሉ"
ነው እንጂ እራሳቸውን በራሳቸው "ክርስቲያን አሉ" አይልም።

በተመሳሳይ ሁኔታ በኢትዮጵያም በአብዮቱ ዘመን ለጌታ
መዛሙርት አዲስ ስም ወጥቶላቸዋል። ይህም "ጴንጤ" የሚለው ቃ
ነው። ይህ ስም በመጀመሪያ የተለጠፈው በጳንጠቆስጤአውያኑ
ብቻ ነበር። አንዳንድ ወንጌላውያን ክርስቲያኖች እንኳ
ጳንጠቆስጤአውያኑን ወንድሞቻቸውን ለይተው በዚያ ስም ይጠሩአቸ
ነበር። አፋቸውን ሞልተው "እኛ ጴንጤዎች አይደለንም" ይሉ የ
ወንጌላውያን ክርስቲያኖችም ጥቂት አልነበሩም። በኋላ
በሚያስገርም ሁኔታ "ጴንጤ" የወንጌላውያን ሁሉ መጠሪያ ሆኖአ
እግዚአብሔርም እራሱ ስያሜውን ያጸደቀው በሚመስል ሁኔታ ስ
በደረሰበት ሁሉ ልምምዱም እንዲደርስ አድርጓል።

ይህንን ስንል በኢትዮጵያ ያሉ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያን ሁ
ጳንጠቆስጤአዊውን አስተምህሮ ተቀብለዋል ለማለት አይደለ
ጳንጠቆስጤአዊውን አስተምህሮም ሆነ ጳንጠቆስጤአዊውን ልም
ያልተቀበሉት አሉ። በመጽሐፍ ቅዱሳዊነቱ ላይ ግን እ
መጀመሪያው ያለ ተቃውሞ የለም ለማለት ነው። ሁሉ
ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያን፣ ከሞላ ጎደልም እንኳን ቢሆ
በመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ይገለገላሉ ለማለት ነው። በሌላ አነጋ
የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያን ካሪዝማዊ ሆነዋል ለማ
ነው።

ካሪዝማዊውን ተሐድሶ ወደ ኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲ
ለማዳረስ እግዚአብሔር የተጠቀመባቸው መንገዶች ብዙ ናቸ
በጊዜ ረገድ ሁለቱ የአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲ
የመዘምራን ቡድኖች ("ሀ" እና "ጽዮን" የሚባሉት) የመጀመ
ተጠቃሾች ይሆናሉ። በብስራተ ወንጌል ራዲዮ ጣቢያ መዝሙሮቻቸ
ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉ ሊሰሙ የጀመረው ከ1962 ዓ.ም. ገ
ጀምሮ ነው። መንግሥታዊው የኢትዮጵያ ራዲዮ ጣቢያም ሳይ
በሁዳዴ ጾም ወቅት መዝሙሮቻቸውን ያሰማበት፣ የኢትዮ
ቴሌቪዥንም ቡድኑ ሲዘምር ያሳየበት ጊዜ ነበር። ከመዘምራኑ አ
የነበረውን አዲሱ ወርቁን ንጉሠ ነገሥቱ እራሳቸው አስጠርተ
አነጋግረውታል። መዘምራኑ በአዲስ አበባና ከዚያም ውጪ በሚ
የተለያዩ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያን እየተጋበዙ በዝ
አገልግለዋል። ጴንጠቆስጤአዊውንም ሪቫይቫል ሆነ ካሪዝማዊ
ተኃድሶ በኢትዮጵያ ከዳር እስከ ዳር ለማዳረስ መንፈስ ቅዱስ በግ
ቀድምትነት ተጠቅሞባቸዋል።

በዚህ ረገድ ከመዘምራኑ ቀጥሎ ሊጠቀሱ የሚገባቸው ከ1964 ዓ
ጀምሮ በአዲስ አበባው የመካነ ኢየሱስ ሴሚናሪ፣ በላንጋኖ
በናዝሬቱ የመጽሐፍ ቅዱስ አካዳሚ በተከታታይ የተደረጉት የመሪ
ኮንፈረንሶች ናቸው። እነዚህ የመሪዎች ኮንፈረንሶች የተለያዩ

ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያን መሪዎች ዓይን ለዓይን የተያዩባቸው፣
ጎን ለጎን አብረው የተቀመጡባቸው፣ ማዕድ አብረው የቆረሱባቸው፣
በአንድ ቤት ውስጥ አብረው ያደሩባቸው ናቸው። በሁላቸው
የሚሠራውን፣ በሁላቸው የሚኖረውንና የሁላቸው አባት የሆነውን
አንዱን አምላክ አብረው ያመለኩባቸው ናቸው። የኢትዮጵያ
ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያን ሕብረት የተወለደው ከእነዚህ
ኮንፈረንሶች ነው።

በ1969 ዓ.ም. በናዝሬት የመጽሐፍ ቅዱስ አካዳሚ በተደረገው
የመሪዎች ኮንፈረንስ ላይ ከተናጋሪዎቹ አንዱ የነበረው መስፍን ተስፋዬ
የጳንጠቆስጤአውያኑን አስተምህሮና ልምምድ ደግፎ ተናግሮአል ተብሎ
ሊደበደብና ስብሰባውም ሊበተን ነበር። የዚህ ዓይነቱ አክራሪነት ግን
ከዚያ በኋላ ለብዙ አመታት አልቀጠለም።

በ1971 ዓ.ም. መገባደጃ ላይ ነበር ጳንጠቆስጤአውያኑ የአዲስ አበባ
መሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን መጋቢ ዳንኤል መኮንን እና ዘለቀ
ዓለሙ "የመንፈስ ቅዱስ ሳምንት" በሚል መጠሪያ በአዲስ አበባ መካነ
ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን በተዘጋጀ ኮንፈረንስ ላይ እንዲያገለግሉ
የተጋበዙት። ያ ኮንፈረንስ ላዘጋጀቸው ቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን
በአዲስ አበባ ላሉ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያን ሁሉ ለበረከት የሆነ
ኮንፈረንስ ነበር። እንደ ፈውስ፣ አጋንንትን ማስወጣት፣ የዕውቀት
ቃል፣ ያሉት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ያለ ምንም ተጽዕኖ እንዲሠሩ
የተለቀቁበት ኮንፈረንስ ነበር። የመጋቢ ዳንኤልም ስምና ዝና በምድሪቱ
ሁሉ ላይ የወጣው በዚያ ኮንፈረንስ ነው። እርሱ ከአገር እስከ
ወጣበት ጊዜ ድረስ ለሁለት አመታት ያህል ተመሳሳይ ኮንፈረንሶች
በአዲስ አበባና በሌሎችም ከተሞች ሁሉ ተደርገዋል። የመንፈስ ቅዱስ
ስጦታዎች በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያን ዘንድ ተቀባይነት
እንዲያገኙ እነዚያ ኮንፈረንሶች ታላቅ አስተዋጽኦ አድርገዋል።
በሦስተኛነት ልንጠቅሳቸው እንችላለን። ያጠቃቀሳችን ቅደም ተከተል
ግን ከእንግዲህ የደረጃ ቅደም ተከተል አይደለም።

አራተኛው ብዙ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያን በመንግሥት
መዘጋታቸውና አገልግሎታቸውን በህቡዕ ለማካሄድ መገደዳቸው ነበር።
ህቡዓኑ ስብሰባዎች የተለያዩ አብያተ ክርስቲያን አባላት የሆኑትን ምዕ
መናን አቀራረቡአቸው። ስደታቸውንና መጽናናታቸውን፣
አስተምህሮአቸውንና ልምምዳቸውን፣ ጎዘናቸውንና ተስፋቸውን
እንዲጋሩ አደረጉአቸው።

አምስተኛው በ1964 ዓ.ም. አካባቢ የተመሠረተው የወንጌላውያን
ተማሪዎች ህብረት ነው። ሕብረቱ ዲኖሚኔሽን - አቀፍ ነው።
ጳንጠቆስጤአውያኑና ኢጳንጠቆስጤአውያኑ በቡድን በቡድን እየሆኑ

በአንድ ላይ ቃለ እግዚአብሔርን ያጠኑበታል። ይመያየቡታል። የጸልየቡታል። ያ አንዱ በሌላው ውስጥ ያለውን መልካም ነገር እንዲያይና እንዲያደንቅም አደረጋቸው። እነዚህ በትምህርት ቤቶች ሳሉ የሚተዋወቁ አማኞች ወጣቶች በዕድሜም፣ በአገልግሎትም እያደጉ ሄደው በየቤተ ክርስቲያናቸው ወደ መሪነት ደረጃ ደረሱ። በሚመሩአቸውም ማህበሮች መካከል ያለውን የተካረረ አቅዋም ለማርገብ ረዱ። የወንጌላውያን ተማሪዎች ህብረት ሲነሳ ስማቸው አብሮ በበጎ ሲነሳ የሚኖረው የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ ኢየሱስና የወጣቶች ጉዳይ ተጠሪዋ የነበረው ተከስተ ተክሉ ናቸው።

ስድስተኛው በሰባዎቹ የመጨረሻ አመታት ላይ በመካኒሳ እና በእንጦጦ መካነ ኢየሱስ አብያተ ክርስቲያን የፈሰሰው የፈውስ ስጦታ ነበር። በሰባዎቹ መጀመሪያ ላይ በአዲስ አበባ መሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ሆኖ እንደ ነበረው የማናቸውም ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን ስለ ቤተ ክርስቲያኑ ስምና ስለ አገልጋዩ ማንነት ምንም ግድ ሳይኖራቸው የእግዚአብሔርን በረከት ፍለጋ ወደ መካኒሳና ወደ እንጦጦ ጎረፉ። በዚህ አገልግሎት እግዚአብሔር በእጅጉ ከተጠቀመባቸው አገልጋዮች መካከል በመካኒሳ ቁስ ተስፋዬ ዲነግዴ እና ወንጌላዊ መኮንን ነገሪ፣ በእንጦጦ ቁስ በልዕና ሳርካ የሚጠቀሱ ናቸው። እነዚህና ሌሎችም አገልጋዮች እየተጋበዙ በየክፍላተ አገሩ በማገልገላቸው ይህ በረከት ወደ ብዙዎች ደርሷል።

ሰባተኛው የወንጌላውያን ክርስቲያን ሠራተኞች ሕብረት ነው። እንደ ተማሪዎቹ ሕብረት ሁሉ ይኸኛውም በተለያዩ መንግሥታዊ ድርጅቶች ውስጥ የሚሠሩ የተለያዩ ዲኖሚኔሽን አባላት የሆኑ አማኞች ሕብረት ነው። ከ1972 ዓ.ም. ገደማ ጀምሮ ቀስ በቀስ እያደገ ብዙዎችን ለማቀፍና ለማቀራረብ የበቃ ሕብረት ነው።

በመጨረሻም ለኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያን ካሪዝማዊ መሆን በአዲስ አበባና በክፍላተ አገር፣ በመሪዎችና በምዕመናንም ደረጃ ትልቅ አስተዋጽዖ ያደረገው ዎርልድ ቪዥን ኢንተርናሽናል የተባለው አብያተ ክርስቲያን አጋዥ የሆነ ድርጅት ነው። ከ1968 ዓ.ም. ጀምሮ በአገር አቀፍ ደረጃ የመሪዎችን ኮንፈረንሶች፣ በኋላም በክፍላተ አገር ደረጃ በተለያዩ ስፍራዎች ዲኖሚኔሽን አቀፍ የሆኑ የምክርና የመንቃቂያ ስብሰባዎችን በማዘጋጀትና ፋይናንስ በማድረግ፣ የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያን ሕብረት በጽሕፈት ቤት ደረጃ ከተቋቋመም በኋላ በሚያስፈልገው ሁሉ ከጎኑ በመቆም ለአብያተ ክርስቲያናት መቀራረብና መቀባበል ሰፊ እገዛ አድርጓል።

የኢትዮጵያን ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያን ካሪዝማዊ ለማድረግ እግዚአብሔር የተጠቀመባቸው መንገዶች እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ብቻ

አይደሉም። ምናልባት ከተጠቀሱት ይልቅ ያልተጠቀሱት በቁጥር ይበዙ ይሆናል። ቃለ እግዚአብሔር አንባቢያን ማህበርን፣ ታላቁ ተልዕኮን፣ ለቅሶውንና ጋብቻውን ሁሉ ሳይቀር ነው እግዚአብሔር የተጠቀመባቸው። እነዚህን ሁሉ ለመጥቀስ የዚህች ዓይነት መጽሐፍ ገጾች አይበቁም።

"ከእነዚህ ድንጋዮች . . . ልጆች"

ይህንን ረዥም ምዕራፍ ከማቴዎስ ወንጌል 3:9 ላይ በተወሰደ በዚህ ጥቅስ ለመደምደም እፈልጋለሁ። መጥምቁ ዮሐንስ ይህንን የተናገረው የአብርሃም ዘር በመሆናችው ትምክህት ለወጠረቸው አይሁዳውያን ነበር። እግዚአብሔር ከሰዎች መካከል ብቻ ሳይሆን ከፈለገ ከድንጋዮችም መካከል ለአብርሃም ልጆች ሊያስነሳለት እንደሚችል ነው የሚነግራቸው። በቅዱስ ቁጣ ተሞልቶ ነው የሚናገራቸው።

እግዚአብሔር "ወዳጄ" ብሎ ከጠራው (ኢሳ 41:8 ያዕ 2:23) ከአብርሃም መወለዳቸው ትምክህተኞች ሳይሆን ትሑቶች፣ በራሳቸው ማንነት የሚመጻደቁ ሳይሆን በእግዚአብሔር ቸርነት የሚያኑቁ ሊያደርጋቸው ይገባ ነበር። ከአብርሃም ለመወለድ እነርሱ ያደረጉት ትንጣት አስተዋፅኦ አልነበረምና። ዮሐንስ እንዳስጠንቀቃቸውም እግዚአብሔር ከአረማውያን መካከል ለአብርሃም ዕልፍ አዕላፋት ልጆች አስነሳለት። እንዲያውም የእስራኤል ዘር በሙሉ እውነተኞች እስራኤላውያን እንዳይደሉ፣ የአብርሃምም ዘር የሆኑ ሁሉ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው ማለት እንዳልሆነ ብዙም ሳይቆይ ግልጽ ሆነ (ሮሜ 9:6-7)።

ሰው የአብርሃምም ሆነ የእግዚአብሔር ልጅ የሚሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን እንጂ ከአብርሃም በመወለድ አለመሆኑ የአዲሱ ኪዳን መሠረታዊ አስተምህሮ ነው።

> በእምነት በኩል ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁና . . . አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም፤ ባሪያ ወይም ጨዋ ሰው የለም፤ ወንድም ሴትም የለም፤ ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና። እናንተም የክርስቶስ ከሆናችሁ እንኪያስ የአብርሃም ዘር እንደ ተስፋውም ቃል ወራሾች ናችሁ (ገላ 3:26-29)።

ጳውሎስ ይህንን የሚጽፈው ለገላትያ አብያተ ክርስቲያን ነው። እነርሱም አይሁዳውያን ሳይሆኑ አረማውያን ነበሩ። የክርስቶስ

በመሆናቸው ምክንያት የአብርሃም ዘር ሆነዋል። ያም ብቻ አይደለም የክርስቶስ በመሆናቸው የእግዚአብሔርም ልጆች ሆነዋል።

በ1958 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ስለ ፈንዳው ጰንጠቆስጤአዊ ሪቫይቫ ያወሳሁበትን ይህንን ምዕራፍ በዚህ ጥቅስ የምደመድመው ያለምክንያ አይደለም። ለዚህ ሪቫይቫል የባለቤትነትም እንኳን ባይሆን የምክንያትነ ሚና የተጫወተው ማነው? የሚል ጥያቄ በየጊዜው በየቦታው ሲነ ስለምሰማ ነው። በመልስነት ስማቸው ተደጋግሞ የሚጠራው የስዊድ ፊላደልፍያ ቤተ ክርስቲያን ሚስዮን፣ የፊንላንድ ጰንጠቆስጤአ ሚስዮን፣ የናዝሬት ሰማይ ብርሃን ወጣቶች ማህበር፤ በአራት ኪሎ በጋ ቤት በመከራየት የጸሎት ስብሰባ የጀመሩት አራቱ የዩኒቨርሲ ተማሪዎች፣ ከፊንላንድ ሚስዮን በመገንጠል ከአራት ኪሎዎቹ ተማሪዎ ጋር የተቀላቀሉት ወጣቶች፣ የሐረር መምህራን ማሠልጠኛ ተቅዋ ተማሪዎች ናቸው።

ያንን ሪቫይቫል ከእነዚህ ውስጥ ከአንዱ ወይም ከሌላው ጋር የሚያያይ ሦስት የኮሌጅ መመረቂያ ጽሑፎችን፣ አንድ ሁለት መጻሕፍትን ጥቂት መጽሔቶችን አንብቤአለሁ። ሪቫይቫል እንደ አልማዝ ባለ ብ ገጽታ ነው። ባለ ብዙ ህብር ነው። አንድ ሰው ሊያይ፣ ሊያውቅ ወይም ንክኪ ሊኖረው የሚችለው ከብዙ ገጽታዎቹ ውስጥ ከአን ወይም ከጥቂቶቹ ጋር ብቻ ነው። በዚህ ምክንያት ነው በጽሑፍ ይሁን በንግግር የሪቫይቫሉን ሙሉ መልክ መዳሰስ የማይቻለው ስለዚህም ምዕራፍ ይህ እውነት ነው። ሌላው ሰው ያየውን ካየበ አቅጣጫ ብቻ ለምን አየኸው? ከማለት ሳይታይ የቀረውን ለማሳየ መሞከር የሚሻል ይመስለኛል።

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በመጠኑ ለማሳየት እንደሞከርኩት ከላይ ስማቸ የተጠቀሰው የሚስዮን ድርጅቶችና ቡድኖች በዚህ ሪቫይቫል ውስ የየራሳቸው ድርሻ ነበራቸው። በሪቫይቫሉ ውስጥ ድርሻ የነበራቸ እነዚህ ብቻ ግን አልነበሩም። ሪቫይቫሉ አምስት ሙቶ አመታ ሊያስቆጥር የደረሰው የተሐድሶው እንቅስቃሴ አካል ነው የተሐድሶው እንቅስቃሴም በመጀመሪያ የእግዚአብሔር አሳብ ነው ቀጥሎም የብዙ ውስጣዊና ውጫዊ መስተጋብሮች ውጤት ነበር።

በኢትዮጵያ የተከሠተው ጰንጠቆስጤአዊ ሪቫይቫል ማንም ግለሰብ ቡድን ወይም ድርጅት ያሰበው፣ ያቀደውና ያቀነባበረው አልነበረም እግዚአብሔር ያኔ ያደረገውን ሁሉ ያለማንኛቸውም ሊያደርገው ይች ነበር። ገና ሊያደርገው ያቀደውንም ያለማንኛችንም ሊያደርገ ይችላል። እግዚአብሔር ባደረገው ደስ ይበለን። የሚመጣው እንዳያልፈን እንማጠነው። በተመጻዳቂዎቹም እስራኤላውያን ላ የደረሰው ለተምሀርታችን ይሁንን።

አራት

የግርጌ ማስታወሻዎች

1 ስለዚህ ቅደም ተከተል ለማወቅ በዚህ መጽሐፍ በአስረኛው ምዕራፍ ውስጥ "ስድስተኛዋ ቤተ ክርስቲያን" የሚለውን ርዕስ ይመልከቱ።

2 Oskarsson, Gunilla Nyberg. "Svensk Pingstmisson i Ethiopien 1959-1980" Pmu, Sweden, 1997

3 ቀዳማዊ ኃአይለ ሥላሴ "ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ 1ኛ መጽሐፍ" ብርሃንና ሠላም የቀንሥ ማተሚያ ቤት 1965 ዓ.ም. ገጽ 74-75

4 ሩት ራምስትራንድ ለአርባኛው አመት የአዋሳ የሕይወት ብርሃን ቤተ ክርስቲያን ምስረታ የላኩት መልዕክት። ለበዓሉ ከተዘጋጀና "ሕይወት ብርሃን" ከተሰኘ መጽሔት ላይ የተወሰደ። ነሐሴ 1992 ዓ.ም.

5 ሩት ራምስትራንድ _____

6 ሚስስ ሩት ራምስትራንድ (የካርል ራምስትራንድ ባለቤት) ለአዋሳ ሕይወት ብርሃን ቤተ ክርስቲያን መጋቢ፣ ለመጋቢ ጌቱ አያሌው እንደነገሩት።

7 የኃይለ ሥላሴ ዘመንዋ ኢትዮጵያ በጠቅላይ ግዛቶች የተከፋፈለች ነበረች። የደርግ ዘመንዋ የተከፋፈለችው በክፍላተ አገር ሲሆን የኢህአዴግዋ ደግሞ በክልሎች ነው። በዚህ ቦታ "ከአስራ አራቱም ጠቅላይ ግዛቶች" ይጎርፉ ነበር ማለት "ከብዙ ቦታ መጥተዋል" ለማለት እንጂ የግድ ከአስራ አራቱም የመጡ ሰዎች ነበሩ ለማለት አይደለም።

8 Emmanuel Abraham "Reminiscence of my Life". Lunde Forlag, Oslo, Norway 1995 pp. 254

9 በ1951 ዓ.ም. የተመሠረተና በኢትዮጵያ አርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሥር የተደራጀ የወጣቶች መንፈሳዊ ማህበር ነው። በሰባዎቹ ውስጥ ደርግ አፈረሰው።

10 Engelsviken, Tormod. "Molo Wongel: A Documentary Report on the Life and History of the Independent Pentecostal Movement in Ethiopia." The Free Faculty of Theology, Oslo, Norway (ያልታተመ) ገጽ: 10-11

11 ሩት ራምስትራንድ _____

12 Lindsay, Gordon. "William Branham, A Man Sent From God" (ዘመኑ አልተጠቀሰም) pp 215

13 "The Voice of Healing" ከ1948 አጋማሽ ገደማ ጀምሮ በጎርደ ሊንድሲይ የሚታተም ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በአሜሪ የፈነዳውን የፈውስ ሪቫይቫልና አገልጋዮቹን ለዓለም በማስተዋወቅ ረገ ብዙ አስተዋጽኦ ያደረገች ወርሐዊ መጽሔት::

14 "ከኒሻ" የትግርኛ ቃል ሲሆን ትርጓሜው "የፈለሰ" ማለት ነው መጀመሪያ ላይ ስያሜው የተሰጠው ክርስትናቸውን ከኦርቶድክስ ወ ወንጌላዊነት ለቀየሩ ኤርትራውያን ነው::

15 "ቻፕል" የእንግሊዝኛ ቃል ሲሆን በትምህርት ቤት፣ በሆስፒታል፣ ወይ በሌላ ስፍራ ሰዎች ለአምልኮ የሚገናኙበት አነስ ያለ ቤት ወይም ክፍ ነው::

16 "ሠራዊተ ክርስቶስ ማህበር" BCMC ወይም Bible Church Mer Missionary Society በኢትዮጵያ ላለው አገልግሎቱ ሚስዮናውያ ያወጡለት ስም ነው:: ዲ.ኤ በሚል ማህፀረ ስም በ1940ዎቹ መጨረ በ1950ዎቹ መጀመሪያ አመታት በጣም በጠራ አማርኛ የሮሚን ብራውያንን፣ የአንደኛ ቆሮንቶስን፣ የአንደኛ ጴጥሮስንና የኤፌሶ መጻህፍት ትርጓሜ የጻፉልን ዴቪድ ስቶክስና "ምስክረ ብርሃ የተሰኘውን በኢትዮጵያ የመጀመሪያውን መንፈሳዊ መጽሔት በ194 ዓ.ም. የጀመረችው ዶሪስ ቤንሰን የዚህ ሚስዮን አባላት ነበሩ::

17 Self propageting, self supporting, self governing ማለት ነው ሙሉ ወንጌሉቱ ህብረቶቻቸውን ወደ አጥቢያነት የሚያሳድጉት እ ቅርብ ጊዜ ድረስ በእነዚህ መመዘኛዎች መሠረት ነው::

18 "እውነት አልነበሩም" ያልኩት ኢትዮጵያ እንደ ብዙዎቹ የአፍሪቃ አገ ቅኝ ተገዥ ስላልነበረች ነው::


19 Engelsviken, Tormod. _____ ገጽ 24

20 ሚኖናይት ሚስዮን ከ1941 ዓ.ም. ጀምሮ ከአዲስ አበባ አንስቶ በምሥ ኢትዮጵያ ወንጌል በማስራጨት፣ የትምህርትና የጤና ግልጋሎት በመስ በእጅጉ ያገለገለ የሚስዮን ድርጅት ነው:: የመሠረታቸው አብ ክርስቲያን በኢትዮጵያ "መሠረተ ክርስቶስ" በመባል የሚታወ ናቸው::


21 ከኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያን ጽ/ቤት የተገኘ የጁን, 2000 አሐዝ:: አብያተ ክርስቲያኑ በጠራ መንገድ ሬኮርድ ለመያዝ የሚያስችላቸው ሁኔታ በኢትዮጵያ ገና ስለሌለ የዚህ አሐዝ አስተማማኝነት በጸሐፊው ግምት አጠራጣሪ ነው::




ቪተጋበርግ የሚገኘው የክሰል ቤተ ክርስቲያን




ሉተር "ጽሑፉን" የሰጠፈበት የክሰል ቤተ ክርስቲያን መግቢያ



“አዙላ ጎዳና 312”



የ1958 ዓ.ም. የአሞኅሉ ኮንፈረንስ ተሳታፊዎች (በመጀመሪያው ረድፍ ዳር ዳር የቆሙት ማትሰን ዘሊ እና አማሃ ቾቾ ናቸው)



አራቱ ወጣቶች የተከራዩት የመጀመሪያው ቻፕል (1958 ዓ.ም.)



መቶሉ (1957 ዓ.ም.)

የምስክር ወረቀት


ነሐሴ ፴ ቀን ፲፱፻፶፮ ዓ. ም. ፊላደልፊያ ሚስዮን አዋሳ ።

ስም አቶ ማርያ ተሰማ

ወ/ሮ

ወ/ት

ከነሐሴ ፱ ቀን ጀምሮ እስከ ፣ ነሐሴ ፴ ቀን ፶፮ ዓ. ም. በአዋሳ ሐይቅ አካባቢ በሚኖረው የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት የተሰጠውን ትምህርት በሚገባ ፈጽሟል /ለች



CERTIFICATE

This is To Certify That

Mr. Mrs. Miss GIRMA TESSEMA

Has Successfully Finished
The Training In The

BIBLE TRAINING CENTER

Held In The Lake Awassa, August, 1966
Lake Awassa Sept. The 4th 1966
Philadelphia Church Mission

Rev. Jos D. Mattsson-Boze. Instructor

Rev. C. Omaka. Instructor

REV. 3:7-13

Karl Ramstrand. Mission Director



ደብረ ብርሃን መምህራን ማሠልጠኛ ተቅዋም (1958 ዓ.ም.)

አምስት

"ትንቢትን አትናቁ"

አምስተኛውና ስድስተኛው ምዕራፎች የዚህች መጽሐፍ መካከለኛ ምዕራፎች ናቸው። መካከለኛነታቸውም በቁጥር ብቻ ሳይሆን ባዘሉአቸውም ሀሳቦች ጭምር ነው። በመጀመሪያዎቹ አራት ምዕራፎች ውስጥ ያነሳናቸው ቁም ነገሮች ሁሉ በሚቀጥሉት ሁለት ምዕራፎች ውስጥ ለምናነሳቸው ቁም ነገሮች እንዲያዘጋጁን የታቀዱ ነበሩ። ቀጥለው ባሉት ሁለት ምዕራፎች ውስጥ የምናነሳቸው ቁም ነገሮች ሁሉ ደግሞ በመጨረሻዎቹ አራት ምዕራፎች ውስጥ ለምናነሳቸው ቁም ነገሮች እንዲያዘጋጁን የታቀዱ ናቸው።

በቀደሙት አራት ምዕራፎች ውስጥ ካየናቸው እውነቶች የተነሳ በሚቀጥሉት ሁለት ምዕራፎች ውስጥ የምናገኛቸውን እውነቶች መረዳትና መቀበል ይቀልልናል። እኛርሱን ስንረዳና ስንቀበል በዙሪያችን እየሆኑ ያሉትን ታሪካዊ ክስተቶች ከእግዚአብሔር አጠቃላይ ዕቅድ አንፃር እንደገና መተርጎም (re-interpret ማድረግ) እንችላለን። በመጨረሻዎቹ አራት ምዕራፎች ውስጥ ለምናያቸውም እውነቶች እራሳችንን እናዘጋጃለን። ከራሳችንም አልፈን ሌሎችን የተዘጋጁ እንዲሆኑ እናግዛቸዋለን። ይኸም ይህች መጽሐፍ የተጻፈችበት ዋና ዓላማ ነው።

ለመሆኑ እግዚአብሔር በቅዱስ መንፈሱ የተናገረው ነገር ምንድነው? የዚህ የአምስተኛው ምዕራፍ ርዕሰ ነገር ይኸ ነው። እግዚአብሔር በቅዱስ መንፈሱ የተናገረው ነገር ስንል ግን ጳንጠቆስጤአዊው ልምምድ ወደ ቤተ ክርስቲያን ከተመለሰ በኋላ ባሉት አንድ መቶ አመታት ሙሉ እና በዓለሙም ሁሉ የተናገረውን ሁሉ ማለታችን አይደለም። እግዚአብሔር በቅዱስ መንፈሱ የተናገረው ነገር ስንል ስለ ኢትዮጵያ የተናገረው ነገር ማለታችን ነው። ስለ ኢትዮጵያም ስንል ስለ ጠባብዋ ኢትዮጵያ ማለታችን ነው።

የመጀመሪያው መድብል

የቅዱስ መንፈሱ ድምፅ በአጠቃላይ ወደ ቤተ ክርስቲያንም ሆነ በተለይ ወደ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የተመለሰው በጰንጠቆስጤአዊው ሪቫይቫል አማካይነት እንደ ሆነ ቀደም ሲል ደጋግመን አንስተናል። ጰንጠቆስጤአዊው ንፋስ በኢትዮጵያ ከነፈሰ ወዲህ ባሉት ሰላሳ ምናምን አመታት ውስጥ ስለ ኢትዮጵያ የተነገሩትን ትንቢቶች በሁለት መድብሎች ከፍለን እናያቸዋለን። የመጀመሪያው መድብል ከ1957 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ 1979 ዓ.ም. ገደማ ድረስ ባሉት ሐያ ሦስት ያህል አመታት ውስጥ የተነገሩትን ትንቢቶች ሲያጠቃልል ሁለተኛው መድብል ደግሞ ከ1980 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ 1990 ዓ.ም. ድረስ ባሉት አስራ አንድ አመታት ውስጥ የተነገሩትን ትንቢቶች ያጠቃልላል።

ትንቢቶቹን እንደዚህ በጊዜ ከፋፍሎና በሁለት መድብሎች ስር አሰባስቦ ማየት ያስፈለገው በሁለት ምክንያቶች ነው። አንደኛ በሁለቱ ጊዜያት ውስጥ የተነገሩት ትንቢቶች ምንም እንኳን በብዙ ረገድ ተመሳሳይነት ቢኖራቸውም ጉልህ የሆነ ልዩነት ደግሞ ይስተዋልባቸዋል። ሁለተኛም የመጀመሪያዎቹ ከዘመዳዊው የአገዛዝ ሥርዓት መውደቅና ከኮሙኒስታዊው ሥርዓት በእግሩ መተካት ጋር የተያያዘ ነገር ሲኖራቸው የኋለኞቹ ግን ከኮሙኒስታዊው የአገዛዝ ሥርዓት መውደቅና በእግሩ ከሚተካው ሥርዓት ጋር የተያያዘ ነገር አላቸው። አሁን ከመጀመሪያው መድብል ውስጥ ሦስት ትንቢቶችን በናሙናነት እንመለከታለን።

> የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ፣ እሳት በባህር ተጭኖ በሰሜን ወደ አገርህ ገቢ . . በሰሜን ታላቅ ዕልቂት ይሆናል. . . የወንድም ሰይፍ በወንድሙ ላይ ይሆናል. . . የሚመጣውን ኃይል አትቋቋሙትም . . . በፊቱ እንደ ምናምን ናችሁ . . . ሕዝቡ ወደ እኔ ቢመለስ ግን እኔ እመልሰዋለሁ. . . እኔን ካልመለስኩት ወዮላችሁ. . . ብዙ ይሆች ይጠፋሉ . . . ለደሆች ጸልዩ . . . ከሦስት ሺህ አመታት በፊት ባሪያዬን ራቁትህን ሁን፣ ወደ ኢትዮጵያም ምድር ሂድ አልኩት. . . በዚያን ጊዜ የነበረው አውራችሁ የባሪያዬን ቃል አልሰማም. . . አሁንም ላለው አውራችሁ ባሪያዬን ላክሁለት. . . ግን የባሪያዬን ቃል አልሰማም. . . አሁንም ባሪያዬን እልክለታለሁ. . . የባሪያዬን ቃል ሰምቶ ራሱን ካላዋረደ ወዮ ለእርሱ፣ ወዮ ለቤተሰቡ፣ ወዮ ለዳኞቻችሁ. . . በዋና ከተሞቻችሁ በየመንገዱ የደም ጎርፍ፣ የሬሳ ክምር ይሆናል።

ይኸ ትንቢት በመጀመሪያ የተነገረው በ1957 ዓ.ም. በናዝሬት ነው። ከዚያ በኋላ በሙሉ ወይም በከፊል በአዋሳ፣ በአዲስ አበባና በሌሎችም ቦታዎች ተደጋግሞአል። የሚቀጥለው ደግሞ መጀመሪያ የተነገረው በ1958 ዓ.ም. በአዲስ አበባ በመጀመሪያዋ ቻፕል ውስጥ ነው።

> በዓለም ዙሪያ እበትናችኋለሁ. . . ወንጌልን ታሳርሳላችሁ።

ሦስተኛው የተነገረው በ1959 ዓ.ም. በናዝሬትና በባህር ዳር ከተማ ነው።

> በአገራችሁ የድቅድቅ ጨለማ ጊዜ አለ። . . . አትፍሩ. . . ከድቅድቁ ጨለማ በኋላ ለእናንተ እኔን ለምትፈሩ የጽድቅ ፀሐይ ትወጣላችኋለች፣ ፈውስም በክንፎችዋ ውስጥ ይሆናል፤ እናንተም ትወጣላችሁ፣ እንደ ሰባ እንቦሳም ትፈነጫላችሁ፤ በምሠራበት ጊዜ በደለኞች ከእግራችሁ ጫማ በታች አመድ ይሆናሉ።

በእነዚያ ሐያ ሦስት ያህል አመታት ውስጥ ትንቢት የተነገረባቸው ቦታዎች በጣም ብዙ ናቸው። እንዲያው በደፈናው ጰንጠቆስጤአውያኑ ለጸሉት በሚሰበሰቡበት ቦታ ሁሉ ይነገር ነበር ማለት ይቀላል። የመልዕክቶቹ ይዘት ግን የቦታዎቹንና የተናጋሪዎቹን ያህል ብዙና የተለያየ አልነበረም። በሁሉም ውስጥ የሚደጋገሙ ጥቂት ዋና ጉዳዮች ነበሩ። እነዚህም ከላይ በናሙናነት በተጠቀሱት ትንቢቶች ውስጥ ቁልጭ ብለው የሚታዩት ናቸው።

- በኢትዮጵያ ላይ ታላቅ ዕልቂት ይሆናል። ይህም ዕልቂት ደሀውን ህዝብ ብቻ ሳይሆን ንጉሡን እራሳቸውን፣ መሳፍንቶቻቸውንና መኳዋንንቶቻቸውንም አይምርም።
- ይህን ዕልቂት ሊመልሰው የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ነው። እግዚአብሔርም ዕልቂቱን የሚመልሰው ንጉሡና ሕዝቡ በንስሐ ወደ እርሱ የተመለሱ እንደሆነ ብቻ ነው።
- ኢትዮጵያውያን ወደ ዓለም ሁሉ ይበተናሉ። ይህም መንጌል የሚሠራጭበት መንገድ ይሆናል።
- በኢትዮጵያ ላይ የድቅድቅ ጨለማ ጊዜ አለ። ከጨለማው በኋላ እግዚአብሔርን ለሚፈሩ የጽድቅ ፀሐይ ትወጣላቸዋለች፣ እነርሱም በጣም ደስተኞች ይሆናሉ።

ሁሉን ፈትኑ

እነዚህን ትንቢቶች ያናገረ በእውነት እግዚአብሔር ነው ወይ የተናገርዋቸው ሰዎች በእውነት ከእግዚአብሔር ሰምተው ነው ወይ የተናገርዋቸው? አዎን ከተባለ ለዚህ ማረጋገጫው ምንድነው መጽሐፍ ቅዱስ “ትንቢትን አትናቁ፣ ሁሉን ፈትኑ፣ መልካሙን ያዙ፣ ከማናቸውም ዓይነት ክፉ ነገር ራቁ” ይላል (1ኛ ተሰ 5:20-22)። ስለዚህም ከላይ ያየናቸው ትንቢቶች በአንድ በኩል መና የለባቸውም፤ በሌላም በኩል ከእግዚአብሔር ለመሆናቸው ሳንፈትናቸው ዝም ብለን ልንቀበላቸው አይገባንም። ይህንንም ለማድረግ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ትንቢቶች ከሚፈተኑባቸው የተለያዩ መፈተኛዎች ሦስቱን ብቻ በተግባር እናውላለን።

እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ወደፊት ሊሆኑ ስላሉ ነገሮች የሚነገ ትንቢቶች ከእግዚአብሔር መሆናቸው ከሚታወቅባቸው መንገዶች አን የተነገሩት ትንቢቶች የተፈፀሙ እንደሆነ ነው።

> አንድ ነቢይ የሚናገረው የትንቢት ቃል ከእግዚአብሔ ያልተሰጠ መሆኑን በምን ለይተን እናውቃለን? በማለት ትደ ይሆናል። አንዳች ነቢይ በእግዚአብሔር ስም ትንቢት ተና ቃሉ ሳይፈፀም ቢቀር ያ ትንቢት ከእግዚአብሔር የተሰ አይደለም። ያም ነቢይ ትንቢቱን የተናገረው በገዛ ሥልጣ ስለሆነ ልትፈሩት አይገባም (ዘዳ 18፡ 21-22)።

ይኸ የመጀመሪያው መፈተኛ ነው። በዚህ መፈተኛ ሲፈተኑ ከላ ያየናቸው ትንቢቶች ሁሉም ተፈጽመዋል። ንጉሡና ሕዝቡ ወ እግዚአብሔር አልተመለሱም። እግዚአብሔርም ዕልቂቱ አልመለሰውም። በምድሪቱ ላይ ከንጉሥዋ አንስቶ ወደ ታች እስ እንስሳትዋ ድረስ ሳይቀር በገፍ ፈስሶአል። በሽብሮችና በጦርነቶ አንድ ትውልድ የወደመው ይኸኛው የትንቢቶች መድብል በሚሸፍነ ዘመን ነው። ዓለሙን በሙሉ ያንቀጫጨው፣ ከዚያም በፊት ታይ ለማይታወቅ የረድኤት አገልግሎት ያነሳሳው፣ በብዙ ሰዎች አእም ውስጥ ኢትዮጵያንና ረሃብን ስመ ሞክሼዎች አድርጎ ያስቀረው፣ የክፍ ዘመኑ ታላቅ ረሀብ የተከሠተው በዚሁ ዘመን ነው።

እነዚህ ትንቢቶች በተነገሩበት ጊዜ ከአገራቸው ውጭ የሚኖ ኢትዮጵያውያን በቁጥር በጣም ጥቂቶች ነበሩ። ለከፍተኛ ትምህር በስኮላርሺፕ ወደ ተለያዩ አገሮች የሄዱ፣ እንዲሁም በዲፕሎማቲ የሥራ መስኮች የተሠማሩ በቁጥር ቢበዛ ከጥቂት ሺዎች የማይበልጡ ነበሩ። “ለምሳሌ በ1962 ዓ.ም. በአሜሪካ ድህረ ምረቃ ትምህርት

የሚከታተሉት ኢትዮጵያውያን ቁጥር ሰባት መቶ ነው ተብሎ ይገመት ነበር”[1]። ያ ዘመን ኢትዮጵያውያን ያለ ቅድሚያ የመግቢያ ቪዛ ወደ አንዳንድ አገሮች መግባት የሚችሉበት ነበር። ሆኖም አንዳንዶች በሄዱባቸው አገሮች እንዲቀሩ ሲለመኑ እንኳን አሻፈረን እያሉ የሚመለሱበት ነበር። በሰባዎቹ መጨረሻ አመታት ላይ ግን በስደት ከአገራቸው ውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በሚልዮኖች ይቆጠሩ ነበር። ዛሬ ኢትዮጵያውያን የሌሉባቸው የታወቁ አገሮች ምናልባት ቢኖሩ እንኳን በጣት የሚቆጠሩ መሆን አለባቸው።

ኢትዮጵያውያን በየደረሱበት ሁሉ ለአምልኮ ይገናኛሉ። ኢትዮጵያውያን ባሉበት ቦታ ሁሉ ትንንሾችም ቢሆኑ የኢትዮጵያውያን ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያን ወይም መንፈሳዊ ህብረቶች አሉ። ከአባላቱም ከመቶ ዘጠና እጅ በላይ የሚሆኑት ጆሮቻቸው ለወንጌል እውነት የተከፈቱት ከአገራቸው ከወጡ በኋላ ነው። ከቻይናውያን፣ ከኮሪያውያን፣ ከናይጄርያውያንና ከጋናውያን በስተቀር በዚህ ረገድ ኢትዮጵያውያኑን የሚመስል የሌላ የብዙ አገር ህዝብ የለም እስከሚባል ድረስ ብዙዎቹን ያስገረመ ነገር ነው። እርግጥ የወንጌል ማዳረሱ ሥራ እስካሁን በጉልህ እየተካሄደ ያለው በኢትዮጵያውያኑ በራሳቸው መካከል ነው። ሆኖም በአንዳንድ አካባቢዎች ይህም ሁኔታ እንኳን እየተለወጠ ነው። ለውጡም እየጨመረ እንጂ እየቀነሰ እንደማይሄድ ነው የሚጠበቀው።

በኢትዮጵያ የድቅድቅ ጨለማ ጊዜ የነበረ መሆኑም አያከራክርም። የሚያከራክረው ምናልባት የጨለማው ጊዜ አልፎአል ወይስ ገና ነው? የጽድቅስ ፀሐይ አሁን ወጥታልናለች ወይስ ገና ናት? የሚለው ይሆናል። በኢትዮጵያ የእምነት ነፃነት የተለቀቀበት እንደ ኢህአዴግ ዘመነ መንግሥት ያለ ሌላ ዘመነ መንግሥት ያልነበረ መሆኑ እውነት ነው። አርቶዶክሳዊው ክርስትና የመንግሥት ሃይማኖት መሆኑ በህገ መንግሥት ደረጃ ያበቃለት በወታደራዊው/ሶሻሊስታዊው ዘመነ መንግሥት ቢሆንም ይህ ግን በተግባር ሊታይ የጀመረው በኢህአዴግ ዘመነ መንግሥት ነው። “ክርስቲያን ነን” የሚሉ የኢትዮጵያ መንግሥታት ለወንጌል ስብከትና ለወንጌል እምነት የነፈጉትን ነፃነት የኢህአዴግ መንግሥት ለሚመራበት የዴሞክራሲ መርህ በመገዛት መስጠቱ ከማስደነቅ ያልፋል። ይህንን ክስተት ብዙዎች እንደ የጽድቅ ጸሐይ መውጣት ቢቆጥሩት አያስከድም አይባልም። ሆኖም ይኸ የበለጠ እውን የሚሆነው በሚመጣው ሪቫይቫል ነው።

ሁለተኛው መፈተኛ የትንቢቱ መፈፀም ወይም እውነት ሆኖ መገኘት ሰዎችን የሚመራቸው ወደ እውነተኛው አምላክ ነው ወይስ ወደ ባዕዳን አማልክት? የሚል ነው።

ነቢይ ወይም ህልም አላሚ ነኝ የሚል አንዳች ሰው ተአ
ወይም አስደናቂ ነገር አደረጋለሁ ይል ይሆናል። ይህን
የሚያደርገው ከዚህ በፊት ወደማያውቃቸው ባዕዳን አማል
ሊመራችሁ አስቦ ሊሆን ይችላል። እርሱ የተናገረው
እውነት ሆኖ ቢገኝ እንኳን ኩሎ አትስሙት (ዘዳ 13፡1-2)

ትንቢቶች መፈፀማቸው ብቻውን ከእግዚአብሔር ለመሆናቸው
ማረጋገጫ አይሆንም። የትንቢቱ መፈፀም የሚያስከትለው ውጤ
ምን እንደሆነ መመርመር አለበት። ሰው ኃጢአተኛነቱን እንዲገነዘ
ከኃጢአቱም ንስሐ እንዲገባና ስለ ኃጢአቱ በሞተለት በኢየሱ
ክርስቶስ እንዲያምን ይገፋፋዋል? ከኃጢአቱ ንስሐ የገባውና በኢየሱ
ክርስቶስ ያመነው ሰው በዕለት ከዕለት ሕይወቱ ከኃጢአት እየራ
ክርስቶስን እየመሰለ እንዲኖር ያበረታታዋል? ወይስ በተቃራኒ
ሕይወቱን እግዚአብሔር በቃሉ ከሰጠው መመሪያ ውጭ እንዲመ
ያደፋፍረዋል? ሰውን ወደዚህ ወደ መጨረሻው የአንዋንዋር ዘይቤ (
style) የሚመራ ትንቢት በትክክል ቢፈፀምም እንኳን ከእግዚአብሔ
ሊሆን አይችልም።

ከኢትዮጵያ በስተቀር የክርስቲያን አገር፣ ከኢትዮጵያም መንግሥ
በስተቀር የክርስቲያን መንግሥት፣ ከኢትዮጵያም ሕዝብ በስተ
ክርስቲያን ህዝብ፣ ከኢትዮጵያም ክርስትና በስተቀር እውነተኛ ክርስ
የትም የሌለ ለሚመስላቸው ብዙ ሚልዮን ኢትዮጵያውያን " . .
ሕዝቡ ወደ እኔ ቢመለስ . . ." ማለት አብዛኛው ሕዝብ እስከዚ
ጊዜ ድረስ ከእግዚአብሔር ጋር አልነበረም ማለት ነው። አብዛኛ
ክርስቲያን ነኝ ባይ ኢትዮጵያዊ ስለ ማርያም፣ ስለ ታቦት፣
መላእክት፣ ጻድቃን ሰማዕታት ስለሚላቸው ስለ ብዙ ሰዎ
የሚአውቀውን ያህል ለኃጢአቱ ይሞትለት ዘንድ ሰው ስለ ሆነ
አምላክ አለማወቁ እውነት ነው። ከሚያውቀውም ከጥቂቱ ብዙ
በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያልተጻፈ፣ በቃለ እግዚአብሔር ያልተደገ
ነገር ነው። እንደዚህ ዓይነቱን ሕዝብ በንስሐ ወደ እግዚአብሔ
ተመለስ ማለት ከባዕዳን አማልክት ተመለስ ማለት ነው። ቅዳ
ድፍረት የተሞላበት እውነተኛ ትንቢት እንጂ ሐሰት ሊሆን አይችልም

ሦስተኛው መፈተኛ በ"ቅዱስ መንፈሱ" በኩል የመጣልን የትንቢ
ቃል በእጃችን ከሚገኘው ከእግዚአብሔር ቅዱስ ቃል ጋር ይታረቃ
ወይስ ይቃረናል? የሚል ነው። ከላይ ያየናቸው ትንቢቶች ሁሉ
ከመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ጋር የሚታረቅ እንጂ የሚቃረን ነ
የለባቸውም። የመጀመሪያውን ትንቢት በተመለከተ በምድሪቱ ላ
ሊመጣ ስላለው ክፉ ነገር እግዚአብሔር ለንጉሡ በቅድሚያ ማሳወቁ
ሕዝቡም በንስሐና በእምነት ወደ እርሱ እንዲመለስ መጠየቁ እን
መጽሐፍ ቅዱስ ቃል ነው። በናዝሬት ትንቢቱን የተናገረው ወጣት

ነቢይ እግዚአብሔር ኢሳይያስን ወደ ኢትዮጵያ ንጉሥ ልኮት እንደ
ነበረ የሚናገረውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ገና አያውቀውም ነበር
ይላሉ (ኢሳ 20)።

የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት "ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ፤ ወንጌልንም
ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ" ተብለዋል። ታላቁ ተልዕኮ ከቦታ ወደ ቦታ
መሄድን ይጠይቃል። የመሄጃው ምክንያትና የመሄጃው መንገድ ግን
ይለያያል። በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ ስንመለከት የጥንቶቹ
ደቀ መዛሙርት ወደ ዓለም ሁሉ የሄዱት በውድ ብቻ ሳይሆን በግድም
እንደ ነበረ እናገኛለን። ጳውሎስ ወደ ሮም የተጓዘው ታስሮ ነው።
ፊልጶስ ወደ ሰማርያ የሄደው ሸሽቶ ነው። ጴጥሮስ ወደ ቂሣርያ
የወረደው ታዝዞ ነው። ኢትዮጵያውያንም ወደ ዓለም ሁሉ
የተበተኑት በተለያዩ ምክንያቶች ነው። ስለዚህ የኢትዮጵያውያን
በየምክንያቱ ወደ ዓለም ሁሉ መበተን ለወንጌል መሠራጨት መንገድ
መክፈቱ ትክክል ነው።

የመጨረሻው ትንቢት እንዳለ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ነው (ሚል 4፡2-
3)። ያንን ትንቢት በሦስቱም መፈተኛዎች ፈትነነዋል።
በአንዳቸውም የመውደቅ አዝማሚያ አላየንበትም። ስለዚህም
ከእግዚአብሔር ነበረ ብለን እንደመድማለን።

እውን ጃንሆይ ባያውቁ ነው ወይ?

በዚህ ርዕስ ስር የምጽፈውን ነገር የምጽፈው ከዚህች ዓለም ከተለዩ
እሩብ ምዕት አመታት ባለፋቸው ንጉሥ ላይ ለመፍረድና ሌሎችም
እንዲፈርዱባቸው ለማነሳሳት አይደለም። ንጉሡ ለአገራቸውና
ለህዝባቸው ስለ አደረጉዋቸው ወይም ስለ አላደረጉዋቸው ነገሮች
መናገር የሚፈልግ ማናቸውም ሰው በመጀመሪያ ንጉሡ ወደ ሥልጣን
የመጡበትን ዘመን መመርመርና ያንን ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት
ይኖርበታል። ዛሬ ስለ አገር አስተዳደር፣ ስለ ልማት፣ ስለ ሌሎችም
ብዙ ጉዳዮች በምናውቃቸው እውቀቶች መስፈርትነት ንጉሡን
ለመገምገም መሞከር ፍትሐዊ አይሆንም። እንደ ሁላችንም ንጉሡም
የዘመናቸው ውጤት ናቸው። በዘመናቸው በነበረው ሁኔታ ነው
መመዘን ያለባቸው።

በአስተሳሰባቸው ዘመናቸውን የቀደሙ አንዳንድ ሰዎች አልፎ አልፎ
በታሪክ መድረክ ላይ ብቅ ብለዋል። በእኔ አስተያየት ተፈሪ መኮንን
እንደዚህ ካሉት ሰዎች መካከል አንዱ ነበሩ። ዘመናዊ ትምህርት
በኢትዮጵያ እንዲስፋፋ ያደረጉት ጥረት ብቻ እንኳን ይህንን ከብር

ያሰጣቸዋል ባይ ነኝ። ከአርባ ሦስት አመታት በላይ በንጉሥ ነገሥትነት ዙፋን ላይ ቆይቶ ከሰማንያ አምስት በመቶ በላይ የሆነውን ያገሩን ሕዝብ ከመሐይምነት ጨለማ ማውጣት ስለ አልቻለ ንጉሥ እንዴት እንደዚህ ያለ አስተሳሰብ ይኖርሃል? ልባል አችላለሁ።

ለዚህ መልሴ ሁለት ነው። አንደኛ ንጉሡ የዚያን ያህልም ማድረግ የቻሉት ዘመናዊውን ትምህርት ለክርስትና ሃይማኖት፣ ለአገር ባህል፣ ለመልካም ነገር ሁሉ ፀር እንደ ሆነ ከሚያምኑና ከሚቃወሙ መሳፍንት፣ መኳንንት፣ ባላባቶች፣ የሃይማኖት አባቶችና ወላጆች ጋር ብርቱ ትግል እያደረጉ ነው። ልጆቻቸውንም ቢሆን በተለያየ ዘዴ እያባበሉ ነው ያስተማሯቸው። ሁለተኛ ኢትዮጵያ ዘመናዊ ትምህርት በዘለቃቸው አውሮፓውያን በትኝነት አልተገዛችም። የሆነችውን ሁሉ የሆነችው በአብዛኛው በራስዋ እየተፍጨረጨረች ነበር።

በዚህ ርዕስ ስር የምጽፈውን የምጽፈው የሆነውን ነገረ አውቀን ትምህርት እንድንወስድበት ነው። እግዚአብሔር በታሪክ ውስጥ፣ በአንድ አገር ደረጃ፣ ሥራውን ሲሠራ ከሚከተላቸው መለኮታዊ መርሆዎች አንዱን ወይም ሁለቱን አስተውለን ወደፊት የምናደርገውን ሁሉ በጥንቃቄ እንድናደርግ ለማሳሰብ ነው።

መንፈስ ቅዱስ በሐዋርያው ጳውሎስ አፍ “. . . እስራኤል ባያውቁ ነው ወይ?” የሚለውን ወሰጀ ነው ለመጨረሻው የኢትዮጵያ ንጉሥ ያዋልኩት (ሮሜ 10:19)። በሮሜ መልዕክት ውስጥ ከዘጠኝ እስከ አስራ አንድ ድረስ ያሉት ሦስት ምዕራፎች የሚናገሩት ስለ እስራኤል ነው። እግዚአብሔር እስራኤልን በሁለት ሰዎች በአብራምና በሦራ ጀምሮ ብዙ ሚልዮን እስክትደርስ ድረስ ያበዛት፣ በግብፅና በከነዓን አገሮች፣ በተስፋና በሀጣ ሥርዓቶች፣ ለሁለት ሺህ አመታት የመራትና ያስተማራት፣ ለመሲህዋ መምጣት ሊያዘጋጃ ት ነበር። እርስዋ ግን መሲህዋ በመጣ ጊዜ ልታውቀውና ልትቀበለው አልቻለችም። እንዲያውም ገድላ አስወገደችው።

ለምን ይሆን ያልተቀበለችው? ምናልባት ስላልተነገራት ወይም ስላልሰማች ይሆን?

> ሳያምኑበት እንዴት ሊጠሩት ይችላሉ? ስለ እርሱ ሳይሰሙ እንዴት ያምናሉ? የምስራቹን ቃል የሚያበስርላቸው ሳይኖር እንዴት ይሰማሉ? (ሮሜ 10:14)።

መንፈስ ቅዱስ በጳውሎስ ብዕር ሆኖ የሚያነሳቸውን እነዚህን ጥያቄዎች እዚያው በሌላ ጥያቄ ይመልሳቸዋል። “ባይሰሙ ነው ወይ?” ይላል (10:18)። የለም፣ መስማትስ ሰምተዋል። እንግዲያው “ባያውቁ ነው ወይ?” የሰሙት ባይገባቸው ነው ወይ? የሰሙትን ባይረዱት ነው

ወይ? ማለቱ ነው። የለም መረዳትስ ተረድተዋል። ታዲያ ለምን ላይቀበሉት ቀሩ? አመፀኞች ስለሆኑ ነው የሚል መልስ ነው የሚሰጠው። “ቀኑን ሁሉ ወደማይታዘዝና ወደሚቃወም ሕዝብ እጄን ዘረጋሁ” (10:21)። የእስራኤል ችግር አለመስማት ወይም የሰማችውን አለመረዳት ሳይሆን የሰማችውን እና የተረዳችውን አለማመን ነበረ።

በኢትዮጵያም የሆነው ልክ እንደዚያ ይመስለኛል። እግዚአብሔር በምድራቱ ላይ ሊመጣ ስላለው ዕልቂት ለንጉሡ ደጋግሞ አስታውቆአል። “. . . ባሪያዬን ላክሁለት፣ ግን የባሪያዬን ቃል አልሰማም. . . አሁንም ባሪያዬን እልክለታለሁ. . . የባሪያዬን ቃል ሰምቶ ራሱን ካላዋረደ . . .” ማለት እግዚአብሔር ንጉሡን የተናገራቸው አንድ ጊዜ ብቻ አልነበረም ማለት ነው። እስከሚገባቸው ጊዜ ድረስ ተናግሮአቸው ነበር ማለት ነው። ሁል ጊዜ እንደሚያደርገው በቂ ጊዜና በቂ ዕድል ሰጥቶአቸው ነበር ማለት ነው። አንድን መልዕክት በተለያዩና በማይተዋወቁ ሰዎች በኩል በተደጋጋሚ ልኮላቸው ነበር ማለት ነው።

ለምን ይሆን እግዚአብሔር መልዕክተኞቹን ወደ ሌላ ወደ ማንም ሳይሆን በቀጥታ ወደ ንጉሡ የላከው? ለምሳሌ የሕዝቡ መንፈሳዊ መሪ ወደ ነበሩት ወደ ፓትሪያርኩ ለምን አላከም? ለምንስ ይሆን ንጉሡ መልዕክቱን እንዲሰሙት ብቻ ሳይሆን እንዲያምኑትና በተግባርም እንዲተረጉሙት የጠበቀባቸው? በሦስት መሠረታዊ ምክንያቶች ይመስለኛል። አንደኛ ንጉሡን እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ አንግሦአቸዋል። የሕዝቡ እረኛ አድርጎአቸዋል። እግዚአብሔርን ቢታዘዙት ሕዝቡን ያተርፋሉ። እምቢ ቢሉት ደግሞ ብቻቸውን ሳይሆን ሕዝቡን የዘው ይጠፋሉ። የሕዝቡ ዕጣ ፈንታ የሚወሰነው በንጉሡ እግዚአብሔርን መስማት ወይም አለመስማት፣ በንጉሡ ለእግዚአብሔር መታዘዝ ወይም አለ መታዘዝ ነው።

ሁለተኛ ስለ ጳንጠቆስጤአዊው ክርስትና በዚያን ጊዜ የንጉሡን ያህል ሰፊ ግንዛቤ የነበረው ሌላ ሰው በኢትዮጵያ አልነበረም። ስለ ጳንጠቆስጤአዊው ክርስትና በማወቅ ንጉሡ የአርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን አባቶችና መምህራን ብቻ ሳይሆን ጳንጠቆስጤአውያኑን አራሳቸውን በብዙ አመታት ይቀድሟቸዋል። ንጉሡ ከወንጌላውያን አማኞች ጋር ብቻ ሳይሆን ከጳንጠቆስጤአውያን አማኞችም ጋር የረዥም ጊዜ ንክኪ ነበራቸው። ኋላ ላይ ከእነዚህ ንክኪዎች ውስጥ አንዳንዶቹን እጠቅሳቸዋለሁ።

ሦስተኛ ንጉሡ በሥጋዊ ነገር ብቻ ሳይሆን በሃይማኖታዊውም ነገር ሞምር የአገሪቱ ከፍተኛው ባለ ሥልጣን ነበሩ። እግዚአብሔር

የላከላቸውን መልዕክት ወደ መሳፍንቱና ወደ መኳንንቱ ብቻ ሳይሆ
ወደ አርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አባቶችም ጭምር ማድረስ ይች
ነበር። በተወሰነ ደረጃም እንኳን ቢሆን ሕዝቡን ለንስሐ ማስከተ
ይችሉ ነበር። ያም ቢቀር፣ ወይም ደግሞ ከዚያ ጋር በተጓዳ
በጳንጠቆስጤአውያኑ ላይ ከመንግሥትና ከመንግሥትዋ ቤተ ክርስቲያ
የተነሳውን ስደት ማስቆም ይችሉ ነበር።

እግዚአብሔር ያልሰጣቸውን አልጠየቀባቸውም። ከማንም ቢ
እግዚአብሔር ያልሰጠውን አይጠይቅም። ብዙ ከሰጣቸው ከእነ
ደግሞ ብዙ ይጠይቅባቸዋል (ሉቃ 12፡48)። ስለ እርሱ አሠራ
በዚያ ዘመን ማንም ያላገኘውን ግንዛቤ እንዲያገኙ ዕድል ሰጣቸው
እውነት እንደሆነ የተገነዘቡትን ያንን ለማድረግ የሚችሉበትን፣ ከፍተ
ሥልጣን አቀዳጃቸው። በዙሪያቸው ባሉት መሳፍንት፣ መኳንን
የቤተ ክርስቲያን አባቶች ዘንድ ከመመለክ ጋር መተካከል የሚቃጣ
መታዘዝና መሸቆጥቆጥ ጨመረላቸው። ይህንን ሁሉ ካደረገላቸ
በኋላ መልዕክተኞቹን ደጋግሞ ላከባቸው። የጠበቀውን ምላሽ
አላገኘም።

ጃንሆይ እና ወንጌላዊው ክርስትና

> አንድ ሰው የቱንም ያህል ጥበበኛ ወይም የቱንም ያህል ኃ
> ቢሆን፣ ያለ እግዚአብሔር መሪ እንደ ሌለው መርከብ ነው
> . ስለዚህም ክርስቲያኖች ሆይ! እንኳሳና የሐዋርያትና የጥን
> ክርስቲያኖች መለያ በነበሩት ትጋትና ታማኝነት እናገልግ
> ወንድሞቻችንን እና እህቶቻችንንም ሕይወትን አትረፍ
> በመስበክ ብቸኛ ወደ ሆነው ወደ መድኃኒታችን ወደ ኢየ
> ክርስቶስ እንምራቸው[2]።

የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ኦክቶበር 26
1966 በርሊን ከተማ ለተሰበሰበው ዓለም አቀፍ የወንጌል ሥርጭ
ኮንግሬስ ካደረጉት የመክፈቻ ንግግር የተወሰደ ነው። ያ ኮንግ
ከአንድ መቶ አገሮች የመጡ በቁጥር አንድ ሺህ ሁለት መቶ የሚ
ወንጌላውያን ክርስቲያኖች የተሳተፉበት ነው። የኮንግሬሱ መሪ ሃ
"አንድ ዘር፣ አንድ ወንጌል፣ አንድ ተልዕኮ" የሚል ሲሆን ያ
ስብሰባ የጠራው የቢሊይ ግራሃም ኤቫንጀሊስቲክ አሶሲየሽን ነበር።

ከንጉሡ በመቀጠል የኮንግሬሱ የክብር ሊቀ መንበር የነበሩት ዶክ
ቢሊይ ግራሃም ባደረጉት ንግግር

> የወንጌልን መክር የመሰብሰቡ ሥራ ሁል ጊዜ አጣዳፊ ነ
> የሰዎችና የአገሮች ፍጭሚ ሁል ጊዜ በመወሰን ላይ ነው።

> እያንዳንዱ ትውልድ ወሳኝ ነው። እያንዳንዱም ትውልድ
> ቁልፍ ሚና ይጫወታል። ስለ አለፈው ትውልድ ሙሉ
> ኃላፊነት የለብንም። ስለሚቀጥለውም ትውልድ ሙሉ
> ኃላፊነት አንሸከምም። ዳሩ ግን የራሳችን የሆነ ትውልድ
> አለን። በተሰጡን ዕድሎች እንዴት እየተቀምንባቸውና
> ኃላፊነቶቻችንን እንዴት እንደሚገባ እየተወጣናቸው እንዳለን
> በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት ተጠያቂዎች እንሆናለን[3]።

በቢሊይ ግራሃም አፍ እግዚአብሔር በቀጥታ ለኢትዮጵያው ንጉሥ
እየተናገረ የነበረ ይመስለኛል። ጃንሆይ የወንጌል ሥርጭትን
በሚመለከት ያንን አስደናቂ ንግግር በበርሊን ባደረጉበትና የዶክተር
ቢሊይ ግራሃምን ንግግር ባዳመጡበት በዚያው አመት ነበር በደብረ
ዘይት ከተማ በጳንጠቆስጤአውያኑ ላይ ድብደባና መንገላታት
የደረሰባቸው። በአዲስ አበባም ሦስተኛው ቻፕል በመንግሥት ትዕዛዝ
ሲዘጋ ከዚያ ኮንግሬስ በኋላ አንድ አመት ከመንፈቅ አልሞላም ነበር።

የበርሊኑ ኮንግሬስ በዓለም አቀፋዊ ይዘቱ ከዚያ በኋላ እንጂ ከዚያ
በፊት ተወዳዳሪ አልነበረውም። ከዚያ በኋላ በ1974 በሉዛን (ስ
ዊትዘርላንድ) በ1989 በማኒላ (ፊሊፒንስ) እና በሌሎችም ስፍራዎች
ከበርሊኑ ኮንግሬስ በእጅጉ የሚበልጡ ኮንግሬሶች በተመሳሳይ ዓላማ
ተደርገዋል። አንዳቸውም ግን በአንድ የአገር መሪ የመክፈቻ ንግግር
ተደርጎላቸው አልተከፈቱም። የበርሊኑን ስብሰባ የኢትዮጵያው ንጉሥ
በአካል ተገኝተው በንግግር የከፈቱት በአጋጣሚ ነበር? በፍፁም ሊሆን
አይችልም። ሉዓላዊ ሥልጣን ያለው እግዚአብሔር በሚገዛው ዩኒቨርስ
ውስጥ ስለ መንግሥቱ በምድር መስፋፋት እንዲነጋገር የተጠራው ያ
ጉባዔ ይመራ የነበረው በአጋጣሚ ነው ማለት ለእኔ ይከብደኛል።

በወንጌላዊው ክርስትናና በጃንሆይ መካከል ንክኪ ሊሆን የጀመረው ግን
በበርሊን አልነበረም። ንጉሡ ለወንጌል ስብከት ከምዕራብ አገሮች ወደ
ኢትዮጵያ ከሚመጡ ሚስዮናውያን ጋር መገናኘትና መወዳጀትም
የጀመሩት ከበርሊን ሃምሳ አመታት ቀደም ሲል የኢትዮጵያ መንግሥት
አልጋ ወራሽ ሆነው ከተሾሙበት ጊዜ ጀምሮ ነበር። ለምሳሌ
ከተወዳጁ ሐኪምና ከስመ ጥሩው ሚስዮናዊ ከዶክተር ቶማስ ላምቤ
ጋር የተገናኙት በአልጋ ወራሽነታቸው ጊዜ ነበር። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ
ንጉሡና ወንጌላዊው ክርስትና ያልተቋረጠ ንክኪ ነበራቸው።
ከእነዚህ ንክኪዎች አንዱን ብቻ ልጥቀስ።

"የሪቫይቫሉች ምድር" በተባለችው በዊልስ በምልጃ አገልግሉቱ በዓለም
ዙሪያ በእጅጉ የሚጠቀስ ሪስ ሆዌልስ የተባለ ሰው ነበር። ሪስ ለደሀ
ወላጆቹ ከሦስት እህቶቹና ከሰባት ወንድሞቹ ጋር ስድስተኛ ልጅ ነበር።
ምንም እንኳን በዘመኑ ሀግ ዕድሜው አስራ ሦስት አመት ያልሞላ
ታዳጊ ተቀጥሮ እንዳይሠራ የተከለከለ ቢሆንም ሪስ ግን በአስራ ሁለት

አመት ዕድሜው ትምህርቱን አቋርጦ ሥራ ለመቀጠር ተገደ
ሪስ በቀን ለአስራ ሁለት ተከታታይ ሰዓታት እየሠራ ከሆኑ ለመሰወር
ሲባል ቀጣሪው ደመወዙን የሚከፍለው በትልቅ ወንድሙ ስም ነበር።

የሪስ አያቶች በ1859 በዊልስ ፈንድቶ በነበረው ሪቫይቫል ጊዜ ነበር
ጌታን የተቀበሉትና ህይወታቸው የተለወጠው። ወላጆቹም ቢሆኑ
ልጆቻቸውን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጻፉ ታሪኮችን እያነበቡላቸው
በእግዚአብሔር ፍርሃት ነበር ያሳደጉአቸው። ሆኖም ሪስ የክርስቶስ
የማዳን ሥራ ወለል ብሎ የበራለት የተሻለ ሥራ ፍለጋ ወደ አሜሪካ
ሄዶ በነበረበት ጊዜ ነው። ዕድሜው ገና ሐያ አምስት፣ በአሜሪካም
የቆየው ገና ሁለት አመት ብቻ እና በዚህም ጊዜ ውስጥ ብዙ ገንዘብ
ማግኘት ጀምሮ የነበረ ቢሆንም ክርስቲያን በሆነ ጊዜ ግን ወደ ዊልስ
ለመመለስ ቁርጥ ውሳኔ አደረገ። የተመለሰበትም አመት ዝነኛው
የዊልስ ሪቫይቫል የፈነዳበት 1904 ነበር።

የዊልስ ሪቫይቫል ጰንጠቆስጤአዊ ሪቫይቫል አልነበረም። በአስራ
ስምንተኛውና በአስራ ዘጠነኛው ምዕት አመታት የተከሰቱት "የቅድስና
ንቅናቄዎች" (holiness movements) አካል ነበር። ይህም ንቅናቄ
የጰንጠቆስጤአዊው ሪቫይቫል አዋላጅ ነበር። የቅድስናው ንቅናቄ
በጣም የሚያስቀና የመንፈስ ቅዱስ ኃይልና ምሪት፣ የወንጌል ስርጭት፣
የሕሙማን ፈውስ፣ የቅድስና ሕይወት፣ የጸሎትና የምልጃ ጉልበት
ታይቶበታል። ሪስ ዊልስ ወደዚህ ዓይነቱ መንፈሳዊ ልምምድ
ውስጥ የገባው በ1906 የበጋ ወራት በተካፈለው አንድ ስብሰባ ላይ
ነበር።

ሪስ ስለዚያ ልምምዱ ሲናገር እንዲህ ይላል፦ ". . . ከዚያ በፊት
መንፈስ ቅዱስ ልክ እንደ ኢየሱስ የራሱ ሕልውና እንዳለውና መጥቶ
በሰው አካል ውስጥ መኖር እንዳለበት አልተገነዘብኩም ነበር። ቤተ
ክርስቲያን ለሁለት ሺህ አመታት አብሯት ካለው ከመንፈስ ቅዱስ
ይልቅ ለሰላሳ ሦስት አመታት ብቻ በምድር ላይ ስለ ኖረው ስለ
ክርስቶስ የበለጠ ታውቃለች። እኔና በሪቫይቫሉ ውስጥ ያለን
ብዙዎቻችን መንፈስ ቅዱስ በስብሰባችን ወቅት ብቻ የሚመጣ ይመስለን
ነበር። ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረ ጊዜ በራሱ ሥጋ ውስጥ መኖር
እንደ ነበረበት ሁሉ መንፈስ ቅዱስም በሰው አካል ውስጥ መኖር
እንዳለበት አልተገለጠልኝም ነበር። . . .ለሐያ ስድስት አመታት
የኖርኩበትን አካሌን ለእርሱ መልቀቅ ቀላል ውሳኔ አልነበረም . .
."[4]።

ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ሪስ ዊልስ በጣም አስገራሚ በሆኑ የምልጃ
ልምምዶች ውስጥ አልፎአል። በሚስዮናዊነት በታላቅዋ ብሪታንያ
በአፍሪቃ ያገለገለ ቢሆንም በጣም የሚታወቀው ግን በምልጃ

አገልግሎቱ ነው። ሪስ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት በ1924 በስዋንሲ
(ዌልስ) የመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ ከፈተ። በብዙዎች እምነት
"መንፈሳዊው ሁለተኛው የዓለም ጦርነት" የተደረገው በዚህ ስፍራ
ነው። ከናዚ ጀርመን ጦር በስተ ጀርባ የነበረው የርኩሳን መናፍስት
ጦር ድል የተመታው በስዋንሲ ነው - በሪስ ዊልስ፣ በኮሌጁ
መምህራንና ተማሪዎች ምልጃ።

በጣም አስገራሚ በሆነ መንገድ መንፈስ ቅዱስ ሪስ ዊልስንና ኮሌጁን
ከጃንሆይና ከኢትዮጵያ ጋር አቆራኛቸው። በ1936 የማይጨው
ጦርነት ውጤት ገና በውል ከመታወቁ ቀደም ብሎ በስዋንሲ ስለ
ኢትዮጵያ የሦስት ሳምንታት ጾምና ጸሎት ተደርጎ ነበር። "በራስዋ
በአገሪቱ ውስጥ ሆነን የምንዋጋ ያህል ነበር . . . እግዚአብሔር
ኢትዮጵያን ለፋሺስቱ አምባገነን አሳልፎ እንደማይሰጣት አምነናል . .
." ይላል ሪስ።

ጦርነቱ በኢጣሊያ ድል አድራጊነት ሲደመደም ንጉሡም ወደ
እንግሊዝ አገር ተሰደዱ። ከዚህ ጊዜ በኋላ ነበር ልጅ አስራት ካሣ፣
አቢይ አበበና የንጉሡ "የግል ቻፕሌን"[5] የሚሰዮናውያን ልጆች የቀለም
ትምህርት እንዲማሩበት ሪስ በከፈተው ተማሪ ቤት በአዳሪነት መማር
የጀመሩት። ከአንድ አመት በኋላ ንጉሡ ልጅ አስራትን ለመጎብኘት
ወደ ትምህርት ቤቱ ለመምጣት ጠይቀው ተፈቀደላቸው። ስዋንሲ
ሲደርሱ የከተማይቱ ከንቲባና ሚስታቸው ተቀበሏቸው። ንጉሡም
ትምህርት ቤቱንና ስለ አገራቸው ብርቱ መንፈሳዊ ጦርነት ሲካሄድበት
የነበረውን ኮሌጅ ጎበኙ። ከሪስ ዊልስና ከባለቤቱም ጋር ተዋወቁ።

በዚያ ኮሌጅ ውስጥ ከዚያም በኋላ ንጉሡ በተገኙበትና ባልተገኙበት
ስለ ኢትዮጵያ ወደ እግዚአብሔር በጽኑ ተማልዷል። ሪስ ዊልስም
አንድ ቀን ንጉሡ ወደ አገራቸውና ወደ ዙፋናቸው እንደሚመለሱ
ከመንፈስ ቅዱስ ያገኘውን መረዳት ለንጉሡ አስረግጦ ነግሯቸው
ነበር። በ1939 የበጋ ወራት ንጉሡ ለሁለት ሳምንታት በስዋንሲ
ቆይተዋል። በየምሽቱም በኮሌጁ የሚካሄደውን የጸሎት ስብሰባ ይካፈሉ
ነበር።

ንጉሡ ለሪስ ዊልስ ከአዲስ አበባ የደስታ መገለጫ ቴሌግራም
ሲያስተላልፉለት ወደ አገራቸውና ወደ ዙፋናቸው ከተመለሱ ሁለት
ወራት እንኳን አላለፉም ነበር። ሪስም ደስታውን በመግለጽ
ለንጉሡና ለአገራቸውም የወደፊት ሠላም እንደሚጸልይ ቃል በመግባት
ወድያው መልስ ልኮላቸዋል። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ በየአመቱ የነፃነት
መታሰቢያ በዓል በሚከበርበት ወቅት ንጉሡና ሪስ የደስታ መግለጫዎች
ይለዋወጡ ነበር ትላለች የትምህርት ቤቱ ዳይሬክተር የነበረችው ዶሪስ
ሩስኮ[6]።

ንጉሣዊው የወንጌል ስርጭት ስልት

ንጉሡ ከኢንግሊዝ አገር ሲመለሱ በመንፈሳዊ አመለካከታቸው (ምናልባት በመንፈሳዊ ሕይወታቸውም ሞምር) ተለውጠው ነበ የተመለሱት። የወሰዱአቸው አንዳንድ እርምጃዎች ሲታ እንዲያውም ለወንጌል ስርጭት ስልት ነድፈው የተመለሱ ይመስላል ሁለት ማስረጃ ዎች እጠቅሳለሁ።

የመጀመሪያው በዚያን ጊዜ በአገሪቱ ገና በማቆጥቆጥ ላይ በነበሩ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለማስተማር ከውጭ አገ የሚያስመጡአቸው መምህራን በእምነታቸው ወንጌላውያን ክርስቲያኖ የሆኑ እንዲሆኑ ለማድረግ የወሰዱት እርምጃ ነው። የሚፈልጉአቸውን ዓይነት መምህራን በማፈላለግ ረገድ ሊረዱአቸው እንደሚችሉ ለንጉሡ የተሰጣቸው የዊተን ኮሌጁ ፕሬዚዳንት የዶክተ ሬይሞንድ ኤድማን ስም ነበር። ዊተን በቺካጎ (አሜሪካ) የሚገ ኘ ክርስቲያናዊ ኮሌጅ ነው።

ዶክተር ኤድማን በንጉሡ ጥሪ ከሌላ አንድ ሰው ጋር ወደ አዲስ አበ ይመጣሉ። ንጉሡም የአገራቸው ወጣቶች በዘመናዊ ትምህርትና በወንጌልም እውነት ተኮትኩተው እንዲያድጉ ያላቸውን ፍላጎት ይገልጹላቸውና ለዚህ ብቁ የሚሆኑ መምህራንን እንዲያፈላልጉላቸው ይጠይቁአቸዋል። ዶክተሩ ጥያቄውን ተቀብለው ወደ አገራቸው ከተመለሱ በኋላ የንጉሡን ፍላጎት የሚያሟሉ መምህራንን ከአሜሪካ፣ ከካናዳ፣ ከአውስትራሊያ፣ ከህንድና ከግብፅ አገሮች መልምለው ወደ ኢትዮጵያ ላኩ። መምህራኑም በዳግማዊ ምኒልክ፣ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ (ኮብቡ)፣ በመድኃኔ ዓለም፣ በእቴጌ መነን፣ በልዕልት ዘነ መርቅ፣ በሐረር መድኃኔ ዓለም ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ተመድበው ማስተማር ጀመሩ።

በ1942 እና በ1943 ዓ.ም. በዳግማዊ ምኒልክ ት/ቤት ከሚያስተምሩ መምህራን መካከል አስራ አንዱ በዶክተር ኤድማን ተመልምለው ወደ ኢትዮጵያ ከተላኩት መካከል ነበሩ። በሁሉም የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ይሁን ወይም በአንዳንዶቹ ብቻ አላረጋገጥኩም እንጂ ሥርዓተ ትምህርቱ (ካሪኩለም) እራሱ የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርት እንደሚያካትት ሆኖ ነበር የተቀረጸው። በክፍል ውስጥ ተማሪዎች መጽሐፍ ቅዱስ ይማሩ፣ የኢንግሊዝኛ መዝሙሮችንም ይዘምሩ ነበር። ይህም በኋላ ላይ ብዙዎቻችን ከደረስንበት በአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች ከሚሰጠው የሞራል ወይም የግብረ ገብነት ትምህርት በተጨማሪ ነበር።

በዳግማዊ ምኒልክ ት/ቤት ሳሉ ጌታን ከተቀበሉት እና/ወይም ከተጠመቁት አስራ ሁለት ተማሪዎች መካከል ብዙዎቻችን የምናውቃቸው፦

ሙላቱ ባፋ (በኋላ ዶክተር)
የሐንስ እጅጉ (በኋላ ካፕቴን/መጋቢ)
ክፍሌ ስዩም (በኋላ ኮሎኔል)

ይገኛሉ። አስራ ሁለቱ ተማሪዎች በሜይ ወር 1951 (ምናልባት በግንቦት ወር 1943 ዓ.ም.) በቀበና ወንዝ በመስጠም (immersion) ተጠመቁ። ያጠመቋቸው የኤስ.አይ.ኤም. ዶክተር አንድርው ግራሃም ናቸው።

ዶክተር አንድርው ግራሃም በንጉሡ ትዕዛዝ የተተረጎመውን ሁለተኛውን የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ከኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ጋር በመሆን የተረጎሙት ሰው ናቸው። በሊቃውንቱ መካከል የነበሩት ብቸኛው የዕብራይስጥና የጽርዕ (ግሪክ) ቋንቋዎች ሊቅ እርሳቸው ነበሩ። ንጉሠ ነገሥቱ ለዚያ ትርጉም በጻፉት መቅድም ውስጥ የሚከተለውን ብለዋል።

> ለእግዚአብሔር ክብርና ምስጋና ይድረሰውና የኢትዮጵያን ነፃነት አስመልሰን ከንጉሠ ነገሥት መንግሥታችን ከገባን በኋላ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ከመሠረታዊ ቋንቋው ከዕብራይስጥና ከጽርዕ ጋር እየተያየ ሊታረም እንደሚገባው ስለ ተመለከትን በቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት ለዚህ ሥራ ተገቢ የሆኑትን ሊቃውንት መርጠን በየካቲት 27 ቀን 1939 ዓ.ም. አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ኮሚቴ በቤተ መንግሥታችን ግቢ እንዲቋቋም አደረግን። ኮሚቴውም አምስት አመት ያህል በትጋትና በቅንነት ሠርቶ በሚያዝያ 11 ቀን 1944 ዓ.ም. አቀረበልን። በዚህ ሥራ ላይ ለረዱንና ላገለገሉን ሁሉ ከልብ የሆነ ምስጋና እንሰጣቸዋለን።

ንጉሡ "ለረዱን" ከሚሏቸው መካከል ያለ ጥርጥር ዶክተር ግራሃም አንዱ ነበሩ። ዶክተር ግራሃም አስራ ሁለቱን ተማሪዎች ባጠመቁበት ጊዜ መሐል ፒያሳ ከወርቅ አፍሳሹ ከተከሉ ደስታ ሱቅ በስተ ጀርባ በነበረው የኤስ.አይ.ኤም. ቻፕል ውስጥ መጋቢ (ፓስተር) ነበሩ።

የተማሪዎቹ መጠመቅ ወዲያው ታወቀ። እንደ ታወቀም ወዲያው ተደበደቡ ታሠሩ። የታሠሩትም በመጀመሪያ በትምህርት ሚኒስቴር፣ ቀጥሎም በአርበኞች ት/ቤት ግቢ ውስጥ ነበር። ከሦስት ወራት በኋላ ተማሪዎቹ ከእስር ሲፈቱ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶአቸው አዲስ አበባ ውስጥ በሚገኙ የተለያዩ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች እንዲማሩ ተደረጉአቸው። በቁጥር በዛ የሚሉት ወደ ተፈሪ መኮንን ት/ቤት ነበር የተላኩት። ወደዚያ የተላኩትም በዚያ መምህራኑ ኢየሱሳውያን

(ጀስዊት) ካቶሊኮች ስለሆኑ ለፕሮቴስታንቶቹ ወጣ
አይመቹአቸውም በሚል ነው።

አዲሱ እምነት ግን ተማሪዎቹ ወደ ተበተኑባቸው ት/ቤ
አብሮአቸው መዝመት ጀመረ። ይኸ መሆኑ እንደ ተሰማ ተማሪ
በሙሉ ከየት/ቤቶቹ እንዲባረሩ ተወሰነባቸው። መምህራኑም
የመጡባቸው አገሮች እንዲመለሱ ተደረገ። በጊዜው የትምህ
ሚኒስትሩ ክቡር አቶ አካለ ወርቅ ሐብተ ወልድ ነበሩ። እርሳቸው
አክራሪ የኦርቶዶክስ ክርስትና ተከታይ ነበሩ።

ይህንን መረጃ የሰጠኝ ከአስራ ሁለቱ ተማሪዎች አንዱ የነበረውና
በቺካጎ የሚኖረው መጋቢ/ካፕቴን ዮሐንስ እጅጉ ነው። የሰ
መረጃ ምንጭ ጠይቄዋለሁ። ምንጮቹ አራት ናቸ
የመጀመሪያው እራሱ ነው። በ1942 እና በ1943 ዓ.ም. የዳግ
ምኒልክ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪ ነበር። ሁለተኛው በጊ
በዳግማዊ ምኒልክ ት/ቤት የነበሩ መምህራን ናቸው። የ
ከእነዚህ አንዳንዶቹን በአሜሪካን አገር የማግኘት ዕድል ገጥሞታ
ሦስተኛው በጊዜው በአዲስ አበባ የነበሩ የኤ.አይ.ኤም. ሚስዮናው
ናቸው። ዮሐንስ ከእነዚህም አንዳንዶቹን በአሜሪካን አገር የማግ
ዕድል ገጥሞታል።

በመጨረሻም በካሴት ተቀርፆ በጆሮው የሰማው የዶክተር ሬይሞ
ኢድማን ስብከት ነው። ያ ስብከት የዶክተሩ የመጨረሻ ስብከት ነ
ርዕሱ "In the Presence of the King" (በንጉሡ ፊት) የሚል ሲ
በዚያ ስብከታቸው ዶክተሩ ወደ ኢትዮጵያ እንዴት እንደ መ
በንጉሡ ፊት ከመቅረባቸው በፊት ስለ ተሰጣቸው የቤተ መንግ
ሥርዓት (ፕሮቶኮል) ትምህርት፣ ከዚያም ወደ ንጉሡ ፊት በቀ
ጊዜ የተመለከቱትን የንጉሡን ክብርና ግርማ፣ በአንዳንድ ደ
የራሳቸውን ፍርሃት ያወሳሉ።

ዶክተር ኢድማን በገዛ ሕይወታቸው ካጋጠማቸው ከዚህ አጋ
በመነሳት የምድራዊ ንጉሥ ክብር፣ ግርማና ማስፈራት የዚህን ዓ
ከሆነ፣ የሰማያዊው ንጉሥ የኢየሱስ ክርስቶስ ክብር፣ ግር
ማስፈራት የቱን ያህል የበለጠ እንደሚሆን እየተናገሩ እያሉ ከቆመ
ወደቁ። ሰዎች ተርዋሩጠው ከወደቁበት ሲያነሱአቸው ነፍሳቸ
በነገሥታቱ ንጉሥ ፊት ልትቆም ተወሰዳ ነበር።

ሁለተኛውን ማስረጃ በአሜሩ ላንሳ። ከበርሊኑ ኮንግሬስ ሰ
አመታት ቀደም ሲል ወንጌላዊ ቢሊይ ግራሃም ለወንጌል ስብከት
ኢትዮጵያ እንዲመጡ ንጉሡ ፈቃድ ሰጥተዋቸዋል። ስብከ
የሚካሄድበት ስፍራ ብዙ ሕዝብ ሊይዝ የሚችለው የቀዳማዊ ኃይለ

ሥላሴ ስታድየም እንዲሆን፣ በከተማው ውስጥ የሚገኙ ትምህርት
ቤቶች ሁሉ ዝግ እንዲሆኑና ተማሪዎች ወደ ካምቦሎጆ ሂደው
የታዋቂውን ወንጌላዊ ስብከት እንዲሰሙ ሞምር ነበር ንጉሡ
ያዘዙት። በስብሰባው ላይ እንዲገኙ ንጉሡ የልጆቻቸውን ልጆች
ሁሉ አዝዘዋቸው እንደነበረ ነው ቢሊይ ግራሃም በግለ-ታሪካቸው
ውስጥ የጠቀሱት[7]።

ይኸ የንጉሡ ተማሪዎችን በወንጌል እውነት የመድረስ ስልት በምዕራፍ
አራት ውስጥ እንዳየነው የእግዚአብሔርም ስልት ሆኖ ነው
የምናገኘው። እርግጥ ነው ንጉሡ ከኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ብርቱ
የሆነ ተጽዕኖ ሳይኖርባቸው አልቀረም። ቢሆንም ከፈለጉ እስከ ምን
ድረስ መሄድ ይችሉ እንደ ነበረም መመልከት እንችላለን።
በሚመጣው ሪቫይቫል እግዚአብሔር ይህንን የኢትዮጵያን ተማሪዎች
በወንጌል የመድረስ ስልቱን ለሦስተኛ ጊዜ በሥራ ላይ ያውለው
ይሆን? ያኔም የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንና የትምህርት ሚኒስቴር
የቀደመ ስህተታቸውን ይሰልሱት ይሆን?

ጃንሆይ እና ጰንጠቆስጤአዊው ክርስትና

ስለ ጰንጠቆስጤአዊው ክርስትና በማወቅ ንጉሡ ጰንጠቆስጤአውያኑን
እራሳቸውን በብዙ አመታት ይቀድሟቸዋል ብያለሁ። በንጉሡና
በጰንጠቆስጤአውያኑ ክርስቲያኖች መካከል የመጀመሪያው ግንኙነት
የሆነው ንጉሡ በስደት እንግሊዝ አገር በነበሩበት ዘመን (1936-
1940) ነው። ጰንጠቆስጤአዊው ሪቫይቫል ወደ አገራቸው
ከመምጣቱ ከእሩብ ምዕት አመታት በላይ ቀደም ብሎ ማለት ነው።

ንጉሡ በስደት በነበሩበት ጊዜ ካወቋቸው ጰንጠቆስጤአውያን መካከል
ምናልባት የመጀመሪያው ሳንፍሪድ ማትሰን ይባላሉ። ከንጉሡ ጋር
በተገናኙ ጊዜ የወንጌልን ቃል ይነግሩአቸዋል። እግዚአብሔር
የአገሪቱን ነፃነት እንዲመልስላቸው ሊጸልዩላቸው ቃል
ይገቡላቸዋል። ንጉሡም እግዚአብሔር ጸሎታቸውን ሰምቶ በድል
ወደ አገራቸው ከመለሳቸው ሚስተር ማትሰን እና ባለቤታቸው ወደ
ኢትዮጵያ መጥተው ወንጌል የሚሰብኩበትን ፈቃድ እንደሚሰጡአቸው
ያረጋግጡላቸዋል[8]። በዚያ ተስፋ መሠረት ነው ሚስተር ሳንፍሪድ
ማትሰንና ባለቤታቸው ወደ ኢትዮጵያ ለመምጣትና በ1954 የፊንላንድ
ጰንጠቆስጤአዊ ሚስዮንን ሥራ በወልመራ ለመጀመር የበቁት።

ሌላው ኬኔት አግሊስቢይ ናቸው። "Det Heliga Aventyret" (The Holy Adventure) በሚለውና በስዊድንኛ ቋንቋ በተጻፈው

መጽሐፋቸው ውስጥ ካርል ራምስትራንድ እንደ ጻፉት ንጉሡ እና ኬኔት አግልስቢይ መጀመሪያ የተገናኙት በአምስቱ የኢጣሊያን ወረራ አመታት ማብቂያ ላይ በሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ ነው። ኬኔት አግልስቢይ በእነዚያ አመታት ከቤተሰባቸው ጋር በዚያ ይኖሩ ነበር። ወደዚያ የመጡት ከኤስ አይ ኤም ሚስዮን ጋር ይሠሩ ከነበረበት ከደቡብ ሱዳን ነው።

ንጉሡ ከስደት ወደ ኢትዮጵያ እየተመለሱ ነበር። አንድ ምሽት በድንገት ኬኔት አግልስቢይ ካሉበት የሚስዮን ጣቢያ ደረሱ። አንድ ሰው እና አንድ በቅሎ ብቻ አብረዋቸው ነበሩ። ሌሊቱን የሚያሳልፉበት ስፍራ እና የማታ ልብስ ያስፈልጋቸው ነበር። አግልስቢይ ሁለቱንም ሰጡአቸው። ንጉሡ ያንን ውለታ አልዘነጉም። ከብዙ አመታት በኋላ አሜሪካንን ሲጎበኙ ሊቀበሉአቸው ከመጡት ሰዎች መካከል ኬኔት አግልስቢይ አንዱ ነበሩ። ንጉሡ ጠርተው አነጋገሩአቸው። ወደ ኢትዮጵያ ለመምጣት ከፈለጉ በሩ ለርሳቸው ክፍት እንደሆነ ነገሩአቸው። እና አግልስቢይ በንጉሡ ግብዣ ወደ ኢትዮጵያ መጡ።

ኬኔት አግልስቢይ ጳንጠቆስጤአዊ ብቻ አልነበሩም። ቅዳሜ ሰንበትን አክባሪም ነበሩ። ስለዚህ በኤስ አይ ኤም እና በሌሎችም ሚስዮናውያን ዘንድ ተቀባይነት አልነበራቸውም። ንጉሡ የሆነ ሥራ ሊሰጡአቸው በጠየቁአቸው ጊዜ ወንጌል መስበክና መጽሐፍ ቅዱስ ማሠራጨት የማይችሉበትን ሥራ መሥራት እንደማይወዱ እንደ ነገሩአቸው፣ ንጉሡም ይህማ ከሁሉ የሚበልጠው ጉዳይ ስለሆነ የምትወዱትን መሥራት ትችላለህ እንዳሉአቸው፣ ሰዎችን ወደ ቤታቸው እየጠሩ ወንጌልን ይሰብኩ እንደነበረ፣ በመኪናቸው በስተኋላ "Be sure your sin will find you out" (እርግጠኛ ሁን፣ ኃጢአትህ ያገኝሃል) የሚል ጽሑፍ ለጥፈው በአዲስ አበባ መንገዶች ላይ ይዘዋወሩ እንደ ነበረ ካርል ራምስትራንድ ጽፈዋል[9]። አግልስቢይ ከሰዊድን ፈላያልፈይ ሚስዮን ጋር በተባበሩነት በየስፍራው እየተዘዋወሩ ወንጌል በመስበክና በማስተማር አገልግለዋል።

ስለ ጳንጠቆስጤአዊው ክርስትና ንጉሡ ሌላ ግንዛቤ ያገኙበት አጋጣሚ የተፈጠረው ጳንጠቆስጤአዊቷ ወንጌላዊት ጄን ኮሊንስ ዳውድ ከባለቤትዋ ጋር በመሆን ኢትዮጵያን በጎበኘችበት ጊዜ ነው። ዘመኑ 1945 ዓ.ም. ነበር። ወንጌላዊት ዳውድ ለሁለት ወራት በአዲስ አበባ ከተማ መጀመሪያ በካምቦሎጅ ቀጥሎም በጃንሜዳ በወንጌል ስብከትና በፈውስ አገልግላለች። ስብሰባው በተጀመረ ቀን የንጉሡ የመጨረሻ ልጅ ልዑል ሣህለ ሥላሴ፣ የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ፕሪንሲፓል ብፁዕ አቡነ ማርቆስ፣ የፍርድ ሚኒስቴር እና የአገር ግዛት

ሚኒስቴር ምክትል ሚኒስትሮች በካምቦሎጅ ተገኝተው ስብሰባውን መከታተላቸውን ወንጌላዊት ዳውድ ጽፋለች[10]።

ያ ክሩሴድ በብዙ መንገዶች ከዚያ በኋላ ከምናውቃቸው ሌሎች ክሩሴዶች የተለየ ነበር። ከዚህ ጫፍ ወንጌላዊት ዳውድን የጋበዛት የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ነበር። የኮሌጁ ፕሪንሲፓል የነበሩት አቡነ ማርቆስ ግብፃዊ ነበሩ። ኮሌጁ ቶዳሪ ዛኪ የተባሉ ግብፃዊ አስተማሪም ነበሩት። እነዚህ ግብፃውያን ወንጌላዊት ዳውድ በግብፅ አገር ስላደረገቻቸው በተአምራት የተሞሉ ክሩሴዶች በግብፅ ጋዜጦች ላይ ከተጻፉት ዘገባዎች ይረዳሉ። ከዚያ ጫፍ ባልና ሚስቱ ወንጌላውያን በየጉዳኖስ አገር የሚያደርጉትን ክሩሴድ አጠናቅቀው ወደ ሌላ አገር ለመሄድ ሲዘጋጁ እግዚአብሔር ወደ አዲስ አበባ እንዲሄዱ በግልጽ ይናገራቸዋል። ይኸ የመጀመሪያው የልዩነት ነጥብ ነው። ጳንጠቆስጤአዊት ወንጌላዊት በኢትዮጵያ ክሩሴድ እንድታደርግ በአርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መጋበዝዋ።

ሁለተኛው በዚያ ክሩሴድ ላይ በወንጌላዊትዋ ጸሎት የሚፈወሱ ሰዎች ምስክርነታቸው እየተጣራ እርግጥ ሆኖ የተገኘው በፖሊስ የዕለት ሁኔታ መገበብ ላይ ይሰፍር ነበር። በክሩሴዱ የመጀመሪያ ቀን ከተፈወሱት ሰዎች መካከል በመጀመሪያ ለመመስከር የወጣው ከልጅነቱ ጀምሮ አንድ ጆሮው የማይሰማለት የፖሊስ ሠራዊት ባልደረባ ነበር። ፖሊሱ የማይሰማው ጆሮው መስማት መጀመሩን ሲመሰክር የሰሙ አንድ የጦር ሠራዊት ኮሎኔል ፖሊሱ መታወቂያውን እንዲያሳያቸው ይጠይቁታል። ከዚያም ፋይሉ እንዲመረመር ያስደርጋሉ። ያም ፖሊስ አንድ ጆሮው እንደማይሰማ ተመዝግቦ ይገኛል። ከዚያ በኋላ ተፈውሻለሁ የሚሉ ሰዎችን ሁሉ ቃል እንዲቀበል ፖሊስ በቋሚነት ይታዘዛል።

ሦስተኛ ያ ክሩሴድ የተካሄደው በየዕለቱ ለሁለት ወራት ነበር። በሥራ ቀናት ከሥራ ሰአት በኋላ በየቀኑ አንድ ጊዜ፤ በየዕሑዱ ደግሞ ከሰአት በፊትና ከሰአት በኋላ ሁለት ጊዜ። በክሩሴዱ መክፈቻ ዕለት የነበረው ሰው ከሰባት መቶ አይበልጥም ነበር። ነገር ግን የተፈወሱ ሰዎች ምስክርነት እየተሰማ ሲሄድ የሰው ቁጥር እየጨመረ ሄዶ በየስብሰባው ቁጥሩ እስከ አስራ አምስት ሺህ የሚደርስ ሰው ይገኝ ነበር። አንድ ቀን በኩበር ትራቡኑ ላይ ወንጌላዊት ዳውድ በቆመችበት ዙርያ ብዙ ሰው ከመከማቸቱ የተነሳ ከእንጨት የተሠራው መቆሚያ ተደርምሶ በዚያ ከቆሙት ሰዎች ብዙዎቹ ለአራት ሜትር ያህል ወደ ታች ወድቀዋል። ሆኖም አንድም ሰው አልተጎዳም። ስብሰባው ከካንቦሎጅ ወደ ጃን ሜዳ የዞረው በዚህ ምክንያት እንደ ነበረ የወንጌላዊትዋ አስተርጓሚ የነበረው የባንኩ ሠመረ ዘርዑ አጫውቶኛል። ሕዝቡ የወንጌላዊት ዳውድን ስብከት ለማዳመጥና ለመመርመር፣

የፈውስዋንም እውነተኛነት ለማጣራትና ለማረጋገጥ በቂ ጊዜ ነበረው። ከጥቂት ቀናት አገልግሎት በኋላ የአዲስ አበባ ሰው ለወንጌላዊት “የካምቦሎጆዋ ማርያም” የሚል መጠሪያ አወጣላት። ተቀበላት ማለት ነው። የሁለትና የሦስት ቀናት ክሩሴዶች ለሕዝቡ ይሆንን ዕድል አይሰጡትም።

አራተኛ የመንግሥት ጋዜጦች ስለ ክሩሴዱ ይጽፉ ነበር። ንጉሣውያን ቤተሰቦችን ጨምሮ የመንግሥት ባለ ሥልጣናትም ክሩሴዱን ይካፈሉ ነበር። ለማስረጃም ያህል የኢትዮጵያ ሔራልድ ስለ ክሩሴዱ የጻፈው ዜና፣ ከጎቲባ ሀለተወርቅ የተባሉ ሰው ስለ ልጃቸው መፈወስ የጻፉት ምስክርነት፣ እንዲሁም የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ፕሪንሲፓል ስለ ክሩሴዱ በጽሑፍ የሰጡት አጠቃላይ አስተያየት በዚህች መጽሐፍ ውስጥ ተካትተዋል።

ንጉሡ ከጳንጠቆስጤአዊው ክርስትና ጋር ፊት ለፊት የተገናኙበት ሌላው አጋጣሚ የተፈጠረው ኢንግሊዛዊው ወንጌላዊ ብራያን ዊልያምስ ከፌብርዋሪ 26 እስከ ማርች 24 ቀን 1965 ድረስ በኢትዮጵያ ክሩሴድ ለማድረግ ከባለቤቱ ጋር በመጣ ጊዜ ነበር። ብራያን እንደሚለው “በ1964 መጨረሻ ላይ ወደ ኢትዮጵያ እንድሄድ እግዚአብሔር ሊናገረኝ ጀመረ . . . ጃንዋሪ 21 ቀን 1965 በጸሎት በጌታ ፊት ባለሁበት ጊዜ ሐዋርያው ጳውሎስ በቂሳር ፊት በቆመበት ዓይነት እኛም በዓዬ ኃይለሥላሴ ፊት እንደምንቆም ጌታ ተናገረን . . ይህም ማርች 23 ቀን ንጉሡ እኔንና ባለቤቴን በኢየቤልዩ ቤተ መንግሥት በተቀበሉን ጊዜ ተፈጸመ . . .” [11]።

ብራያን ዊልያምስ እና ባለቤቱ አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በቆዩባቸው የአንድ ወር ጊዜ ውስጥ በፊንላንድ ሚስዮንና በሌሎችም ቦታዎች ስብሰባዎች አካሂደዋል። ብራያን እንደሚለው ስብሰባቸው የቴሌቪዥን፣ የራድዮና የጋዜጣ ማስታወቂያዎች የተነገሩለት ቢሆንም እንደታሰበው በጃንሜዳ አልተደረገም። ሆኖም ባገለገሉባቸው ሌሎች ቦታዎች ሁሉ ሰዎች ጌታን ተቀብለዋል፤ ከአጋንንት እስራት ተፈትተዋል፤ ከበሽታ ተፈውሰዋል፤ አንድ ከሐረር ከተማ የመጣ ወንድም በመንፈስ ቅዱስ ተጠምቆ በልሳን ተናግሮአል። የንጉሣውያን ቤተሰብ አባላት እያስጠሩት ብዙ ጊዜ ወደ ቤታቸው እየሄደ እንደ ጸለየላቸውም ጠትሷል።

ወደ ንጉሡ የተላኩት መልዕክተኞች

ሁሉንም አናውቃቸውም። ስማቸው ከሚጠቀሰው መካከል ኬኔዝ አግልስቢይ፣ ብራያን ዊልያምስና ሩት ሔፍሊን ይገኙበታል። ሩት

በዓለም ዙሪያ ለብዙ አገሮች መሪዎች ከእግዚአብሔር ዘንድ መልዕክት በመቀበልና በማድረስ የታወቀች ሴት ናት። ሩት ወደ ኢትዮጵያ የመጣችው ሦስት ጊዜ ነው። የመጀመሪያው በ1967 መጀመሪያ ላይ ለስድስት ወራት በአውሮፓ፣ በመካከለኛው ምስራቅና በአፍሪካ ለወንጌል አገልግሎት በተዘዋወረችበት ጊዜ ነበር። ያን ጊዜ ከካርቱም ተነስታ በከሰላ፣ በተሰነይ፣ በአስመራና በጎንደር አድርጋ በየብስ ነበር የመጣችው። ለፈረንጆቹ ትንሳኤ በዓል ካርቱም ስለ ነበረች አዲስ አበባ የደረሰችው በግቦት ወር 1959 ዓ.ም. ሳይሆን አይቀርም። በዚህኛው ጉዞዋ በአስመራ እንጂ በአዲስ አበባ አላገለገለችም።

በዚያው የፈረንጆች አመት መጨረሻ አካባቢ ሩት ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ መጥታለች። ይኸኛው አመጣጥዋ እንደ መጀመሪያው በየብስ ሳይሆን በአየር ነበር። የመጣችውም እግዚአብሔር በቀጥታ ወደ ኢትዮጵያው ንጉሥ ልኳት ነው። አዲስ አበባ እንደ ደረሰች በሚኖናይት ሚስዮን የእንግዶች ማረፊያ ቤት መኝታ ከያዘች በኋላ ወደ ቤተ መንግሥት ስልክ ደውላ ንጉሡን ማግኘት እንደምትፈልግ ታስታውቃለች። ነገር ግን ንጉሡ በመጀመሪያ ከሆላንድ አቻቸው ከንግሥት ጁሊያና ጋር፣ ቀጥሎም ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጸሐፊ ከኡ ታንት ጋር ከዚያም ከሌሎች ብዙ ሰዎች ጋር ትልልቅ ስብሰባዎች ስላሏቸው ልታገኛቸው እንደማትችል ይነገራታል። እርስዋም ንጉሡ ሊያደዋት እስከሚችሉበት ጊዜ ድረስ በትዕግሥት እንደምትቆይ ትነግርና ስምዋንና አድራሻዋን ትተዋለች።

በዚህ ቆይታዋ ጊዜ ነበር በኢትዮጵያ የፊንላንድ ጳንጠቆስጤአዊ ሚስዮን ጀማሪ በነበሩት በሚስተር ሳንፍሬድ ማትሰን ቤት አገልግሎት መስጠት የጀመረችው። ሚስተር ማትሰንና ባለቤታቸው ሚስስ አናሊስ ማትሰን ቀደም ሲል ይኖሩ የነበረው በወልመራ ሲሆን ከአንድ አመት በፊት ጀምረው ግን በዳግማዊ ምኒሊክ ሆስፒታል አካባቢ ቤት በመከራየት መኖሪያቸውን በአዲስ አበባ አድርገዋል። እንዲህ ያደረጉትም እግዚአብሔር የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን እንዲያገለግሉ ምሪት ሰጥቶአቸው ነበር።

ነገር ግን እዚያ ቤት ከገቡበት ከመጀመሪያው ቀን አንስቶ ባለቤታቸው ታማሚ ስለ ሆኑባቸው ሰውየው ከአስታማሚነት ያለፈ ነገር ለማድረግ አልቻሉም። ይህንን ሁኔታ ለሩት ይነግሯትና እንድትጸልይላቸው ይጠይቋታል። ሩት ስትጸልይላቸው ሴትየዋ ወዲያው ይፈወሱና እንግዳዋን ሴት ማስተናገድ ይጀምራሉ። ያን ዕለት ሩት ወደ ማረፊያዋ ለመሄድ ስትነሳ ነገም ብትመጣና አብራቸው ብትጸልይ ደስ እንደሚላቸው ይነግሯታል። ሩትም እንደተጠየቀችው ትመጣና አብረው ሲጸልዩ ያረፍዳሉ።

የዚያም ቀን ጸሎት ሲያልቅ ነገም እንድትመጣ የጠይቋታል። ነገምን
ከነገ ወዲያም እየተመላለሰች አብራቸው መጸለይ ትቀጥላለች።
"ለስንት ቀናት እንደዚህ እንደ ጸለይን አላስታውስም። ነገር ግን ከ
ለታት አንድ ቀን የምንጸልይበት ክፍል በወጣት የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች
መሙላት መጀመሩን አስታውሳለሁ" ትላለች ሩት "Harvest
Glory" በተሰኘው መጽሐፍዋ ውስጥ[12]።

ክፍሉ በአማዳሚዎች አማዳሚዎቹም በተቀማጮች ተሞሉ። ሩት
መጸለይ ብቻ ሳይሆን መስበክም ጀመረች።

> ብዙ ወጣቶች ሲመጡ ባየሁ ጊዜ ተስቸ የደህንነት መልዕክት
> ሰበክሁላቸው። ከዚያ በፊት ደህንነት ያላገኙ ያን ቀን አገኙ
> ከዚያ በኋላ ስለ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ለጥቂት ደቂቃዎ
> ተናገርኩና ስንቶቻቸው በመንፈስ ቅዱስ ለመጠመ
> እንደሚፈልጉ ጠየቅኋቸው። በዚያ የነበሩት ወጣቶች በሙሉ
> እጃቸውን አነሱ። ወደ እያንዳንዳቸው እየሄድኩ
> ለእያንዳንዳቸው በየተራ እጃችንን እየጫንን ጸለይን
> በመጀመሪያው ቀን ሃምሳ የሚሆኑ ተማሪዎች በመንፈስ ቅዱ
> ተጠመቁ። ከዚያ ቀን ጀምሮ በብዙ ሳምንታት ውስ
> ከአምስት መቶ የሚበልጡ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በመንፈ
> ቅዱስ ተሞልተው በልሳኖች ተናገሩ።

በዚህ መካከል ነበር አንድ ቀን ስልክ ተደውሎ ንጉሥ አሁን ሊያዩአቸ
እንደሚችሉ የተነገራት። ሩት ወደ ቤተ መንግሥት የሄደችው
የሚኖናይት ሚስዮን የእንግዳ ማረፊያ ቤት ኃላፊ ከሆነችው
ከአሜሪካዊቷ ከሣራ ሩሽ ጋር ነበር። "ስለ ሪቫይቫሉና ጌታ
ለህዝባቸው እያደረገ ስላለው ነገር ለንጉሥ ነገርኳቸው" ትላለች
ሩት።

> በዚህ አገልግሎት ከሚሳተፉት ሰዎች ውስጥ ብዙዎቹን በስም
> ጠራሁላቸው። እርሳቸውም ጥቂቶቹን በግ
> እንደሚያውቋአቸውና ስለ ተፈፀሙት ስለ አንዳንድ የፈው
> ተአምራት መስማታቸውን ነገሩኝ። ለጥቂት ጊዜ እንደዚ
> ከተነጋገርን በኋላ ለማርማዊነትዎ ከእግዚአብሔር ዘንድ መል
> ክት አለኝ። አሁን ልነግርዎ እችላለሁ? አልኳቸው። ወ
> ግቢ ሚኒስትሩ ዘወር አሉና የሆነ ነገር በአማርኛ ከተናገ
> በኋላ ወደ እኔ መለስ ብለው በእንግሊዝኛ ቋንቋ የጌታን መል
> ክት አሁን ማስተላለፍ ትችያለሽ አሉኝ። ከዚያ በፊት ብዙ
> ጊዜ እንደማደርገው ዓይኖቼን ጨፈንኩና መተንበ
> ጀመርኩ። ነገር ግን ከአፌ የሚወጣው ከዚያ በፊት
> የተለማመድኩት ዓይነት ነገር አልነበረም[13]።

ሩት ከዚያ በፊት ስትተነበይ ሙሉውን መልዕክት አስተላልፋ
እስክትጨርስ ድረስ ረጋ ብላ ግን ሳታቋርጥ እንደምትናገር፣ ያን ቀን
ግን በዝምታ ጊዜያት የተራራቁ አሜሞር ዓረፍተ ነገሮች
እንደተናገረች፣ መልዕክቷንም ተናግራ ለመጨረስ ከቀድሞው ይልቅ
ረዥም ጊዜ እንደፈጀባት ትገልጻለች።

> በመጨረሻ ዓይኖቼን ስገልጥ የግቢ ሚኒስትሩ የምናገረውን
> ሁሉ በችኮላ ቃል በቃል ሲጽፉ አየሁአቸው። ንጉሡ ለግቢ
> ሚኒስትሩ ምን እንዳሏቸው፣ ጌታም ለምን በዝምታ
> እንድናገርና በየዓረፍተ ነገሩ መካከል ጊዜ እንድሰጥ
> እንዳደረገኝ ያኔ ነበር የገባኝ[14]።

ሩት ለሦስተኛ ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ የመጣችው በመስከረም ወር
መጀመሪያ 1964 ዓ.ም. ነበር። ሩት ለሦስተኛ ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ
የመጣችው ለሁለተኛ ጊዜ በእግዚአብሔር ወደ ንጉሡ ተልካ ሲሆን
አዲስ አበባ ለማደር የነበራት ጊዜ ግን አንድ ሌሊት ብቻ ነበር።
ከንጉሡ ጋር ቅድሚያ ቀጠሮም አልነበራትም። ነገሩ ሁሉ የጥድፊያ
ነበር። ጥድፊያው ግን ሩት የፈጠረችው ሳይሆን እግዚአብሔር
የፈለገው ነበር።

የሚኖናይት ሚስዮኗ ሣራ ሩሽ ከቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ ተቀብላት
ወደ ሚስዮኑ የእንግዶች ማረፊያ ወሰደቻት። ሩት ወዲያው ወደ ቤተ
መንግሥት ስልክ ደውላ ክቡር ጸሐፌ ትዕዛዝ ተፈራ መርቅን
አነጋገረች። እርሳቸውም ንጉሡ በቅድሚያ የያዙአቸውን ጉዳዮች
አስረድተዋት ሊያነጋግሯት እንደማይችሉ ይገልጹላታል። ሩትም "ነገ
ጠዋት ወደ እስራኤል እበርራለሁ። እግዚአብሔር ወደ ንጉሡ
ልኮኛል። የሰጠኝም ጊዜ ይኸ ጊዜ ነው" እንዳለቻቸውና ያረፈችበትን
ቦታ የስልክ ቁጥር እንደ ተወችላቸው ትናገራለች[15]።

በዚያው ዕለት ተደወለላትና ከሰአት በኋላ በአስር ሰአት ንጉሡ በትልቁ
ቤተ መንግሥት ሳይሆን በኢየቤልዩ ቤተ መንግሥት
እንደሚያነጋግሩአት ተነገራት።

> ንጉሡና እኔ ከመጀመሪያው ጊዜ ይልቅ ተቀራርበን ፊት
> ለፊት ተቀመጥን። . . .እግዚአብሔር ለንጉሡ ከፊታቸው
> ስላለው ነገርና ሊያደርጉ ስለሚያስፈልጋቸው ነገር
> ተናግሯቸዋል። በማግሥቱ ወደ ቻይና ሊሄዱ እንደሆነ
> አላወቅሁም ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር ያውቅ ነበርና
> ስለዚያ ጉዞአቸውም ተናገራቸው . . . ያን ዕለት ከቤተ
> መንግሥቱ ስወጣ ንጉሡ "ሩት፣ እግዚአብሔር ለአንድ አገር
> መሪ መልዕክት በሚሰጥበት በማናቸውም ጊዜ ለመሄድና መልዕ
> ክቱን ለማድረስ አታመንቺ" አሉኝ . . . በትክክለኛው ጊዜ
> መምጣቴን ማሳወቃቸው ነበር . . . ችግሮቹ ከመምጣታቸው

በፊት ካገለገሉአቸው የመጨረሻ ሰዎች አንዷ እኔ ነበርኩ . . . በትንቢቱ ውስጥ እግዚአብሔር ሊሆን ስላለው ነገር በቅድሚያ አስጠንቅቆአቸውና ምላሽም ሰጥቶአቸው ነበር[16]::

ያን ዕለት ሩት ወደ ማረፊያዋ ከተመለሰች በኋላ ከቤተ መንግሥት እንደገና ይደወልላትና እግዚአብሔር ስለ ሰጣት መልዕክት አንዳንድ ነገሮችን የበለጠ እንድታብራራ ወደ ቤተ መንግሥት ትጠራለች::

የነበረኝ ጊዜ አጭር ቢሆንም እንኳን በአንድ ምሽት ሁለት ጊዜ ነው ወደ ቤተ መንግሥት የተጠራሁት:: ሊመጡ ስላሉ ፖለቲካዊ ጉዳዮች እግዚአብሔር ንጉሡን እያዘጋጃቸው ነበር[17]::

አዎ! እግዚአብሔርማ እያዘጋጃቸው ነበር:: ንጉሡ ግን እየተዘጋጁ ነበር? እግዚአብሔር የሰጣቸውን የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ተጠቅመውበታል? የግቢ ሚኒስትራቸው ከነቢይትዋ አፍ እየሰሙ ቃል በቃል የጻፉትን የትንቢት ቃል በጥሞና አስበውበታል? የነገሩ ክብደት ታውቋቸዋል? በቅርባቸው ከነበሩት ባለሟሎቻቸው ጋር ተነጋግረውበታል? እግዚአብሔር ለንጉሡ የሰጣትን መልዕክት ሩት እስከ ዛሬ ድረስ ምስጢር አድርጋ የጠበቀችው ቢሆንም በዚያው አመት የተደረጉ አንዳንድ ድርጊቶች ሲታዩ ለእነዚህ ጥያቄዎች አሉታዊ ምላሽ ለመስጠት ነው የምንገደደው::

ለምሳሌ በዚያው አመት በጥቅምት ወር ነበር ጸንጠቆስጤአውያኑን በተመለከተ “. . .የህብረተሰቡን ሞራልና አንድነቱን ለመጠበቅ የሀገሪቱንም ሠላምና ጸጥታ ለማስከበር የኢያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ተግባርና ኃላፊነት ስለሆነ ይህን አጉል የሆነ ስብከት ጎጂነቱን አውቆ እንዲያወግዝና ጨርሶም እንዲያጠፋ. . .” የሚል ሰርኩላር በአገር ግዛት ሚኒስቴር የሕዝብ ጸጥታ ጥበቃ እና በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትረያርክ ጽህፈት ቤት ማህተሞች በአስራ አራቱም ጠቅላይ ግዛቶች የተብተነው:: እንደ ገናም በዚያው አመት በታህሣሥና በሚያዝያ ወራት ነበር የአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ምዕመናን ለአቤቱታ ሁለት ጊዜ ንጉሡ ፊት የቀረቡት:: የተሰጣቸው ምላሽ ከተለመደው “ጉዳያችሁ ተጠንቶ ውሳኔ ይሰጣችኋል” ያለፈ አልነበረም:: በአሰላና በደሬዳዋም ተመሳሳይ አቤቱታዎች ለንጉሡ በግንባር ቀርበው ነበር:: የተሰጡት መልሶች በሁሉም ቦታ ተመሳሳይ ናቸው::

በመጨረሻም በዚያው አመት ነሐሴ 21 ቀን ዕሑድ ዕለት ነበር የሁለተኛ ፖሊስ ጣቢያ አዛዥ የታጠቁ ፖሊሶችን አስከትለው ወደ አዲስ አበባ ሙሉ ወንጌል አማኞች ጸሎት ቤት በመሄድ አምልኮውን በኃይል ያስቆሙትና በቁጥር ወደ ሁለት መቶ ሰባ የሚገመቱ ምዕ

መናንን አሰልፈው ወደ ጣቢያቸው የነዱአቸው:: እነዚያ ወጣቶች ለሦስት ቀናት ያህል በፖሊስ ጣቢያው ከቆዩ በኋላ ወደ ወህኒ ቤት ተጥለዋል:: ወንጀላቸው “ያልተፈቀደ ስብሰባ” ሲያደርጉ መገኘታቸው ነው:: ጥፋተኞች መሆናቸውን ያመኑት ጥቂቶች እስከ 200 ብር የሚደርስ መቀጫ እየከፈሉ ወዲያው ሲለቀቁ ጥፋተኞች አይደለንም ያሉት ብዙዎች ግን የስድስት ወራት እስራት ከጉልበት ሥራ ጋር ተፈረደባቸው:: የአውራጃው ፍርድ ቤት ይህን ፍርድ የሰጠው በሚቀጥለው አመት በጥቅምት ወር ነው:: ፍርደኞቹ ለክፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኝ አሉ:: የከፍተኛው ፍርድ ቤት በሐምሌ ወር ውስጥ በሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ጸንጠቆስጤአውያኑ በሚቀጥሉት ሦስት አመታት ውስጥ በቁጥር ከአምስት በላይ ሆነው ተሰብስበው ቢገኙ ያለ ምንም ጥያቄ ተይዘው እንደሚታሰሩ በማስጠንቀቅ የበታቹ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ አጽንቶ በአመክሮ ለቀቃቸው::

እዚህ ላይ ለንጉሡ የተነገረውን ትንቢትና በሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን ላይ የደረሰውን ስደት ለምን ታያይዛቸዋለህ? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል:: መልሴ አጭር ነው:: በአንድ በኩል ያ ሪቫይቫል ከእግዚአብሔር ለመሆኑ ንጉሡ በቂ ማንዛቤ ነበራቸው:: በሌላ በኩል ደግሞ በኢትዮጵያ እርሳቸው ሳያውቁት የሚሆን ነገር አልነበረምና ያ ሪቫይቫል የተሰደደው እርሳቸው እያወቁ ነበር:: መንግሥታቸው በፖሊስ ኃይሉና በፍትህ አካላቱ ተጠቅሞ የእግዚአብሔርን ጉብኝት ሊያስቆም ሞክረ:: እግዚአብሔር ደግሞ የገዛ ወታደራዊ ኃይሉን በመጠቀም ያንን መንግሥት አስቆመው::

የአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን በኃይል በተዘጋች ልክ በአስራ ስምንተኛው ወር መጨረሻ የካቲት 20 ቀን 1966 ዓ.ም. የሚንስትሮች ምክር ቤት ፈረሰ:: ልክ በሐያ ሁለተኛው ወር መጀመሪያ ሰኔ 21 ቀን ወታደራዊው ደርግ ተቋቋመ:: ልክ በሰላሳ ስድስተኛው ወር (ማለትም ልክ በሦስት አመቱ) ነሐሴ 21 ቀን 1967 ዓ.ም. ንጉሡ መሞታቸው ለኢትዮጵያና ለዓለም ሕዝብ ተነገረ:: እነዚህ ነገሮች አጋጣሚዎች ናቸው? ለእኔ አይመስሉኝም:: ኃያሉ እግዚአብሔር አስቀድሞ የተናገራቸውን ነገሮች እየተገበረ ነበረ:: እርሱም በንጉሡና በመንግሥታቸው ላይ የሦስት አመት የአመክሮ ፍርድ ሰጥቶ የነበረ ይመስለኛል:: በዚያ ዓመት መጀመሪያ ላይ ሩት ሔፍሊንን ለአንድ ቀን አዳር ብቻ በአስቸኳይ ወደ ንጉሡ ሲልካት፣ ወደ አገር በገባችበት በዚያው ቀን ያለ ምንም ቅድሚያ ቀጠሮ በአንድ ከሰዓት በኋላ ንጉሡን ሁለት ጊዜ እንድታገኛቸው ሲያደርግ፣ ከረቫይቫልና ከፍርድ የትኛውን እንደሚመርጡ እየጠየቃቸው የነበረ ይመስለኛል::

ንውጥውጥታ

በሚቀጥሉት ሁለት አመታት ውስጥ የንጉሡ ምርጫ በግልጽ ከታ
በኋላ በኢትዮጵያ የሆነው ነገር በዚህች ዓይነት መጽሐፍ በገጽ
ሊዘከር መቸም አይሞከርም። ያ የታሪክ ጸሐፊዎች ተግባር ይሆናል
እንዲያው በደፈናው ግን የ“ፀሐዩ ንጉሥ” ፀሐይ ጠለቀች። የሦ
ሺህ አመታት ዕድሜ አለው እየተባለ ይተረትለት የነበረው ሰሎሞ
ሥርወ መንግሥት በውርደት ተደመደመ። ዘውዳዊ አገዛ
አከተመ። በቦታው ወታደራዊ/ሶሻሊስታዊ መንግሥት አቆጠቆጠ
በኢትዮጵያ ስር የሰደደውን፣ እጅግ የተጠላውንና እጅግም የተፈራ
ፊውዳላዊ የመሬት ስሪት ለወጠ። የከተማ ቦታና ትርፍ ቤ
በሙሉ የመንግሥት እንዲሆኑ ደነገገ። ብዙ የማምረቻ፣ የማከፋፈ
የአገልግሎት ሰጭ ድርጅቶችንም የራሱ አደረገ።

በዚህ እጅግ ስር ነቀል፣ እጅግም ድፍረትና ቆራጥነት የተሞላ
ድርጊቱ ወታደራዊው/ሶሻሊስታዊው መንግሥት የብዙዎችን ቀ
ቀለበ። በተግባሩ፣ በምሁሩ፣ በጪሰኛው፣ በወገዘ አደሩ፣ እንዲ
አገሩ ተለውጣ ለማየት በሚናፍቀው ሁሉ ታጀበ። ገበሬ
እንዲያኑቱ፣ እንዲያደራጁና በሶሻሊስታዊው ርዕዮተ ዓ
እንዲያስተምሩት በአስሮች ሺዎች የሚቆጠሩ ተማሪዎችን አዘመ
የአገሪቱን ዜጎች በሙሉ በገበሬዎች፣ በከተማ ነዋሪዎች፣ በሴቶ
በወጣቶችና በሞያ ማህበራት ስር አስከተተ።

በቀደሙት ስርዓቶች የተሠራውን ሥራ ሁሉ አከሸፉ። በአንድ
ጀንበር ምድሪቱን ምድራዊ ገነት ሊያደርጋት ደኸ። ሰዎች ሀ
አንድ እራስ እና አንድ ምላስ ቢሆኑለት ወደደ። አይሆንም ያሉ
ሁሉ ያለ ርህራሄ አስወገደ። “ቀኝ” ቃሉ ሳይቀር ተጠላ። “ግ
ተወዳጅነቱ ጎላ። እግዚአብሔርን መፍራት፣ ስነ ምግባር፣ የአ
ህዝብ መለያ የሆነው ባህሉና ወጉ በሙሉ ተሸቀንጥሮ ተጣ
“ከሁሉ በላይ አብዮቱ!” ተባለ። ክፉኩሩ ሰው ለጥቅሙ ከሠራ
ሥርዓት ይልቅ ዋጋው ቀለለ። ከአጽናፍ እስከ አጽናፍ በምድ
ሁሉ ላይ ጨኸቱ “ይውደም!” ሆነ። ለሰው የሚበቅመውን ዐ
ልፋትን፣ አረሙንና አራሙቻውን ግን ያለ ምንም ጥረት የምታበቅ
ምድር እርግማኑን በደስታ ተቀብላ አበቀለች። በጥድፊያ አላደገ
ወዲያውም ለመከር ደረሰላት አንድ ትውልድ አጨደች።

“በሰፈሩት ቁና”

መጽሐፍ ቅዱስ እጅግ አስደናቂ መጽሐፍ ነው። ትምህርቱ እውነት ነው። በውስጡ ያዘላቸው መለኮታዊ መርሆዎች ሁል ጊዜ በሁሉ ቦታ፣ በሚያምኑና በማያምኑም ላይ እኩል ይሠራሉ። የሚከተለውን ጥቅስ በዋቢነት ማየት ይቻላል።

> . . . በእናንተ ላይ እንዳይፈረድባችሁ በማንም ሰው ላይ አትፍረዱ። ምክንያቱም በሌሎች ላይ በምትፈርዱበት ዓይነት በእናንተም ላይ ይፈረድባችኋል። እንዲሁም በምትሰፍሩበት መስፈሪያ ይሰፈርባችኋል (ማቴ 7፡1-2)።

የንጉሡን መንግሥት መንገዳገድና መውደቅ በመተጋገዝ ካፋጠኑት ክስተቶች ውስጥ ዋነኛው የተደበቀው “የወሎ ረሀብ” ነበር። ያንን ረሀብ የደበቁት የኢትዮጵያ መንግሥትና በኢትዮጵያ የሚገኙ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ባለ ሥልጣኖች በመተባበር ነው[18]። ረሀቡን ለመደበቅ ምክንያት የሆነላቸው በግንቦት ወር 1965 ዓ.ም. የሚከበረው የአፍሪቃ አንድነት ድርጅት ምስረታ አስረኛው መታሰቢያ በዓል ነው። ለዚያ በዓል ዝግጅትና የአዲስ አበባን ከተማ ለማስጌጥ ሦስት ሚልዮን የአሜሪካ ዶላር ወጭ ተደርጎ ነበር ይባላል።

የረሀቡ መኖር በሌሎች ዘንድ የታወቀው ትግራዮቹና ወሎዬዎቹ ረሀብተኞች ከቀያቸው ተፈናቅለው፣ ተሰድደውና በእግራቸው ተጉዘው አዲስ አበባ በደረሱ ጊዜ ነበር። ረሃብተኞቹ ስደተኞች በመንግሥት ትዕዛዝ እየታፈሱ ከከተማ ውጭ መወሰዳቸው፣ መጪዎቹም ወደ ከተማ እንዳይገቡ መከልከላቸው በተሰማ ጊዜ የብዙ ኢትዮጵያውያን ቁጣ ነደደ። ዛሬ በመላው ዓለም የኢትዮጵያውያን ብሔራዊ መለያ የሆነው ድርቅና ረሃብ ያኔ ለኢትዮጵያውያኑ ለራሳችንም አዲስ ክስተት ነበርና በህዝቡ ዘንድ የፈጠረው የርህራሔም የቁጣም ስሜት ቀላል አልነበረም። በዚያ ረሀብ ከአንድ ሙቶ ሺህ የማያንሱ ሰዎች ህይወት እንደ ተቀጠፈ ተገምቷል።

ንጉሡን በህዝቡ ለማስጠላት ወታደራዊው ደርግ ያንን ረሀብ በፕሮፖጋንዳ መሣሪያነት ተጠቅሞበታል። በቤተ መንግሥቱ አካባቢ ያለውን አለ ትጥ የተቀናጣ አንዋንዋር ከረሀብተኞቹ አንዋንዋር ጋር በማነፃፀርና ሕዝቡም እንዲያውቀው በመገናኛ ብዙኃን በማሰራጨት በህዝቡ ቁጣ ላይ ነዳጅ አርከፍክፎአል። ይሁን እንጂ በኢትዮጵያ በዚያ ረሀብና በስፋቱም ይሁን በአስከፊነቱ ከዚያ ረሀብ አስር እጅ በሚበልጠው ረሀብ መካከል ያለፉት አስር አመታት ብቻ ነበሩ።

በዚህ ረዥም ረዘመ ጊዜ ውስጥ ወታደራዊው ደርግ ለኢሠፓ ምሥረታ በዓሉ ወጡን ባሞር ታጥቆ ሽር ጉድ እያለ ነበር። ለበዓሉ ዝግጅት፣ ለሐውልት ሥራ፣ ለሰልፈኞች ልብስ፣ ከአገር ውስጥና ከአገር ውጭ በበዓሉ ላይ እንዲገኙ ለተጋበዙ እንግዶች መስተንግዶ የአገሪቱ ጥሪት ይከሰከስ ነበር። ሞሐመድ አሚንና ቢቢሲ ገለጡበት እንጂ ያም ረሀብ ከኢትዮጵያውያንና ከዓለም ሕዝብ ተደብቆ ነበር። ከአስር አመት በፊት የነበረውን ረሀብ ለዓለም ሕዝብ ያጋለጠው ዮናታን ዲምብልቢ እንደ ነበረ፣ የአሁኑን የማጋለጡ ዕጣ ደግሞ በሞሐመድ አሚን ላይ ወደቀበት። እንደ ንጉሡ መንግሥት ሁሉ ወታደራዊው/ሶሻሊስታዊው መንግሥትም መቅኖ ያጣው ከዚያ ረሀብ በኋላ ነበር።

ሁለተኛው መድብል

በሰባዎቹ መጨረሻና በሰማንያዎቹ መጀመሪያ አመታት ወታደራዊው/ሶሻሊስታዊው መንግሥት የመዳከምና የመለሳለስ አዝማሚያ ሊታይበት ጀምሮ ነበር። ለዚህ መዳከምና መለሳለስ ዋነኞቹ ምክንያቶች በውስጥ ከሻዕቢያና ከወያኔ ጋር በሚያደርጋቸው ጦርነቶች የደረሰበት ተደጋጋሚ ሽንፈት፣ በውጭ ደግሞ በሶሻሊስቱ ካምፕ ውስጥ በተለይም በሶቪየት ህብረት መንፈስ የጀመረው የለውጥ ሃሳብ ነበሩ።

በዚህ ጊዜ ነበር ከከፍተኛ ባለሥልጣኖቹ አንዳንዶቹ እየከዱት መኮብለል የጀመሩትና እራሱም ከመካከሉ አንዳንዶቹን በሰበብ ባስባቡ ማግለል የጀመረው። በዚህ ጊዜ ነበር "ቅይጥ" የተባለ የኢኮኖሚ ስልት መከተል የተጀመረው። በመንፈሳዊውም ረገድ ከቀድሞው ይልቅ ለቀቅ ያለ ሁኔታ ሊያንፀባርቅ የጀመረው በዚሁ ጊዜ ነበር። በይርጋዓለም፣ በቦረና ነጌሌ እና በአዋሳ ላለፉት ሰባት አመታት በጽኑ እስራት ሲሰቃዩ የነበሩት ወንጌላውያኑ ተሾመ ወርቁ፣ ተስፋዬ ጋቢሶ፣ ኃይሉ በቀለ አብረዋቸው ከታሠሩት ከሌሎቹ ጋር የተፈቱት በዚሁ ጊዜ ነበር።

ከዚያ ጊዜ ጀምሮ በተከታታይ ለአስር አመታት ያህል ይነገሩ የነበሩት ትንቢቶች በመጀመሪያው መድብል ውስጥ ካየናቸው ትንቢቶች ለየት ያለ ይዘት አላቸው። በእነዚህ አመታት ውስጥ ስለ ኢትዮጵያና ስለ ኢትዮጵያውያን በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በሌሎችም አገሮች፣ በኢትዮጵያውያን ትንቢት ተናጋሪዎች በኩል ብቻ ሳይሆን የሌሎቹ አገሮች ዜጎች በሆኑ ትንቢት ተናጋሪዎችም በኩል ትንቢቶች ይነገሩ ነበር። አብዛኛዎቹ ትንቢቶች በሚከተሉት ዓበይት ሀሳቦች ስር ሊፈረጁ ይችላሉ።

- በምድራችሁ ላይ በጽድቅ እወጣለሁ

- በፊታችሁ አሞር ግን ብርቱ ጨለማ አለ። ያንን ጨለማ ማንም በራሱ ኃይልና በራሱ ዘዴ አያልፈውም። እናንተም ከእኔ ጋር ካልተጣበቃችሁ በቀር አታልፉትም። አብዝታችሁ ወደ እኔ ቅረቡ። አብዝታችሁ ፊቴን ፈልጉ። ብርቱ መናወጥ ይሆናል። መፍረስና መፈራረስ ይሆናል። ቤቴንም አጠራለሁ። መድረኬንም እቀድሳለሁ። ፍርድ ከእግዚአብሔር ቤት የሚጀምርበት ሰአት ደርሶአል።
- ከጨለማው በኋላ በታላቅ መነብየት እነበርሻችኋለሁ። ለዓለም ሁሉ በረከት አደርጋችኋለሁ። የምድራችሁ አፈር ሳይቀር ለመድኃኒትነት ይፈለጋል።

አንዳንድ ሀሳቦች ጠቀሜ እነዚህን ትንቢቶች የመፈተኑን ነገር ለአንባቢ እተዋለሁ። "በጽድቅ እወጣለሁ" ማለት እፈርዳለሁ ማለት ነው። ይህ በደርግ/ኢሠፓ መንግሥት ላይ ተፈጽሟል። በዚያ ላይ ያበቃል ማለት ባይሆንም። "ብርቱ ጨለማ" ማለት ሰው መንገዱን አጥርቶ የማያይበት፣ የሚደነቃቀፍበት፣ የሚሰነካከልበት፣ በመንገዱ ላይ ከሚያጋጥመው ነገር ሁሉ ጋር የሚላተምበት፣ የሚጎዳበት፣ የሚወድቅበት፣ ማለት ነው። ሌሎቹ ምን ማለት እንደሆኑ መከታተልና መጠባበቅ ነው።

በፖለቲካው ሰፈር ከታየው መፍረክረክ የተነሳ የሰባዎቹ መጨረሻና የሰማንያዎቹ መጀመሪያ አመታት የወታደራዊው/ሶሻሊስታዊው መንግሥት መውደቅ ምናልባት ለራሱ ካልሆነ በስተቀር ለሌሎች ግልጽ የሆነላቸው ነበሩ። እንደ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ሁሉ አብዛኞቹ አማኞችም በብዙ ጉጉት ነበር ያንን የሚጠብቁት። ችግራቸው ሁሉ ከዚያ መንግሥት ጋር አብሮ እንደሚወድቅላቸው የሚመስላቸው ብዙ ነበሩ። እና እነዚህ ትንቢቶች፣ በተለይም "በፊታችሁ ብርቱ ጨለማ አለ" የሚለው ትንቢት በቀላሉ የሚቀበሉት አልሆነም።

ወታደራዊው/ሶሻሊስታዊው መንግሥት አዲስ አበባንና ቤተ መንግሥቱን ከለቀቀበት ከግንቦት 20 ቀን 1983 ዓ.ም. አንድ ቀን ቀደም ብሎ በአሜሪካ መንግሥት አደራዳሪነት ኢህአዴግንና ሻዕቢያን ጨምሮ ከትልልቆቹ ተቃዋሚዎቹ ጋር በሉንዶን ኮንፈረንስ ይቀመጣሉ። የኮንፈረንሱ ዓላማ ምናልባት በህዝቡ ምርጫ ሥልጣን የሚጨብጠው መንግሥት እስከሚታወቅበት ጊዜ ድረስ ተቃዋሚዎቹ ግንባሮችና በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት በስምምነት አንድ የሽግግር መንግሥት ስለሚመሠርቱበት ሁኔታ ለማደራደር ነበር ይሆናል።

አዲስ አበባ ከውስጥ በሚወድቀው መንግሥት ከውጭ ደግሞ በሚጥለው ተቃዋሚ ግንባር ቁጥጥር ተወጥራለች። በደስታና በስጋት፣ በተስፋና በቀቢፀ ተስፋ ታምጣለች። ሁለቱ ጉልበተኞች በከተማ

መሐል ተኩስ ቢካፈቱ፣ ሥርዓት አስከባሪ በሌለበት በዚህ ሁኔታ ውስጥ የተራበውና የጠገበው፣ በተለያየ ዓላማ ለዘረፋ ቢወጡ ሊከተል በሚችለው ነገር ፍርሃት ከተማዋ ተውጣለች።

ከጥቂት ቀናት በፊት ክርስቲያኑና እስላሙ ወደ አምላኩ እንዲጸልይና ምህረት እንዲለምን መንግሥት ተማጥኖአል። በዚህም መሠረት የአዲስ አበባ ነዋሪ እንደየእምነቱ በየቤተ ጸሎቱ ወደ እግዚአብሔር ሲጮህና ሲያለቅስ ውሏል። የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በኦርቶዶክስ፣ በካቶሊክ፣ በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያንና እንዲሁም በእስላም መስጊዶች መንዱና ሴቱ፣ አዋቂውና ወጣቱ በእንባ እየታጠበ ወደ አምላኩ ያቀረበውን ምህላ ከዕለታቱ ዋና ዋና ዜናዎች ጋር ለኢትዮጵያ ሕዝብ አሳይቷል።

የተፈራው የተኩስ ልውውጥና ዕልቂት፣ የተፈራውንም ያህል ዘረፋ ሳይሆን በአዲስ አበባ የመንግሥት ሥልጣን ከአንዱ ወደ ሌላው ኃይል በፀጥታ የተሸጋገረው ከዚያ ጸሎት የተነሳ እንደ ሆነ ነው የማምነው። ከጥቂት ቀናት በኋላ በእህል ጎተራ አካባቢ የከረመው የጦር መሣሪያ ዴፖ በእሳት በጋየ ዕለት በአጠገቡ ከከፉት የነዳጅ ዴፖዎችና ነዳጅ ጭነው ከቆሙትም ቦቴዎች አንዳቸውም ያልተመቱትና የአዲስ አበባ ከተማ ከታላቅ የእሳት አደጋ የተረፈችው በእዚያ ሁለት ቀናት ወደ እግዚአብሔር ከፈሰሰው የህዝብ እንባ የተነሳ እንደ ሆነ ነው የማምነው።

በእነዚያ ቀናት ማንም የማንንም ሃይማኖት አልተሳደበም። ማንም ከማንም ይልቅ ለእግዚአብሔር የተለየ ቅርበት እንዳለው አልተናገረም። ማንም ከማንም የተሻለ መመኪያ አልነበረውም። የሁሉ ሕይወት የሁሉም ንብረት፣ አደጋ ላይ ነበረ። ስለ ሆነም ሁሉም ወደ እግዚአብሔር ጮኸ። እግዚአብሔርም የእጆቹን ሥራዎች ጨክኖ አደመጠ። ምነው እንደዚያ ያለው የጸሎትና የምልጃ መንፈስ ቀደም ሲል ጀምሮ በእኛ ዘንድ ተገኝቶ ቢሆን ኖሮ? ምነው መንግሥትም ከድንፋታው ቀነስ አድርጎ ከጸሎቱ ጨመር እንዲል ሁኔታዎች አመቻችቶ ቢሆን ኖሮ? ዛሬ የምንጽፈው ታሪክ ሌላ በሆነ ነበር። ምን ያደርጋል? "ጅብ ከሄደ ውሻ ጮኸ" እንደተባለው ሆነ።

በዚህ ርዕስ ስር ልናገር የፈለግሁትን ግንቦት 18 ቀን ዕሑድ ዕለት የአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን በቁጥጥር ጥቂት ጥቂት እየሆኑ ለአምልኮ ከሚሰበሰቡባቸው ብዙ ቦታዎች በአንዱ ላይ የተነገረውን ትንቢት በመጻፍ ላጠቃልል።

> ልጆቼ ሆይ! ስለ ምን ፈጥናችሁ ትዘነጋላችሁ? እንዳልተነገረው፣ ምንም እንደማያውቅ ስለ ምን ትሆናላችሁ?

> ይህ ቀን እንደሚመጣ በባሪያዎቼ አፍ አልነገርኳችሁምን? ምድሪቱ በአንድ ቀን እንደምታምጥ ነግሬአችኋለሁ። እንደሚያጠራ እሳት ወጥቻለሁ። ሥርና ጉልላት እስከማይቀርለት፣ ፈልጋችሁ እስከማታገኙት ድረስ እቆርጠዋለሁ። አሁንም አድምጡ፦ ይሰበሰባሉ፣ ይነጋገራሉ፣ ይመካከራሉ። ነገር ግን ከእኔ ዘንድ አይደለም። በአንድ አሳብና በአንድ ልብ እስከሚመለሱ ድረስ አደቅቃለሁ። እናንተ ግን አትፍሩ። ሁሉን አስቀድሚ ነገርኳችሁ። ወደ ግራ፣ ወደ ቀኝ፣ ወደ ሰሜን፣ ወደ ደቡብ አትበሉ። አንዱ በሌላው ላይ ይነሳል። እጅግም ይበረታል። ጥቂት ጊዜ እሰጠዋለሁ። ነገር ግን ይረሳኛል። በራሱ ከንድ የሆነ ይመስለዋል። በልጆቹ ላይ፣ በቅዱሳኔም ላይ ይነሳል። በዚያን ጊዜ ፍፃሜ ይሆናል። ምድሪቱም ታርፋለች። ወደ ተዘጋጀላትም ደህንነት ትገባለች።

ይህንን ትንቢት የሰማን አማኞች በማግስቱ ስኞ በሉንዶን ከተማ ሊደረግ ያለው ኮንፈረንስ እንደማይሳካ፣ መጪውም ዘመን ብዙዎች የጓጉለትን ያህል የሠላም፣ የጸጥታና የዕረፍት እንደማይሆን በቅድሚያ አውቀነው ነበር። ተግተን ካልጸለይንና እግዚአብሔርም ጸሎታችንን እና ምልጃችንን ሰምቶ ካልራራልን በስተቀር በፊታችን ያሉት አመታት በአንዳንድ ረገድ ምናልባት ከቀደሙትም ይልቅ ፈታኝ ሳይሆኑ እንደማይቀሩ ለአንዳንዶቻችን ግልፅ ሆኖልን ነበር።

ሌላ ንውጥውጥ

የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴዋ ኢትዮጵያ ከፋሺስት ወረራ በኋላ ለሰላሳ ሦስት አመታት ያህል በአንፃራዊ ሠላምና መረጋጋት ኖራለች። ምንም እንኳን በትግራይ፣ በባሌ፣ በጌዴኦ (ያኔ ደራሳ)፣ በጎጃም፣ በኋላም በኤርትራ የጸጥታ ችግር አጋጥሞ የነበረ ቢሆንም በአብዛኛው ህዝብ የዕለት ከዕለት ኑሮ ላይ ጉልህ የሆነ መናወጥ አላስከተለም። የዚያ መንግሥት የጦር ሠራዊት ብዛት አርባ አምስት ሺህ ገደማ ነበር የሚገመተው።

ወታደራዊው/ሶሻሊስታዊው መንግሥት ወደ ግማሽ ሚልዮን የሚጠጋ የመከላከያ ኃይል ነበረው። በአፍሪቃ ከግብጽና ከደቡብ አፍሪቃ ቀጥሎ ተወዳዳሪ የሌለው ተብሎለታል። ከዚያ ሌላ በፖሊስ፣ በቀበሌ፣ በአብዮት ጥበቃ፣ በሞያ ማህበራት፣ በየመሥሪያ ቤቱ በተቋቋሙት መሠረታዊ የፓርቲው ጽህፈት ቤቶች፣ በደህንነት ቢሮዎች ምናልባት በሙቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ሌሎች ጠባቂዎች ነበሩት። ሆኖም ያ

መንግሥት በሥልጣን የቆየባቸው አመታት ማንም ሰው ዕረፍ
እንዳይኖረውና በዕረፍትም እንዳይኖር የሆነባቸው ነበሩ።

ምንም እንኳን “በማንም፣ በምንም የማይበገር መከላከያ ኃይ
እንገነባለን” እያለ የተለመደውን መፈክሩን ቢያስተጋባም ያ መንግሥ
በሥልጣን ላይ የቆየባቸውን አመታት ያለ እንቅልፍ እንዳሳለፋቸ
እናውቃለን። “እግዚአብሔር ከተማን ካልጠበቀ የከተማ ጠባቂዎ
ትጋት ከንቱ ነው” የሚለውን መለኮታዊ ቃል አላወቀም (መ
127:1) ነበርና ጠባቂዎቹን ባበዛ መጠን እግዚአብሔር ደግሞ ጠላቶች
አበዛበት።

የዚያን ዓይነት ኃያል መንግሥት፣ የዚያን ያህል ድርጅታዊ ጥንካ
ያለው መንግሥት ዕድሜ የንጉሡን መንግሥት ዕድሜ፣ ያው
ከጣሊያን ወረራ ወዲህ ያለውን፣ ግማሹን ያህል ብቻ ሆነ። ባ
ዘውዴ እንደሚሉት “የተፈሪ ኮከብ ደመቅ ብሎ መብራት” ከጀመረበ
ከ1916 ጀምረን ያሰላን እንደ ሆነ ደግሞ ሲሶውን ያህል ብቻ መሆ
ነው[19]። በወደቀም ጊዜ አወዳደቁ እግዚአብሔር እንደ ተናገረ
ሥርና ጉልላት እስከማይቀርለት፣ ተፈልጎም እስከማይገኝ ድረስ ሆነ።

የዚህች መጽሐፍ አምስተኛ ምዕራፍ ረቂቅ በሚጻፍበት ጊዜ የኢህአዴ
መንግሥት የዘጠኝ አመታት ዕድሜ አስቆጥሮአል። እነዚህም ዘጠ
አመታት ከጸጥታ ይልቅ የንውጥውጥታ አመታት ነበሩ ብንል ማጋ
አይሆንብንም። ግማሽ ሚልዮን የሚገመተው የቀድሞው መንግሥ
ጦር መፍረስና መበተን፣ በየብሔረ ሰባቸው በተደራጁት አፍቃሬ እ
ጸላኤ ኢህአዴግ የፖለቲካ ግንባሮች መካከል የተፈጠረው ውዝግብ
ፌዴራላዊ የሆነው የመንግሥቱ አስተዳደራዊ አወቃቀርና ያ
ያስከተለው ግብ ግብ፣ የዓለም ባንክና አይ ኤም ኤፍ የሚጭ
የስትራክቸራል አድጀስትሜንት ፕሮግራምና በዚያ የተሳበበው ከሥ
መፈናቀል፣ የንውጥውጥታው ዳር ዳርታ ነበሩ።

የአስር ሚልዮን ኢትዮጵያውያንን ሕይወት አደጋ ላይ የጣለው ድርቅ
ረሀብ፣ በኢትዮጵያና በኤርትራ መካከል የተፈጠረው የድንበር ችግ
ከዚያም ጋር ተያይዞ የመጣው የሁለቱ ወንድማማች ህዝቦች ለብ
አመታት “አገሬ” ብለው ከኖሩባቸው ከኢትዮጵያና ከኤርት
መባረር፣ ባስከተለው ዕልቂት በሁለቱ አገሮች መካከል ለሰላሳ አመታ
የተካሄደውን ውጊያ እንደ ልጆች ጨዋታ ያስቆጠረው እጅግ አሰቃ
ጦርነት፣ የንውጥውጥታው አካላት ናቸው።

ከ“ቀላፊው” ኤች አይ ቪ ኤይድስ የተነሳ ያለ ወላጅ የቀሩት
ከግማሽ ሚልዮን በላይ ልጆች፣ የቫይረሱ ተሸካሚ የሆኑትን ከሦስ
ሚልዮን በላይ አምራች ዜጎች፣ ቁጥራቸው በአሁኑ ጊዜ ሰባት ሙ

ሃምሳ ሺህ ደርሷል የሚባለውን “የጎዳና ተዳዳሪዎች”፣ የሁለተኛ ደረጃ
ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ በየአመቱ ወደ ሥራ አጡ ጎራ
የሚቀላቀሉትን ከአንድ መቶ ሺህ በላይ ወጣቶች፣ ሂሳብ ውስጥ
ስናስገባ ንውጥውጥታው የቱን ያህል የከፋና እየከፋም የሚሄድ መሆኑን
እንገነዘባለን። እነዚህ የእኛ ግምት ሊዳስሳቸው የቻለው ናቸው።
ከእኛ ግምት ውጭ የሚከሰቱ ነገሮች ደግሞ ይኖራሉ። ለምሳሌ እንደ
ኤርትራው ጦርነት። በሻዕቢያና በኢህአዴግ መንግሥታት መካከል
እንደዚህ ያለ ጦርነት ይሆናል ብሎ ያሰበ ኤርትራዊም ሆነ ኢትዮጵያዊ
ወይም ሌላ ምናዊም የፖለቲካ ተንታኝ የነበረ አይመስለኝም።

ይኸኛውን ንውጥውጥታ ከቀድሞው የተለየና የባሰም የሚያደርገው
ነገር አለ። ይኸውም የሥላምና የፍቅር አምባ የነበሩትን አብያተ
ክርስቲያንም ያልራራላቸው መሆኑ ነው። በቀደመው ንውጥውጥታ
አብያተ ክርስቲያኑ ችግር ያጋጠማቸው ከውጭ ሲሆን ከውስጥ ጤና
ነበሩ። በዚህኛው ንውጥውጥታ ግን አብያተ ክርስቲያኑ ችግር
ያለባቸው ከውስጥ ሲሆን ከውጭ እስከ አሁን ጤና ናቸው። እስከ
አሁን ስለ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን አልሰማሁም እንጂ
አርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን፣ የሰባተኛው ቀን አክባሪ አድቬንቲስት
ቤተ ክርስቲያን፣ ከወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያን ብዙዎች
በንውጥውጥታው ተናውጠዋል። ይህም በውስጥ ካሉት ብዙዎቹን
ግራ አጋብቷል። በውጭ ካሉትም ብዙዎቹን ሁኔኛ መሸሻ አሳጥቷል።

በወርሐ የካቲት 1966 ዓ.ም. ጀምሮ ይህች ገጽ እየተጻፈች
እስካለችበት እስከ ወርሐ መስከረም 1993 ዓ.ም. ድረስ ያለማቋረጥ
ቀጥሎ ስላለ ንውጥውጥታ ነው የምናገረው። ተራውን ዜጋ
ከንጉሡ፣ ቁሱን ከጳጳሱ፣ ጭሰኛውን ከባለ ርስቱ፣ ጎልማሳውን
ከወጣቱ፣ መሐይሙን ከምሑሩ፣ መናጢውን ከተጃሩ፣ ነጋዴውን
ከገበሬ፣ ከተሜውን ከገጠሬ፣ ሲቪሉን ከመለዮ ለባሹ፣ አማኙን
ከአምላክ የለሹ፣ ሸማቹን ከአምራቹ ጭፍራውን ከአዝማቹ፣
ተማሪውን ከመምህሩ፣ አለቃውን ከምንዝሩ፣ እስላሙን ከክርስቲያኑ፣
ካህኑን ከምዕመኑ፣ ያገር ቤቱን በዐ ከሚኖረው፣ ባለ ትዳሩን
ካላገባው፣ እንዲያው ማንንም ከማን በለማይለይ፣ ኢትዮጵያዊ የሆነን
ሁሉ እንበለ ቀለም፣ እንበለ ቋንቋ፣ እንበለ ያታ፣ እንበለ ጎሣ፣
በገባበት እየገባ ስለሚያበራይ ንውጥውጥታ ነው የምናገረው። ከቀን
ወደ ቀን እየከረረና እየመረረ በመሄድ ላይ ስላለ ንውጥውጥታ ነው
የምናገረው።

የታሪክ ሂደት ነው? መሆን ስላለበት ነው የሚሆነው? በኛ ብቻ ሳይሆን
በሌሎችም ላይ እየሆነ ስላለ ሊያስደንቀን አይገባም? መሪዎቻችንና
የአመራር ዘይቤአቸው ነው ለዚህ ምክንያቱ? ወይስ ሕዝባችን
ለመሪዎቹ አለመመቸቱ? አለመማሩ፣ አለመሰልጠኑ ነው ምክንያቱ?

ወይስ መንቃቱ፣ ራሱን ማወቅ፣ መብቱን መጠየቅ መጀመሩ? የብዙ ብሔረሰቦች አገር መሆናችን ነው ሰበቡ? ደሀነታችን ነው ዳፋው? እምነታችንና አምልኮአችን ነው ጦሱ? ራስ ወዳድነት ያጠቃናል? አብሮ መኖር አናውቅበትም?

እነዚህ ሁሉ እውነትነት የለባቸውም አልልም። አለባቸው። የሆነ የሆነ ያህል። ሌላም እውነት ግን አለ ነው የምለው። በሁላቸው ላይ የሚያጠላ ሌላ እውነት አለ ነው የምለው። እየሆነ ያለው ሁሉ በዓላማ ነው እየሆነ ያለው ነው የምለው። እየሆነ ያለው ሁሉ እንዲያስከትል የሚጠበቅበት ውጤት አለ ነው የምለው። ሁኔታዎች ሁሉ፣ በማንም ሆነ በማን ቢከናወኑ፣ የልዑል እግዚአብሔርን ሉዓላዊ ፈቃድ ያገልግላሉ ነው የምለው። በሚቀጥለው ምዕራፍ ውስጥ ይህንን ሌላ እውነት፣ ይህንን ዓላማ፣ ይህንን የሚጠበቅ ውጤት፣ ይህንን ሉዓላዊ ፈቃድ ለማሳየት እሞክራለሁ።

አምስት

የግርጌ ማስታወሻዎች

1 ባህሩ ዘውዴ። "የኢትዮጵያ ታሪክ፣ ከ1848 እስከ 1966" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፣ 1989፣ ገጽ 235

2 በአማርኛ የተጻፈውን የንቡሥን ንግግር ይህ ጸሐፊ ማግኘት አልቻለም። እዚህ ላይ የተጠቀሰው ጸሐፊው እራሱ ከኢንግሊዝኛው የተረጎመው ነው። ኢንግሊዝኛውን ያገኘው "Just As I Am" ከሚለው የዶክተር ቢሊይ ግራሐም ግለ ታሪክ ነው። ገጽ 565

3 Graham, Billy, "Just As I Am- The Authobiography Of Billy Graham." Billy Graham Evangelistic Association 1997 Pp 565

4 Grubb, Norman. "Rees Howells: Intercessor" Christian Literature Crusade, Fort Washington, Pa, 1999 Edition. Pp 35

5 ልጅ አስራት (በኋላ ልዑል ራስ) የልዑል ራስ ካሣ ልጅ ሲሆኑ አቢይ አበበ (በኋላ ጄኔራል) ደግሞ የልዕልት ፀሐይ (የንቡሥ ልጅ) ባል ነበሩ። ሁለቱም በ1967 ዓም በወታደራዊው/ሶሻሊስታዊው መንግሥት በግፍ ተገድለዋል።

6 Ruscoe, Doris M. "The Intercession of Rees Howells". The Lutterworth Press, Cambridge 1983. Pp 22

7 Graham, Billy ———Pp 349

8 መጋቢ ስለሺ ከበደ አቶ ክንፉ ኤዳኤን በመጥቀስ እንደ ጻፈው። "የኢትዮጵያ ገነት ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፣ ክፍል አንድ 1951-1978" ለመካነ ኢየሱስ ሴሚናሪ የቀረበ የመመረቂያ ጽሑፍ፤ ግንቦት 1982 ዓ.ም. አማርኛ ትርጉም ከአዲስ ከተማ ገነት ቤተክርስቲያን የተገኘ። በተጨማሪም ጸሐፊው ከቀደምት የሚስዮኑ ሠራተኞች አንዱ ከሆኑት ከአቶ አብዲሣ ሑሪሲ እንደ ተነገረው። አቶ አብዲሣ በአዋሳው ኮንፈረንስ ላይ የአማሄ ቾቾ አስተርጓሚ ነበሩ።

9 Ramstrand, Karl. "Det Heliga Aventyret" den Kristna Bokringen, Stockholm. 2/1986 pp 107

10 Daoud, Jane Collins. "Miracles and Missions And World-Wide Evangelism" E. J. Storm Printing Co. 1953 pp 72

11 Williams, Brian. "The Gospel With Evidence." Brian Williams Evangelistic Association Ltd. 1968 Pp 34-35

12 Heflin, Ruth Ward. "Harvest Glory- I Ask For the Nations" Mc Dougal Publishing 1999 pp 128

13 ---------- pp 128

14 ---------- pp 128, 129

15 ---------- pp 179

16 ---------- pp 179

17 ---------- pp 179

18 Engelsviken, Tormod. "Molo Wongel A Documentary Report on The Life and History of the Independent Pentencostal Movement In Ethiopia 1960-1975". The Free Faculity of Theology, Oslo Norway. (ያልታተመ):: ገጽ 142

19 ባህሩ ዘውዴ ---------- ገጽ 140

ታህሣሥ 15 ቀን 1945 ዓ.ም.

ማዕርግ 30055 የአሥር አለቃ አርቢ ተሰለቀበበ የመድፈኛ ጠር መዋደቅ በጆሮአቸው የ ሆነው በ1935 ዓ.ም በመድፍ ተኩስ ላይ ሠለጥኖ ጀርባ የነበር ስለኖር በ1945 ዓ.ም በ ህዳር ወር ላይ አነሣ ሲነ ፈረንጂ ባየሬሳት በነበረት ላይ የሳንት መሆኑን በፊርማዉ አረጋገጫለሁ።

አርቢ ተሰለቀበበ

15th Tahesas, 1945 E.C. (24th Dec. 1952)

I, Corporal Arabe Tekleyesus, No. 30055 of the Artillery Headquarters, who have been deaf in both ears since 1935 E.C. (1942) as a consequence of heavy cannoning, hereby testify and confirm that I got my hearing in Heolar 1945 (Nov. 1952) after hearing the sermons of the European lady.

right thumb impression: CPL Arabe Tekleyesus.

ታህሣሥ 15 ቀን 45 ዓ.ም.

ማዕር 290235 የኃ አለቃ መንገሻ ወልደሥላሴ የማስ የቆር ሠራዊት ሣረጀት ሠራር በጆሮአቸው የሆነው በ1942 ዓ.ም ጀምሮ የዉለቱም ጎዶናች የማየት ጋይነ አነሰለቶዉ በመሪ በነዝ የቆጂ በ1945 ዓ.ም በህዳር ወር ላይ አነሣ ሲነ ፈረንጂ ባየሬሳት በነበረት ላይ ሳንቱም ጎዶነ የሳነች መሆነነ በፊርማዉ አረጋገጫለሁ።

መንገሻ ወልደሥላሴ

2. Blind soldier healed.

15th Tahesas, 1945 E.C. (24th Dec. 1952)

I, Sergeant Mangasha Wolde Selassie, No. 290235 of the Imperial Ethiopian Army, who have been totally blind since 1942 E.C. (1950) hereby testify and confirm that I recovered my sight in Hedar 1945 E.C. (Nov. 1952) after hearing the sermons of the Healing European Lady.

right thumb impression: Sgt. Mangasha Wolde Selassie.

የተፈወሱ ሰዎች ለፖሊስ የሰጡት ቃል (1945 ዓ.ም.)

THE ETHIOPIAN HERALD

Published Weekly by the Ethiopian Press and Information Office — Tel. 1555
Editor: DAVID A. TALBOT.

No. 25 - Vol. 10
Saturday, December 13, 1952.

Visiting Faith Healer Having Great Success in Work in The Capital

By Our Own Reporter

Miss Jane Collins, the faith healer, who has been preaching and healing the sick and infirm for the past six weeks here in Addis Ababa was interviewed by one of our reporters. The missionary's desk in her apartment was covered with photos of the crowds that attended her meetings and written testimonials of several of the persons healed through her medium.

As a report on the services held since her arrival here, Miss Collins said:

"From the first meeting, which averaged about 700 people, the attendance has increased greatly, sometimes averaging near to 15,000. The authorities, and especially the Police, have been very gracious and cooperative, and the Lord has marvellously blessed his word."

God's Blessings

Asked about the number of persons healed through her sermons and her prayers, the faith healer replied:

"We can only judge by the public testimony given to God by those who have been touched by his blessings. I cannot therefore say exactly how many souls have been redeemed and how many bodies healed through the power of faith and prayer."

Producing a wad of papers, Miss Collins showed many written testimonials signed by persons healed, some names of others, photographs of some of them and of the huge crowds of people which came to the meetings.

Among them were some who were sick and maimed in many ways with ailments thought to be incurable. They included sufferers from cancer, tuberculosis, blindness, deafness, dumbness and others. Several cripples were in the lot.

"In every meeting", declared Miss Collins, "people testified that they were healed. Some of them publicly said that they were sick for years and that they had lost hope of recovery. I can only thank God that he has blessed His word and fulfilled His promise, as is written in the Bible."


Many Cured

The faith healing missionary told of three soldiers who were healed: one was deaf and dumb, one blind, and the other, registered in his company as deaf. In addition, Makuria Teferilegn, after being crippled for 21 years, was able to walk; Wondu Aye who suffered from cancer and swelling for six years testified to healing; so also Shaitu Damti who had the same ailment for 14 years; Yadatu Gomtu, 70 years old, was healed from blindness after 17 years of darkness.

God's Tools

What exactly are the tools you use in this faith healing mission? Miss Collins was asked. "My only tools are the word of God — the simple gospel and faith in the Lord Jesus Christ. Those who are healed through my medium, naturally, believe and have faith in God," she declared.

Miss Collins holds her meetings now at Jan Meda at the same hours as before, with a morninig and afternoon service on Sundays. This is probably her last week here, as she expects to visit other parts to help the sick.



(Above) The Major of the Police force recording the names and cases of those testifying to healing.

(At left) Photostatic copy of the daily Police Records of healings in Addis Ababa, Ethiopia, Nov. and Dec., 1952, during revival. (Translation follows on next page.)

Retired Judge of the High Court Testifies



Evangelist Daoud, Judge Heletework and son, Aklog.

Kentiba Heletework Ishete
Judge of the High Court
(Retired)
Addis Ababa, Ethiopia
December 15, 1952

"By the Grace of God I witness the following:

"My son, Aklog Heletework, is now ten years old. He had been stricken with disease when he was five years old, and in consequence, his eyes, ears, and limbs were rendered useless. With the exception of Dr. Anderson of the Empress Zawditou Memorial Hospital, all the remaining doctors that have examined him, have said that he was hopeless, but even Dr. Anderson could help him little in spite of his gigantic efforts. I took him to the healing stream at St. Michael's Church in Yika, Addis Ababa, and after 15 days bathing, his limbs worked, and one eye and one ear were healed. The year following he began to talk, but his right ear and his left eye seemed to remain deaf and blind forever. I took him to the Haile Selassie Hospital and the eye specialist there told me to the effect that something wrong in his right ear makes a shadow to fall and to affect his sight, and that both cases were hopeless.

"Nevertheless, I never gave up hope, but was praying to God when I was informed of your revival and the miracles that were performed *during your preaching*. I took my boy to the prayers consecutively for eight days, and on the eighth day, thank God, during prayer, my son cried, 'Papa, my ear is opened.' Afterwards I found out that his eyesight was also restored at the same time! Glory be to God, who through His servant, a woman, who by nature is feeble and timid, showed His great mercies and might."

Signed: Kentiba Heletework Ishete.

To: Mrs. J. C. Daoud
Ras Hotel, Addis Ababa

አቡነ ማርቆስ፣ ቶዳሪ ዛኪ፣ መንፈላዊት ዳውድ እና ባለቤትዋ



Front row: Rev. Marcos, Director of the Coptic Theological Seminary in Ethiopia, with one of his teachers, Mr. Todari Zaki. Back row: Mr. Azar and friend, who gave us their own apartment to live in, and Evangelist and Mrs. Daoud at the airport.

Addis Ababa, December 26, 1952.

"After what had been already written about Mrs. Jane Collins Daoud in the Egyptian papers, she was anxiously received in Addis Ababa in November of 1952. One week after her arrival, she began her meetings on the football playground.

"I had the pleasure to attend the first meeting and two other meetings. In every one of these meetings there were some cases which were healed, most of which were chronic diseases. I was told by some of my Ethiopian friends who hold high positions in the government that there were some strange cases which were miraculously healed.

"Many were impressed and showed confidence in her ministry by the fact that she acknowledged the power of healing was not due to her, but absolutely to God and to the faith of the sick person or his relatives. She preached in a great power; and the primary aim of her preaching was to deliver the message of repentance.

"My best wishes to her, hoping that God may use her as an instrument for healing the spirit and body of as many as possible, and for the Glory of His Name!"

Signed: Rev. Marcos.



ከ12ቱ የዳግማዊ ምኒልክ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች አስሩ
(1943 ዓ.ም.)



ብራዮን ቂልያምስና ባለቤቱ



ሩት ዋርድ ሑፍላን
(1960 ዓ.ም.)